# በ ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ-ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የኤምኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

አመልማል ተሻለ

ሰኔ 2004 ዓ. ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣
የጆርናሊዝና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ
ምርቃ መርሀ ግብር

# በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጦች ገላጭ-ጥናት

በ

አመልማል ተሻለ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ሰኔ 2004 ዓ. ም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| [illegible] | |
| የፈታኝ ስም | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ [illegible] | |
| የውጭ ፈታኝ [illegible] | |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ዲግሪዬ ላይ ከስነጽሁፍ ጋር እንደተዋወቅ ሳደረጉኝና በሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ቆይታዬ ደግሞ በርካታ ስነጽሁፋዊ ጉዳዮችን እንድገነዘብ ያስቻሉኝ መምህሬና አማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያለመሰልቸት በማረም እና አቅጣጫ በማስያዝ የዘወትር ምክራቸውና ማበረታታቸው ሳይለየኝ እዚህ ስለደረስኩ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ጥናቱ ከታሰበለት ግብ ይደርስ ዘንድ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን በማገናኘትና መረጃ በመስጠት በመስክ ቆይታዬ ያጋጠሙኝን ችግሮች ያቃለልሽልኝ ለእናቴ ወ/ሮ ደጅይጥኑ ምናለ አንችን የማመሰግንበት ቃል ስለሚያጥረኝ እግዚአብሔር ረጅም እድሜ ይስጥሽ፡፡

ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎችን በመስጠትና ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን በማገናኘት ቀና ትብብር ያደረጋችሁልኝ እና ስማችሁ በአባሪው የተጠቀሰው መረጃ አቀባዮቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

የትምህርት ወጭዬን በመሸፈን እና ውድ ጊዜህን ሰውተህ የጥናታዊ ጽሁፉን ግልጽ ያልሆኑ ሀሳቦችን በማቅናት ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከጎኔ ያልተለየኸው ጓደኛዬ ገብርሽ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

ለዚህ ጥናት ማስኬጃ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ማውጫ
ምስጋና ............................................................ i
ማውጫ ............................................................ ii
የፎቶ ማውጫ ............................................................ iv
የአማራ ክልል (ካርታ) ............................................................ v
የባንጃ ወረዳ (ካርታ) ............................................................ vi
ሙዳዬ ቃላት ............................................................ vii
አጠቃሎ ............................................................ viii
1. መግቢያ ............................................................ 1
1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............................................................ 1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ............................................................ 1
1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ............................................................ 2
1.4 የጥናቱ ወሰን ............................................................ 2
1.5 የአጠናን ዘዴ ............................................................ 3
1.5.1 የመረጃ አሰባሰብ ............................................................ 3
1.5.1.2 ምልከታ ............................................................ 3
1.5.1.3 ቃለ መጠይቅ ............................................................ 4
1.5.1.4 ቡድን ተኮር ውይይት ............................................................ 5
1.5.2 የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ............................................................ 6
1.5.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ............................................................ 6
1.6 ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎች ............................................................ 7
1.7 የመስክ ተሞክሮ ............................................................ 8
2. ክለሳ ድርሳን ............................................................ 10
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ............................................................ 10
2.2 የንድፈ ሃሳቦች ቅኝት ............................................................ 12
2.2.1 ቁሳዊ ባህል ............................................................ 12
2.2.2 የቁሳዊ ባህል መጠናት አስፈላጊነት ............................................................ 14
2.3 ሀገረሰባዊ ልብሶች ............................................................ 14
2.3.1 ልብሶችና ሀገረሰባዊ ማንነት ............................................................ 15
2.3.2 ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ............................................................ 16
2.3.3 የሀገረሰባዊ ልብሶች ፋይዳ ............................................................ 17


2.4 ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ........................................................................ 18
2.5 የቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረትና የአተናናተን ሂደቶች ........................................ 19
3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ገጽታና የማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ .............................23
3.1 የአዊ ብረሰብ ገጽታ ....................................................................... 23
3.2 የባንጃ ወረዳ ገጽታ ....................................................................... 23
3.3 መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት ሁኔታ .......................................... 24
3.4 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ........................................................................ 25
3.5 የወረዳው ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ ...................................................... 25
3.5.1 ሀገረሰባዊ ጋብቻ ..................................................................... 25
3.5.2 የለቅሶ ሥነ ስርዓት ................................................................. 29
4. የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና ጌጣጌጥ .......................................................... 31
4.1 ሀገረሰባዊ አለባበስ ....................................................................... 31
4.1.1 የሴቶች ሀገረሰባዊ ልብሶች............................................................ 31
4.1.2 የወንዶች ሀገረሰባዊ ልብሶች ......................................................... 36
4.2 ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች ..................................................................... 43
4.2.1 የአንገት ጌጥ .......................................................................... ..44
4.2.2 የእጅ ጌጥ ............................................................................... 50
4.2.3 የእግር ጌጥ .............................................................................. 51
4.2.4 የጸጉር አሰራር ........................................................................... 51
4.2.5 ውቅራት (ንቅሳት)........................................................................ 54
4.3 የባንጃ ሀገረሰባዊ ልብሶችና ጌጣጌጦች ፋይዳ............................................... 58
4.3.1 ዕድሜ መግለጽ ........................................................................... 59
4.3.2 ማህበራዊ ደረጃ ማሳያ.................................................................. 59
4.3.3 ከእርኩስ መንፈስ ለመጠበቅ............................................................. 60
4.3.4 እናትነትን ማሳየት ...................................................................... 60
4.3.5 ማህበራዊ ሁኔታዎችን መጠቆም ......................................................... 61
5. ማጠቃለያ ................................................................................... 62
የአማርኛ ዋቢ ምንጮች........................................................................... 64
የእንግሊዝኛ ዋቢ ምንጮች........................................................................ 66

# የፎቶ ማውጫ

ገጽ

ፎቶ1. ሽብሽቦ ........ 33
ፎቶ2. ጉንፍና ጎዶ ቀሚስ ........ 33
ፎቶ3. መቀነት ........ 34
ፎቶ4. ወንጨሬና ተነፋነፍ........ 36
ፎቶ5. ባተ ሁለት ........ 37
ፎቶ6. ቁምጣ........ 38
ፎቶ7. ለምድ ........ 39
ፎቶ8. ገሳ ........ 40
ፎቶ9. የጤና ልብስ........ 41
ፎቶ10. የአንገት ጌጥ ........ 44
ፎቶ11. ሳንቃ ድሪ ........ 45
ፎቶ12. ብር ቅጥል ........ 47
ፎቶ13. ቢሪጂ ........ 48
ፎቶ14. እርባን........ 49
ፎቶ15. አምባር ........ 50
ፎቶ16. አልቦ ........ 51
ፎቶ17. ጋሜና ቁንጮ........ 52
ፎቶ18. ሳዱላ........ 53
ፎቶ19. ውቅራቶች........ 54
ፎቶ20. የአንገት ንቅሳት........ 55
ፎቶ21. የእጅ ንቅሳት ........ 56
ፎቶ22. የእግር ንቅሳት........ 57

# የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ ካርታ




ምንጭ፡- አዊ ዞን ኮሚኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ሚዲያ

- የዞኑን ካርታ ማግኘት አልተቻለም




ምንጭ፡- አዊ ዞን ኮሚኒኬሽንና ኢንፎርሜሽን ሚዲያ

# ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| መብሩቅ | የወንዶች የጤና ልብስ |
| መጎነፍ | በጎማ ላስቲክ ማያያዝ (መስፋት) |
| መዶክዶክ | በተደጋጋሚ መስፋት (መደረት) |
| ማጫ | ለሙሽራ የሚሰጥ ጥሎሽ |
| ሰባት ጉልበት | ሰባት ጊዜ የሚቆጠር የዘር ሀረግ (ትውልድ) |
| ሶማያ | ሙሽራ የሚይዘው በትር (ዱላ) |
| ቡላን | አባት አምላክ የሚባል መንፈስ |
| ትፍትፍ | ያልተፈተለ ዘርፍ |
| ወፍ እግር | በሰው እጅ የሚሰፋ ሲሆን ለጋቢና ለነጠላ የሚያገለግል |
| ቀዋጂይ | ለሞተ ሰው የሚለቀስ ስሆን ሂዶ ቀረብኝ ማለት ነው |
| አብዚ | የተደራረበ እንጀራ ሆኖ ቅቤና ሌላ ነገር የተቀባ (ጉዝጉዞ) |
| አንጡራ | ቋሚ ንብረት |
| አይነታ | ዋናው ቀን |
| እዳይት | ልብሶች ላይ የሚደረግ ጥለት |
| ክርክም | በአጭሩ ተቆርጦ ዳርዳሩን (ግንባር አካባቢ ዙሪያውን) መላጨት |
| የስር ሚዜ | የመጀመሪያ ሚዜ |
| ጉሊት | በእርሻ ላይ የሚገኝ የተያያዘ አፈር |
| ጎዶ | ጥለት የሌለው ልቅ ቀሚስና ጥለት የሌለው ጋቢ |

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በባንጃ ሃገረሰባዊ ልብስ እና ጌጣጌጦች ገላጭ ጥናት ላይ የሚያተኩር ነው:: አበይት ዓላማዎቹም በአዊ ብሄረሰብ ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ ያሉትን የአለባበስና አጊያጊያጥ ውክል ናቸውን መመርመር፣ መሰነድ፣ መግለጽ እና ማሳየት ነው። ንኡሳን አላማዎችም በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ ማለትም ቸውሳ፣ ባታማሪያምና ቅዳማጃ ተብለው በሚጠሩ የገጠር ቀበሌዎች ያሉ ወጣቶች፣ እናቶችና አባቶች ምን ምን ባህላዊ ልብሶችን እንደ ሚለብሱ ምን ምን ጌጣጌጦችን እንደሚያደርጉ፤ ልብሶቹና ጌጣጌጦቹም ያሏቸው አገልግሎቶች ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ምን ምን እንደሆኑ ማሳየት ነው።

እንዲሁም የፀጉር አሰራርና የውቅራትን መልክ ማሳየት፤ የአለባበስ ስርዓቱን እና አጋጣሚዎቹን መግለፅ የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎችን ያካተተ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ልብሶቹ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት እንዴት እንደሚገልፁ እና በቁሶቹ ዙሪያ እየተደረጉ ያሉ ለውጦች ምን ምን እንደሆኑ ያሳያል:: በዚህም የተመረጡ ሶስት የፀጉር አሰራር፣ አስር ልብስ እና ስድስት የጌጣጌጥ አይነቶች ተተንትነዋል::

ይህ ጥናት የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ በተሰበሰቡ ቀዳማይ መረጃዎች የተመሰረተ ነው:: ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴ እንደ መሆኑ መጠን በታላሚ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ከተመረጡ እና ባህሉን ጠንቅቀው ያውቃሉ ከተባሉ ግለሰቦች፣ ከባህል ቢሮ ሰራተኞችና የእጅ ባለሞያዎች በቃለ መጠይቅ እንዲሁም ከመኖሪያ መንደሮች እና ከገበያ ቦታዎች በምልከታ በተወሰዱ መረጃዎች የተገነባ ነው:: ከእነዚህ ቀዳማይ ምንጮች ከተገኙ መረጃዎች በተጨማሪ ከጥናቱ ጉዳይ ጋር ከተያያዙ የጥናት ውጤቶች እንዲሁም ከመፃህፍት የተገኙ ሃሳቦችንም ያካትታል::

የአካባቢው ሃገረሰባዊ ልብሶች ከቁሳዊ ፋይዳቸው በተጨማሪ በባህሉ ባለቤቶች ዘንድ የሚታወቁ ተምሳሌታዊ ፋይዳዎች ያሏቸው ከመሆናቸውም በላይ የተለያዩ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎችን የሚያመለክቱ ትዕምርቶች ሆነው ያገለግላሉ:: በሚያስተላልፉት መልዕክት አማካይነትም እድሜን የማሳወቅ፣ ማህበራዊ ደረጃዎችን የማሳየት፤ከእርኩስ መንፈስ የመከላከል፤ እናትነትን እና የተለያዩ ማህበራዊ ሁኔታዎችን የማሳወቅ ፋይዳ ያላቸው መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል::

# 1. መግቢያ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በአዊ ዞን ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ በሚገኙ ልብሶችና ጌጣጌጦች ላይ የሚደረግ ነው። ጥናቱ በዋናነት በባንጃ ወረዳና በስሯ የሚገኙ ሶስት የገጠር ቀበሌዎችን ያካትታል። እነሱም ቻውሳ፣ ባታ ማሪያም፣ እና ቅዳማጃ ናቸው። እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡት የመጀመሪያው ከቀበሌዎች መካከል ለወረዳዋ በቅርብ በመገኘታቸው ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግም ለጥናቱ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ከሶስት በላይ ቀበሌዎችን በጥናት ለመሸፈን የጊዜ እጥረት የሚያስከትል በመሆኑ ነው።

ባንጃ አዊ ዞን ውስጥ የምትገኝ የወረዳ ከተማ ስትሆን በአካባቢዋም 26 የገጠር ቀበሌዎች ይገኛሉ። ኗሪዎቿ በአብዛኛው በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ ሲሆን ጎን ለጎንም የተለያዩ የእደ ጥበብ ስራዎችን ያከናውናሉ። ከእነዚህም ልብሶች፣ ከቀርቀሀ፣ከቀንድ የሚሰሩ ባህላዊ ጌጦች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የጥናቱ መግቢያ ምዕራፍ ስምንት ንዑሳን ጉዳዮችን አካቶ ይዟል። እነሱም የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች ናቸው። ሁለተኛው ምዕራፍ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የንድፈ ሀሳቦች ቅኝትን ያካተተ ሲሆን ሶስተኛው ምዕራፍ የተጠኚው ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መልኮች የተዳሰሱበት፤ በአራተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከተጠኚው ማህበረሰብ የተገኙት መረጃዎች ተገልጸዋል። በመጨረሻም የጥናቱ ማጠቃለያና የይሁንና ሀሳቦች ቀርበዋል።

## 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ጥናቱ በሚያተኩርበት አካባቢ የሀገረሰብ ሙያ ውጤቶች የሆኑትን ልብሶች እና ጌጦች የማህበረሰቡ አባላት በተለያዩ ጊዜያት ሲያጌጡባቸውና ሲለብሷቸው አስተውላለሁ። ነገር ግን በአካባቢው የእነዚህን ቁሶች በሚመለከት የተሰበሰበ መረጃም ሆነ የተደረገ ጥናት አላየሁም።

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የጥናቱ ዋና አላማ በአዊ ብሄረሰብ ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ ያሉትን አለባበስና አጊያጊያጥ ውክልናቸ ውን መመርመር፣መሰነድ፣ መግለጽ እና ማሳየት ነው። በዚህ ስር የሚከተሉት ዝርዝር አላማ ዎችም ይገኛሉ።

እነዚሁም

- ❖ የልብሶችንና የጌጦችን ምንነት እና የማንነት መገለጫነታቸውን እና አሰራራቸውን በእድሜ፣ በፆታ ከፋፍሎ ማሳየት
- ❖ የንቅሳት (ውቅራት) አይነቶች፣ የፀጉር አሰሟጨት አይነቶች በእድሜ እና በፆታ የመለያየታቸውን ምክንያት ማሳየት እንዲሁም የማህበረሰቡን ማንነት እንዴት እንደሚገልፁ ማቅረብ
- ❖ የልብሶቹና የጌጦቹን ተግባር እና ማህበረሰቡ የሰጣቸውን ትርጉም ማሳየት
- ❖ ልብሶችና ጌጦች በምን መልኩና መቼ እንደሚደረጉ ማህበረሰቡ ያለውን ደምብ ማሳየት
- ❖ ልብሶችና ጌጦች የሚሰሩበትን ጥሬ እቃዎች መግለፅ

ጥናቱ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፡፡

- ➢ በአዊ ብሄረሰብ ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የሚታዩት ባህላዊ ልብሶች ምን ምን ናቸው? ጌጦችስ? አጊያጊያጣቸውስ ምን ይመስላል?
- ➢ የብሔረሰቡ ወንዶችና ሴቶች (ህፃን፣ ወጣት፣ ሽማግሌ) የሚለብሷቸው ልብሶችና የሚያደርጓቸው ጌጦች እንዲሁም አጊያጊያጣቸው በእድሜና በጋብቻ ሁኔታ ይለያያሉ?
- ➢ አለበበሳቸውና አጊያጊያጣቸው ከማንነት ጋር የሚያቆራኛቸው ጉዳይ አለ ?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ❖ በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ ወደ ፊት ሰፋ ያለ ጥናት ይካሄድ ዘንድ አዎንታዊ ግፊት ይፈጥራል፡፡
- ❖ ስለ አዊ ብሄረሰብ በቁሳዊ ባህል ረገድ ማንነታቸውን ማወቅ ለሚፈልጉ ወገኖች መረጃ በመስጠት ያገለግላል፡፡
- ❖ በሀገራችን ያሉ ብሄረሰቦች ቁሳዊ ባህል በስፋት ባለመጠናቱ በዘርፉ ያለውን ክፍተት በመሙላት ረገድ የራሱን አስተጾ ያደርጋል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ክልል አዊ ዞን ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የሚገኙ የአዊ ብሄረሠብ አለባበስና አጊያጊያጥን በተመለከተ መግለፅና ማሳየት ላይ የተወሰነ (የተገደበ) ነው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

ባንጃ አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች በሚለብሳቸው ልብሶችና አጊያጊያጥ ማንነቱን እንዴት እንደ ሚገልጽ ና መልዕክቱን በመግለጽ ጥናቱ ግብ ይመታ ዘንድ በዋናነት functionalism (ተግባራዊነት) ንድፈ ሀሳብን አካቷል፡፡ ከመስክ የተገኙት መረጃዎችን ለመተንተንም በገላጭ (descriptive study) የምር ምር ስልት ተተንትነዋል፡፡

## 1.5.1 መረጃ አሰባሰብ

ይህ ጥናት ቀዳማይና ካልዓይ መረጃዎችን ተጠቅሟል፡፡ ከቤተ መጽሀፍት እና የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበዋል፡፡ Best (1981:254) Marshallን እና Rossmanን ጠቅሰው በአይነታዊ ምርምር ጽሁፋዊ ሰነዶች ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡ በዚህ መሰረት በመጀ መሪያ በቤተ መጽሀፍት የፎክሎር ንድፈ ሀሳቦች እና ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት የጥናት ስራዎች ተቃኝተዋል፡፡ ቀጥሎም ፈቃደ አዘዘ (1991:90) እንደገለጹት በመስክ ስራው በተደረገው ምልከታና በተካሄደው ቃለ መጠይቅ እንዲሁም በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙ መረጃዎች በማስታወሻ፣ በመቅረጸ ድምጽ በቪዲዮና በፎቶግራፍ ተይዘዋል፡፡ ስለዚህ ከላይ የተ ዘረዘሩትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ዘዴዎችን በተመለከተ ማብራሪያ ቀጥሎ እንደሚከ ተለው ይሆናል፡፡

### 1.5.1.2 ምልከታ

በመስክ ስራ ወቅት መረጃ ሰብሳቢው በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም ቢችልም የተለያዩ የህብረተሰብ ሳይንስ አጥኝዎች ምልከታን እና ቃለ መጠይቅን በዋናነት እንደሚጠቀሙ Goldstein (1974:77) ገልጸዋል፡፡

እኔ ደግሞ በመስክ ቆይታዬ ወቅት ምን አይነት ሂደቶችን በመከተል በምልከታ መረጃዎችን እንደሰበሰብኩ በዚህ ንዑስ ክፍል እገልጻለሁ፡፡ ምልከታው የተካሄደው በተፈጥሯዊ እና ቅንብር ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ ተፈጥሯዊና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶችን በምልከታ ወቅት መጠቀም መረጃዎችን የተሟሉ ለማድረግ ያላቸው አስተዋጾ የጎላ መሆኑን Goldstein (1964:50-90) እና ፈቃደ (1991:122-124) መክረዋል፡፡

የአንድን ማህበረሰብ ባህል ለማጥናት የስዓታት አስተውሎት የማይበቃ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት ለ50 ቀናት (ከጥር 11 እስከ የካቲት 5 2004 ዓ.ም እንዲሁም ለሁለተኛ ጊዜ ከየካቲት 22 እስከ መጋቢት 18 2004 ዓ.ም) በመስክ ስራ ላይ በመቆየት ከቃለ መጠይቁ ጎን ለጎን ምልከታ አካሂጃለሁ፡፡ በተፈጥሯዊ መቸት የተካሄደው ባንጃ ወረዳ በየሳምንቱ ማክሰኞ እለት በሚውለው የገበያ ቦታ፣ በሸማም ሆነ በጌጣጌጥ ስራ ላይ በተሰማሩት ሙያተኞች የመስሪያ ስፍራ፣ በዞኑ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት አዘጋጅነት በተካሄደው የባህል ፌስቲቫል፣ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ያቋቋመው የአዊ ባህል ቡድን አባላት ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት በአካል በመገኘት የልብሶችን እና የጌጣጌጦቹን ቅርጽ ቀለም የአሰራር ሁኔታ በቪዲዮና በፎቶ ካሜራ ምስላቸውን ቀርጫለሁ፡፡ በቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ደግሞ መለበሳቸው እየቀረ የመጡትንና በግለሰብ እጅ ያገኘኋቸውን ልብሶች ወጣቶችን እናቶችን እና አባቶችን በማልበስ ከላይ በተጠቀሱት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የምስል ቀረጻ አካሂጃለሁ፡፡

በምልከታ ወቅት የድርጊቱ ሙሉ ተሳታፊ እና ቀጥተኛ ታዛቢ በመሆን ረገድ የተመልካችነት ሚና አንዱ ከአንዱ እንደሚለያይ የታወቀ ነው፡፡ እኔ ግን ትኩረት ካደረግኩባቸው አጋጣሚዎች የበለጠውን ጊዜ የሰጠሁት በሙሉ ተሳታፊነት ሳይሆን በቀጥታ ተመልካችነት ነው፡፡ ምክንያቱም በምልከታ የሚሰበሰበውን መረጃ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በጽሁፍ ማስታወሻነት ለመያዝ ስለፈለግኩ ነው፡፡

### 1.5.1.3 ቃለ መጠይቅ

ይህ ጥናት ገላጭ የምርምር አይነትን እንደተከተለ ቀደም ሲል ተጠቅሷል፡፡ በዚህ አይነት መንገድ ለሚካሄደው ምርምር መረጃን ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ አይነተኛ መሳሪያ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆነው መረጃ መሰብሰብ በቃለ መጠይቅ እንዴት እንደተከናወነ ቀጥዬ እመለከታለሁ፡፡

ቃለ መጠይቅ በብልሀት ተግባር ላይ ከዋለ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያና የማጠናቀሪያ ስልቶች በተሻለ መንገድ መረጃን ከዋናው ከምንጩ ለመሰብሰብ የሚያስችል አንዱ መንገድ እንደሆነ አለም እሸቱ (1992፡6) ይገልጻሉ፡፡ ለዚህ ቃለ መጠይቅ በመስክ ስራ ወቅት አስተማማኝነት ያለው መረጃን ሰብስቦ ለማጠናቀር ያስችላል ማለት ነው፡፡

እኔም ለቃለ መጠይቅ የሚሆኑትን ጥያቄዎች ከማዘጋጀቴ በፊት የምልከታ ጉብኝት እና በተለያዩ መጽሀፍት ላይ ንድፈ ሀሳባዊ ንባብ አካሂጃለሁ። ከዚህ በኋላ ደግሞ የቃለ መጠይቁ ሂደት በሁለት አይነት መንገድ አከናውኛለሁ። የመጀመሪያው የተነሳሁበትን አላማ መሰረት ያደረጉ እና ለአ ላማዬም ግብ መምታት ወሳኝነት ያላቸውን ጥያቄዎች (Structured interview) ከመረጃ አቀባ ዮቼ ጋር ከመገናኘቴ በፊት አዘጋጅቻለሁ። በሁለተኛው ደግሞ በድንገት ካዬኋቸውና ከመረጃ አቀባዮቼ ምላሽ ከሚፈልቁት ሀሳቦች በመነሳት ለጥናቴ አስፈላጊ ሁነው ያገኘኋቸውን (Unstru ctured interview) በቃለ መጠይቁ እንዲካተቱ አድርጌያቸዋለሁ።

በሁለቱም መንገዶች የቀረቡት ጥያቄዎች በአብዛኛው ማን? እንዴት? ምን? ከምን? መቼ? የት? የሚሉ መጠይቃዊ ቃላት የያዙ ናቸው። ልብሶቹን እና ጌጣጌጦችን በተመለከተ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚነገሩ ስነቃሎችን ምን ምን እንደሆኑ ለማወቅም ለመረጃ አቀባዮቼ ጥያቄ ቀርቦላቸ ዋል። በዚህ አይነት ሁኔታ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ክፍት በመሆናቸው መረጃ አቀባዮቼ ገደብ ሳ ይጣልባቸውና ብዙም ሳይጨነቁ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ተደርጓል፡

## 1.5.1.4 ቡድን ተኮር ውይይት

በአንድ አይነት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ከተለያዩ የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ልዩ ልዩ ምላሾች ሊገኙ ይችላሉ። እነዚህ የተለያዩ ምላሾቸ በመረጃ አቀባዮቼ መካከል በሚኖረው የአመለካከት፣ የአስተያየት እና የእውቀት ልዩነት እንደሆነ መገመት አያዳግትም። ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች የተገኙት ምላሾችም ልዩነታቸው ሰፍቶ መረጃው የተዛባ እንዳይሆን ለማ ድረግ የተተኳሪቡድን ውይይት ተካሂዷል። በውይይቱም ወጣቶች፣ ጎልማሶች እና የሀገር ሽማ ግሌዎች እንዲሳተፉ ተደርገዋል።

በዚህ ዘዴ ለውይይት የቀረቡት የቁሶቹ ተጠቃሚ የሆኑት ግለሰቦችን በሁለት ቡድን እንዲሁም የሃገር ሽማግሌዎች ከተጠቃሚዎች ጋር በመሆን ሌላ ሁለት ቡድን በመመስረት ሲሆን የሀገር ሽማግሌዎችን ብቻ ያሳተፈ ደግሞ ሶስት ቡድን ናቸው። በመጀመሪያ ሁለቱ ቡድኖች የተወያዩት ስለማህበረሰቡ ማህበራዊ ሁኔታ ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን 5 እና 7 ሰዎችን ያቀፈ ነው። ከነዚህ ውስጥም 4 ወንድ 8 ሴቶች ናቸው። ሌላው ሶስቱ ቡድን ደግሞ የቁሶቹ ተጠቃሚ ሲሆኑ ወጣቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ናቸው። ስለ ልብሶቹ በተመለከተ መረጃ ሰጥተዋል። በዚህም በየቡድኖቹ ውስጥ 5 ሴቶችና 6 ወንዶች ተሳትፈዋል። እንዲሁም በሁለቱ ቡድኖች የሀገር

ሽማግሌ ሁለት ሴቶች፣ሁለት ወጣት ወንዶችና አንድ ጎልማሳ የተካተቱበት ነው። ውይይቱ የተካሄደውም በተለያየ ስዓትና ቦታ ነው።

### 1.5.2 የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ከዞኑና ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤት ሰራተኞች፣ እና ለጥናቱ በተመረጡ ሶስት ቀበሌዎች ላቅ ያለ ዕድሜ ያላቸው መረጃ አቀባዮች ተመርጠዋል። ከነዚህም መካከል የስራ መደባቸው ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥ ሆኖ ያገኘኋቸው ሶስት ሲሆኑ በዞኑና በወረዳው ባህልና ቱሪዝም መስሪያ ቤቶች ባህልን በተመለከተ ግንዛቤ አላቸው ተብለው የተጠቆሙኝ እና እንደዚሁም በሶስቱም ቀበሌ አስተዳደሮች ውስጥ ላቅ ያለ ዕድሜ ኖሯቸው መረጃን ሊያቀብሉ ይችላሉ ተብለው ዝርዝራቸው የተሰጠኝ 7 ወንዶች እና ሶስት ሴቶች በድምሩ አስር ጎልማ ሶችና አዛውንቶች ተመርጠዋል። በጌጣጌጥ ስራ ላይየተሰማሩ ሶስትወንዶች በሽማ ስራ ላይ የተሰማሩ ሶስት ወንዶች መረጃ አቀባይነት ተሳትፈዋል። ለዚህ ጥናት ወንዶች 10 ሴቶች ደግሞ 11 በድምሩ 21 ሰዎች በቁልፍ መረጃ አቀባይነትና በረዳት መረጃ ሰጭነት ተሳትፈዋል።

### 1.5.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በተለየዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ማለትም በቃለመጠይቅ፣ በምልከታ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እንዲሁም በንባብና ማስታወሻ በመውሰድ የተሰበሰቡት መረጃዎች የጥናቱን ዓላማ እና ጥያቄዎ ች በሚመልስ መልኩ ተደራጅተው ተተንትነዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎችም በገላጭ የምርምር ስ ልት[1] የተተነተኑ ሲሆን ገለጻውም የተካሄደው የተጠኝ ቁሶቹን አገልግሎቶች ምን ምን እንደሆኑ እ ና ከምን ከምን እንደተሰሩ በማብራራት ነው። በተጨማሪም ልብሶቹና ጌጣጌጦቹ ከዘወትራዊ አገል ግሎታቸው ውጭ ሌላ ነገር በውክልና የመቆም ተግባራት እንዳሏቸው በአካባቢው ባህል መሰረት ማየት ነው። በዚህም ልብሶችን ከጾታ አንጻር በመከፋፈልና ጌጣጌጦችን ከሚደረጉበት የሰውነት ክፍል አንጻር በመመደብ ተተንትነዋል።

---

[1] በዚህ ጥናት ገላጭ ተንታኝ የምርምር ስልት ማለት ልብሶችና ጌጣጌጦችን ለመግለጽ የተሞከረበትን አጠቃላይ ሂደት ያመላክታል።

## 1.6 ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎች

በቅድሚያ የሚጠቀሰው ችግር የባለሙያዎቹ እንደ ልብ አለመገኘት እና ቢገኙም መረጃ ለመስጠት ያላቸው ፈቃደኝነት አናሳ መሆን ነው፡፡ በተለይ ከውቅራት ባለ ሙያዎች፣ ከአንጥረኞች መረጃ ለማግኘት የተደረገው ጥረት አስቸጋሪ ነበር፡፡ አንጥረኞች የሚገኙት ከተማ አካባቢ በመሆኑና የእኔ ጥናት የአካባቢ ምርጫ ደግሞ ልብሶቹና ጌጣጌጦቹ ሲሰሩ የሚታዩባቸው ቀበሌዎች መሆናቸው አንጥረኞችን በተመረጡት ቦታዎች ማግኘት አልተቻለም፡፡ ካሉበት ሲገኙም መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ የማይሆኑበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ የውቅራት ባለሙያዎች ጥናቱ ባካተታቸው ቀበ ሌዎች የተገኙ እና ውቅራቱንም የሚያደርጉ መሆኑ ቢገለጽም ‹‹መንግስት መውቀር አጉል ባህል ስለሆነ አቁሙ ብሎናል›› በማለታቸው ከእነሱ መረጃ ለማግኘት የተደረገው ጥረት ከባድ አድርጎታል፡፡

ስነቃሎችን ለማግኘት መቸገርም ከመስክ ካጋጠሙኝ ችግሮች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ስነቃሎችን በአፈጣጠራቸውም ሆነ በአከዋወናቸው የሚነገሩበት አጋጣሚ (በዓላት፣ሰርግ፣ወዘተ.) የሚፈል ጉ በመሆናቸው ከቁሶቹ ጋር የተያያዙ ስነቃሎችን በአውዳቸው ማግኘት ተቸግሬ ነበር፡፡ ከስነቃሎቹ አውድ በተጨማሪ ስለ ባለሙዎች የተነገሩ ስነቃሎች ብዙዎቹነቀፌታን ያዘሉ በመሆናቸው እና ባለሙያዎቹን ፊት ለፊት መንቀፍ ደግሞ የተከለከለ በመሆኑ ስነ ቃሎቹን ማ ግኘት ተቸግሬ ነበር፡፡

የጌጣጌጥ እና የሸማ ስራ ሙያተኞቹ ገበያችንን አጥንተሽ ከፍተኛ ግብር እና የአገር ውስጥ ገቢ ዕዳ ስለምትጥይብን ለቃለ መጠይቁ ምላሽ አንሰጥሽም ብለውኝ ነበር፡፡

በአዊ የባህል ፌስቲቫል ወቅት ያገኘኋቸውን አንዳንድ መረጃዎች ውክልናቸውን ለማግኘት ቃለመጠይቅ በማደርግበት ስዓት ቀልባቸው ከዝግጅቱ በመሆኑ ሊነግሩኝ ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ የዞኑን ካርታን በተመለከተም ሙሉ መረጃ ለማግኘት አልቻልኩም፡፡

### ➢ የተወሰዱ እርምጃዎች

እነዚህን ችግሮች ለማቃለልም የተለያዩ ጥረቶች አድርጌያለሁ፡፡ ከጥረቶቹ መካከል ባንጃ ወረዳ በመሄድ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኛ በሆኑት በአቶ አዲሱ መንገሻ በኩል ለማግኘት መሞከር አንዱ ነበር፡፡ በባንጃ ወረዳ ያሉት አንጥረኞች ሁለት ሲሆኑ ከአቶ ከተማ ቢተው እና ከአባ ያየህ ሙሴ

መረጃዎችን ወስጃለሁ፡፡ ጥናቱ በተደረገበት አካባቢ ከተገኙት የውቅራት ባለሙያዎች ባታ ማሪያም ቀበሌ ነዋሪ ከሆኑት ከወ/ሮ የክትነሽ እና ከጽሀይነሽ አበራ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ፡፡

በተጨማሪም ስለ ባለሙያዎቹ ማህበራዊ ህይወት እና የአሰራር ሁኔታ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይቶች መረጃዎች ለማግኘት ባደረግኩት ጥረትም የተፈጠሩትን ክፍተቶች ለመሙላት ችያለሁ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ስነቃሎችን በአዊ ባህል ቡድን አባላት (በተለይ ከዘፋኞች) በመሰብሰብ፤ አንድም ከነዚህ መረጃ አቀባዮች ያገኘኋቸውን ስነቃሎች ለሌሎች መረጃ አቀባዮች በቃል እያነበብኩ እንዲነሳሱ እና ሌሎች ስነቃሎችን እንዲነግሩኝ በማድረግ፤ አንድም ስነቃሎቹን ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች በመሰብሰብ ችግሮችን ለማቃለል ችያለሁ፡፡

በመጨረሻም ከወረዳው አስተዳደር እንደዚሁም ከባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ደብዳቤ በማስጻፍ እና ሀላፊዎችም በአካል ተገኝተው ሙያተኞችን እንዲያሳምኑልኝ በማድረግ ችግሩን ቀርፌያለሁ፡፡ በፌስቲቫሉ ወቅት ያገኘኋቸውን የፎቶ መረጃዎች ውክልናቸውን የገጠር ቀሌዎች ባሉ ዕድሜ ባለ ጸጎች በመጠየቅ መረጃዎችን ለማግኘት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

## 1.7 የመስክ ተሞክሮ

የመስክ ስራው የተጀመረው አርብ ጥር 11 2004 ዓ.ም ሲሆን ከዚህ ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ከጥናቱ አማካሪ ለመስክ ስራዬ ጠቃሚ የሆኑ መመሪያዎችን ተቀብያለሁ፡፡ የመስክ ስራው የተጀመረው በተጠቀሰው ቀን በባንጃ ወረዳና በአዊ ዞን ዋና ከተማ እንጅባራ የአዊ የባህል ፌስቲቫል የሚከበርበት ዕለት በመሆኑ ይህን አጋጣሚ ለመጠቀም ችያለሁ፡፡

መረጃዎችን ለመሰብሰብ በአዊ ዞን ባንጃ ወረዳና አካባቢዋ (ቸውሳ፣ ባታ ማሪያም እና ቅዳማጃ) ቀበሌዎች የመስክ ጉዞ የተደረገው ሁለት ጊዜ ሲሆን በመጀመሪያው ጉዞ መረጃ አቀባዮችን የማፈላለግ፣ የመምረጥ፣ ከተመረጡት የመረጃ አቀባዮች ጋር የመገናኘት እና ራስን፣ አላማን ወዘተ. በዝርዝር የማስተዋወቅ ስራ ተካሂዷል፡፡

በሁለተኛው የመስክ ጉዞም የጥናቱ ተተኳሪ ወደ ሆነው አካባቢ ከደረስኩ በኋላ በቅድሚያ ከትምህርት ክፍሉ ያስጻፍኩትን ደብዳቤ ለአዊ ብሄረሰብ ዞን አስተዳደር ጽህፈት ቤት ሀላፊ በማስረከብ ስለ ዞኑ አጠቃላይ ገጽታ መረጃ ሊሰጡኝ ለሚችሉ መስሪያ ቤቶች ማለትም ለዞኑ ማስታወቂያ መምሪያ፣ የሚዲያ ማስፋፊያ የስራ ሂደት አስተባባሪ እና ለገንዘብ እና ኢኮኖሚ መምሪያ የመረጃ ኦፊሰሮች ደብዳቤ እንዲጽፉልኝ አድርጌያለሁ፡፡

በመጀመሪያ የመስክ ጉዞ ከተመረጡት መረጃ አቀባዮች ጋር በመገናኘት ተገቢው መረጃ በቴፕ፣ በካሴት ተሰብስቧል፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን ፎቶ ግራፍ የማንሳት ስራም ተሰርቷል፡፡ ከዚያም እስከ የካቲት 5/2004 ዓ.ም ድረስ ባሉት ተከታታይ ቀናት ሰነዶችን በመመርመር መረጃዎችን በጽሁፍ ሰብስቤያለሁ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ከትምህርት ክፍሉ የያዝኩትን ተጨማሪ ደብዳቤ ለዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ሀላፊ በማሳየት ተገቢውን ትውውቅ ካካሄድኩ በኋላ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች እንዲያዘጋጁልኝ እና ቁልፍ የሆኑ መረጃ አቀባዮችን እንዲጠቁሙኝ አድርጌያለሁ፡፡

ለቃለ መጠይቅ ምላሽ ይሰጣሉ ተብለው ከተጠቆሙኝ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ጋር ቃለ መጠይቁን ያካሄድኩት ወድያውኑ እንደተጠቆሙኩኝ ሳይሆን ከ12 ቀናት ላላነሱ ጊዜያት በእኔ እና በእነሱ መካከል ትውውቅ እና መልካም ግንኙነት ከፈጠርኩ በኋላ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ቤተሰባዊነትን ስለፈጠረልኝ ሰዎቹ ለምጠይቃቸው ነገሮች ሁሉ በጎ ምላሽ እንዲሰጡኝ ረድቶኛል፡፡

በመቀጠልም ከዞኑ የተጻፈልኝን ደብዳቤ ይዤ ወደ ቻውሳ፣ባታ ማሪያም እና ቅዳማኝ ገጠር ቀበሌዎች በመሄድ ለቀበሌ ሊቀመንበሩ ሰጥቻለሁ፡፡ እንዲሁም ለግሌ ‹‹ለሚመለከተው ሁሉ›› በሚል አድራሻ የተጻፈ ደብዳቤ በመያዝ ስራዬን ለማከናወን ችያለሁ፡፡ ለወረዳው ማስታወቂያ ፣ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት በተጻፈልኝ ደብዳቤ መሰረት ስለ ባንጃ ወረዳና ስለ አዊ ዞን አጠቃላይ ገጽታ የሚገልጹ መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በአንደኛው ከጥናቱ ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ በሁለተኛው ደግሞ ስለ ቁሳዊ ባህል እንዲሁም ስለ ልብሶችና ጌጣጌጥ የተሰጡ ንድፈ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

## 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ቀደም በአዊ ዞን በባንጃ ወረዳ እና አካባቢዋ አለባበስ እና አጊያጊያጥ ላይ የተደረገ ጥናት አላገኘሁም፡፡ ነገር ግን በአለባበስና አጊያጊያጥ ርዕስ ጉዳይ በሌሎች አካባቢዎች የተጠኑ ጥናቶች አሉ፡፡ እነሱም በዋግ ኽምራ ብሄረሰብና በከሚሴ ናቸው፡፡ እንዲሁም በወረዳዋና በብሄረሰቡዞን በፎክሎር ጥናት የተሰሩትን ለመጀመሪያ ዲግሪ እና ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን አግኝቼአለሁ፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ በአልጋነህ ደሴ 1984 ‹‹የአገውኛ እንቆቅልሽ አበጃጀት››፣ ወርቃየሁ አረጋ 1995 ‹‹የአዊ ብሄረሰብ (ሴንተ) የለቅሶ ስርዓት እና የአውኚ ዚንዚምኚ (ሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና››፣ በምንይበል ገዳሙ ‹‹የሰከላ ወረዳ እና በፋግታ ለኮማ ወረዳ የፋግታ አካባቢ ፈረሰኞች የሚያሰሟቸው ቃላዊ ግጥሞች›› ፈለገ ህይወት ዘገየ 1997 ‹‹በባንጃ ሽጉዳድ ወረዳ ቀብር ስነ ስርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና ይገኛሉ፡፡

በሁለተኛ ዲግሪ ደግሞ ማሞ ተፈራ 2002 ‹‹በመኸር ወቅት የሚፈጸሙ የቃል ግጥሞች ይዘት ትንተና በዳንግላ እና አካባቢዋ፣ ሰዋገኝ አስራት 2002‹‹ የፈረስ ማህበር እና ማህበራዊ ፋይዳው በአዊ ዞን ባንጃ፣ ሽጉዳድ እና እንጅባራ ዙሪያ ወረዳ›› ፣ብርሀኑ አሳየ በ1999 ‹‹በባንጃና በአንከሻ ወረዳዎች ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች በአዊኛ የሚያዜሟቸው የስራ ላይ ዘፈኖች ጭብጥ ገለጻና ትንትና ነው፡፡

አማራ ክልል ስር ከሚገኙት ሶስት የብሄረሰብ ዞኖች መካከል የዋግ ኽምራ ብሄረሰብ እና በኦሮሞ ብሄረሰብ በልብስና ጌጣጌጦች ዙሪያ የቀረቡ ጥናቶች አሉ፡፡ እነዚህም ከኔ ጥናት ጋር ስለሚገናኙ እነሱን እቃኛለሁ፡፡

በመጀመሪያ ዲግሪ ከቀረቡት ጥናቶች ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመድ ሆኖ ያገኘሁት ‹‹የወይዛዝርት አልባሳት እና ጌጣጌጥ ስሞች በአማራው ባህል ›› (1978) በሚል ርዕስ የቀረበው የውብሸት አሰፋ ስራ ነው፡፡ የውብሸት የጥናት አላማ በአብዛኛው መለበሳቸው እና ጌጥነታቸው የቀረውን የአማራ ወይዛዝርት ልብሶችን እና ጌጣጌጦችን ስም በመሰብሰብ መጭው ትውልድ ለስሞቹ ባዕድ ሳይሆን በሚገባ እንዲያውቃቸው ለማድረግ ነው፡፡ አጥኚው ለአላማው ግብ መምታት የተከተለው የአሰራር ዘዴ የልብሶቹን እና የጌጣጌጦቹን መጠሪያ ስሞች ከተለያዩ መጽሀፍት በመልቀም ቃላቱ ፍቻቸው ምን እንደሆነ ከመዝገበ ቃላት በመረዳት ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ሊያቀብሉ የሚችሉ ግለሰቦችን በማነጋገር ነው፡፡ ይህን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ቁሶቹን የሚለብሷቸውን እና የሚያጌጡባቸውን አጋጣሚዎች በመግለጽ አን ዲት ሴት ወይዘሮ የምትለብሳቸውና የምታጌጥባቸውን ነገሮች በመዘርዘሩ ነው፡፡ ልዩነቱ በጾታ ረገድ በወይዛዝርት ላይ ብቻ ሲያተኩር የኔ ጥናት ግን ጾታ አይለይም፡፡ በተጨማሪም ውብሸት መረጃውን የሰበሰበው ማህበረሰቡ ከሚገኝበት ቦታ ድረስ (እውዱ ላይ በመገኘት) ሳይሆን በቅርብ ያገኛቸውን ጓደኞቹን በመጠየቅና ቤተመጽሀፍት በተገኙት መረጃዎች ብቻ መሆኑ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ ያገኘሁት ሌላው ጥናት ‹‹ የጎጃም አካባቢ አልባሳት ስያሜ›› (1992) በሚል ርዕስ የቀረበው የአያል አድማሱ ጥናት ነው፡፡ የአጥኚው አላማም የልብሶቹን መጠሪያ ቃላት ስነቃላዊነት መመርመር እና ስለ ህብረተሰቡ ሁኔታ የሚገልጹ ስያሜዎች ምንን መሰረት እናዳደረጉ መተንተን ነው፡፡ አያል በጥናቱ የፋብሪካ ውጤት የሆኑት እና ከዘመናዊ ፋሽን ጋር የተያያዙት ልብሶች እንደመጡ ዋጋቸውን ፣ ቀለማቸውን ተፈላጊነታቸውን መሰረት ያደረጉ ስ ያሜዎች እንደሚሰጣቸው እየቆዩ እና እየተለመዱ ሲሄዱ ግን የለባሾችን እድሜ ጾታ፣ሙያ በሚያመላክቱ ቃላት መጠራታቸውን አመልክቷል፡፡ በመጨረሻም ልብሶቹ በለባሹም ሆነ በተመልካቹ ላይ የሚያሳድሩት ስሜት ለአብዛኞቹ ልብሶች ስያሜ ምንጭ ሆኖ እንደሚያገለግል አስረድቷል፡፡

የአያል ጥናት በልብሶች ላይ ትኩረት ማድረጉ እንዲሁም በጾታ እና በእድሜ ያልተገደበመ ሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ የአልባሳቱን የመለበሻ አጋጣሚዎች እና ባህላዊ አንድምታቸውን ባለ መመልከቱ ከኔ ጥናት ይለያል፡፡

ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከቀረቡ ጥናቶች ውስጥ ያሬድ ተፈራ (2002) ‹‹በሰቆጣና በአበርገሌ ወረዳዎች የሴቶች እና የወንዶች የአለባበስ እና አጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች›› በሚል ርዕስ አቅርቧል፡፡ አጥኝው አላማዩ ብሎ የተነሳው በሰቆጣና በአበርገሌ ወረዳዎች ተመርጠው ትንተና በተደረገባቸው ቁሶች አማካይነት የዋግ ኽምራ አገውን ባህላዊ አልባሳት እና ማጌጫዎች ማሳየት እና ቀርሶ ማኖርን ነው፡፡ አላማው ከግብ እንዲደርስ ለማድረግም ቁሶቹን፣ የቁሶቹን አሰራር፣ የቁሶቹን ተግባር ባለሙያዎቹን እና በቁሱ እና በባለቤት ማህ በረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሁም የተደረገባቸውን ለውጥ አጉልተው የሚያሳዩን ሉሳን አላማዎች ተዘጋጅተዋል:: ጥናቱ ጾታ ሳይለይ ሀገረሰባዊ ልብሶችን እና አጊያጊያጥን በማንሳቱ ይመሳሰላል፡፡ ልዩነቱ ደግሞ በዋግ ኽምራ አገው ሰቆጣ አካባቢ መወሰኑ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ከተደረጉ ጥናቶች መካከል ሰይድ ይማም (2002) ላይ ‹‹በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶች እና ሴቶች አለባበስ እና አጊያጊያጥ›› በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት አንዱ ነው፡፡ የአጥኝው አላማ በከሚሴ ከተማ ዙሪያ ባሉ ገጠር አካባቢዎች ያሉ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ምን ምን ልብሶችና እና ጌጦችን እንደሚጠቀሙ አልባሳቱ እና ጌጣጌጦቹም ያሏቸው አገልግሎቶች፣ ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ምን ምን እንደሆኑ መርምሮ ማሳየት ነው፡፡ አጥኚው በሚያጠናው ማህበረሰብ ወጣቱ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡ የእኔ ጥናት ግን የዕድሜ ገደብ ሳይለይ ሁሉንም የሚያጠቃልል በመሆኑ ከሰይድ ጥናት ይለያል፡፡

## 2.2 የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ንድፈ ሀሳቦች ይቃኛሉ፡፡

### 2.2.1 ቁሳዊ ባህል

ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ከፊሎቹ ቁሳዊ ባህል ማለት የቁሶች ስብስብ ሲሉ ሌሎች ደግሞ ቁሶች የሚጠኑበት የጥናት ዘርፍ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ፈቃደ አዘዘ (1991፡15) Dorsonንን ጠቅሰው

*ቁሳዊ ባህል  በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሠው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሀትን የልብስ የቤት የአጥር ወዘተ. አሰራርን የሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን ያጠናል ::*

ከላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ቁሳዊ ባህል ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚያመርቷቸውንና አካላዊ ህልውና ያላቸውን ነገሮች በሙሉ የሚያጠና የፍክሎር አይነት ነው። በተጨማሪም ቁሶቹ በምን አይነት ቴክኒክ እንደሚሰሩና ቁሶችንም ለመስራት ምን አይነት መሳሪያዎችን እንደሚጠቀሙ የምናጠናበት ዘርፍ እንደሆነ ያስገነዝበናል።

በሌላ በኩል ደግሞ Beals (1959፡229) ቁሳዊ ባህል የእደ ጥበብ ውጤት ለሆኑት ነገሮች በመጠሪያነት የሚያገለግል ነው በማለት አጠቃላይ የዕደ ጥበብ ውጤቶችን እንደ ሚያመለክት ነው። ስለዚህም የዕደ ጥበብ ውጤቶች መገልገያ መሳሪያዎችንና መያዥያዎችን፣ የምግብ ዝግጅቶችን፣ ልብሶችን እና ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች እንደ ሚያጠቃልሉ ይገልጻሉ። የሰው ልጅ ለህልውናው እንዲረዱት የሚያመርታቸው፣ የሚጠቀምባቸው፣ እነዚህንም ለማምረት ሚገለገልባቸውና አካላዊ ህልውና ያላቸው ቁሳቁሶች በሙሉ በቁሳዊ ባህል ስር እንደሚካተቱ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ እንችላለን። በተጨማሪም Glassie ቁሳዊ ባህልን እንደሚከተለው በይነውታል።

> *Material culture is the culture made material; it is the inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things, but not ending wtith them, the study of material culture uses objects to approach human thought and action (1999:41)*

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ቁሳዊ ባህል ተጨባጭ ለሆኑና የሰው ልጅ ባህልን መሰረት አድርጎ ለዕለት ከዕለት ኑሮው ማከናወኛ የሚሰራቸውን ቁሶች የሚመለከት መሆኑን ነው። ከላይ ፊቃደ ከሰጡት ብያኔ የቁሶችን ምንነትና የተሰሩበትን ዘዴ የሚመረምር መሆኑን ለማወቅ ሲቻል ከGlassie ብያኔ ደግሞ ፅንሰ ሀሳቡ የቁሶች ባለቤት የሆነውን የሰው ልጅን አስተሳሰብ እና ፍልስፍና በቁሶች አማካይነት መመርመር የሚቻል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም በአለም የሚገኙ ማህበረሰቦች አብዛኛው ታሪካቸው ለብዙ ዘመናት ተጠብቆ የቆየው በጽሁፍ

በሚገኙ መረጃዎች ሳይሆን ማህበረሰቡ በሰራቸው ቁሶች ነው። በዚህ ምንጮች በመሆኑም እንደሚያገለግሉ Glassie ገልጸዋል።

የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫም ቁሳዊ ባህልን እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ ወስዶ በመመልከት ልብሶችንና እና ጌጣጌጦችን መመርመር ነው። ምክንያቱም ማህበረሰቦች ልብሳቸው እንዴት እንደሚሰፉ፣ ቤታቸውን እንዴት እንደሚሰሩና እንዴትእንደሚጠቀሙ እንዲሁም እንዴት ቅርጽ እንደሚያወጡና እንደሚገለገሉባቸ መመርመር የቁሳዊ ባህል ተማሪውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው ብሏልና። (Dorson 1972፥2-3)

## 2.2.2 የቁሳዊ ባህል መጠናት አስፈላጊነት

የቁሳዊ ባህል ጥናት በተፈጥሮና በባህል መካከል ያለን ልዩነት በአዕምሯችን የምንስልበት ወዲያውም በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ፍላጎታችንን መሪ አድርገን ተፈጥሮን መልሰን መላልሰን የምንለዋውጥበትንና አዲስ ቅርጽ የምናስይዝበትን መንገድ የምናጠናበት ዘዴ ነው። የቁሳዊ ባህል ጥናት ታሪክን ከጥበብ ጋር አዋህደን የምንመለከትበት መነጽር ነው። Glassie (1999፡41) ደግሞ ቁሳዊ ባህል ባህልን መሰረት አድርጎ በማህበረሰቡ የሚሰራና ጥቅም ላይ የሚውል ቁስ ነው። የቁሳዊ ባህል ጥናትም ቁስ ነገሮችን በመጠቀም የሰው ልጆችን አስተሳሰብ እና ተግባር የማጥናት ዘዴ ነው።

## 2.3 ሀገረሰባዊ ልብሶች

የሀገረሰባዊ ልብሶችን (Folk costume) ምንነት በተመለከተ ትንተና ከሰጡት ምሁራን መካከል Yoder እና Wilson ይጠቀሳሉ። Yoder እንደ ገለጹት ሀገረሰባዊ ልብሶች አንድም የማህበረሰቡን ማንነት የሚያሳዩ ትዕምርቶችን የያዙ፣ አንድም በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦችና በማህበረሰቡ መካከል ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ። Yoder (በDorson ውስጥ 1972፡304) የሀገረሰባዊ ልብስ ተግባር አንድ ማህበረሰብ ከሌላ ማህበረሰብተለይቶ የሚታወቅ ባቸው ገጽታዎችን ማሳየት ነው በማለት ይገልጻሉ።

አለባበስን አስፍተን ስናየው የሰው ልጅ በሰውነት ላይ የሚያደርጋቸውንና የሚለብሳቸውን የተለያዩ ቁሶች ይገልጻል፡፡ በሽመና ከተሰሩ ጨርቆች በተጨማሪ በአካል ላይ የሚደረግ ቅብን፣ ላባዎችን እና የተለያዩ በእጅ ስራት የተዘጋጁ ልብሶችን ይይዛል፡፡

ሀገረሰባዊ ልብሶች በማህበረሰቡ ውስጥ ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉ ትዕምርቶችንና ቅርጾችን በመያዝ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት መግለጽ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ሀገረሰባዊ ልብሶች ስንል አንዱ ማህበረሰብ የኔ ብሎ በሚሰራበት ባህል ውስጥ በሚታወቁ ትዕምርቶች የበለጸጉ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተግባቦትን መፍጠር የሚችሉና በሚያስተላልፉት መልዕክትም የተለያዩ ማህበራዊ ፖለቲካዊና የመሳሰሉ ጉዳዮችን ማሳወቅና መግለጽ የሚችሉ ቁሶች ናቸው Wilson (1948)፡፡

ልብሶች ልዩ ልዩ መልዕክቶችን የማስተላለፍ ብቃት አላቸው፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ተግባቦትን በመፍጠር ነው፡፡ በልብሶቹ አማካይነት የሚተላለፈው መልክት የሚያ መለክተው የማህበረሰቡን ማንነት ነው፡፡ በትዕምርቶች አማካይነት የሚተላለፈው መልዕክት ትርጓሜ ደግሞ የሚወሰነው በለባሹ ማንነት ወይም በመለበሻ አጋጣሚውና በመለበሻ ቦታው ነው፡፡

### 2.3.1 ልብሶችና ሀገረሰባዊ ማንነት

ልብሶች በውስጣቸው ሁለት ገጽታዎች አሏቸው፡፡ አንደኛው አንድ ማህበረሰብ ባህሉንና ማንነቱን ለመጠበቅ ሲል በሚያደርገው ነገር እራሱን የሚገልጽበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ያ ግለሰብ በሚለብሰው ልብስ ሌላው አካል እሱን የሚረዳበት ሁኔታ ነው፡፡

Mathisen ማንነት በሁለት አይነት መንገድ ሊታይ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡

> ‹‹*The concept of identity has two mainconotation. From one point of view, it has to do with the feeling of something is and remains the same ,the feeling of continuty on the other hand having an identity also means being different from others» (በፈቃደ ውስጥ 2003፡355)*

እንደ Mathisen ገለጻ የመጀመሪያው የማንነት ጽንሰ ሀሳብ የነገሮች በተመሳሳይ መልኩ መቀጠል ወይም የቀጣይነት ስሜት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ከሌሎች ተለይቶ መታየት ነው፡፡ ማንነት በግለሰብ አልያም በማህበረሰብ ደረጃ ሊገለጽ ይችላል፡፡ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች በሚጋሯቸው የጋራ

ጉዳዮች መኖር ምክንያት ሀገረሰባዊ ማንነት ይፈጠራል፡፡ ይኸውም ከሌላው አካል እንዲለዩና እንዲታወቁ ያደርጋቸዋል፡፡ (Johnson in Dundes 1965፡43) የአንድ ህብረተሰብ የማንነት መገለጫ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ ልብስ ነው፡፡ ስለሆነም ልብሶች የአንድን ሰው ጾታ፣ ሀገራዊ፣ ጎሳዊና ክልላዊ ከየት መጣ ሊነግሩን ይችላሉ፡፡

## 2.3.2 ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (*Functionalism Theory)*

የአንድን ማህበረሰብ ባህል ለማጥናት ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች አንዱ የፎክሎር ፋይዳ ይጠቀሳል:: እነዚህ አጥኝዎችም (በተለይም የአሜሪካ ተመራማሪዎች) ፎክሎር በማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ ያለውን ፋይዳ ለማጥናት ሞክረዋል፡፡ በአውሮፓም ከአሜሪካ በተሻለ በዘመናዊው አለም የማህበሰብ ባህል አጥኝዎች በፎክሎር ፋይዳ ላይ ያተኮሩ ጥናቶችን በመምረጥ ጀምረዋል፡፡ Functionalism can be applied to materal aswell as to oral literature . In his monograph on the function of folk costume inMoravian slovakia, (fekade azeze 2003:231) ፋይዳዊነት ከቁሳዊ ባህል እና ለቃላዊ ስነጽሁፍም ያገለግላል፡፡

Functionalism በአንድ ባህል ውስጥ ፎክሎር ሊጫወት በሚችለው ሚና ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚያጠና ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ የጥንታዊ Functionalism ንድፈ ሀሳብ አራማጅ ዊሊያም አር ባስኮም ፎክሎር አራት ጥቅሞች እንዳሉት አመላክቷል፡፡ አንደኛ የማስተማር ሁለተኛ የማምለጥ ሶስተኛ የባህላዊ ማንነታችን መጠበቂያ አራተኛው የማህበረሰቡን ነባራዊ ባህልና ወግ ማሳያ ነው፡፡

Functionalism በአንድ ባህል ውስጥ ፎክሎር ሊጫወት የሚችለው ሚና ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚያጠና ዘዴ ነው፡፡ እንደ ፎክሎር ባለሙያዎች ገለጻ Functionalism ቃላዊ ልማዳዊና ቁስ አካላዊ ስብስቦችን የያዙ ፎክሎሮች ለህብረተሰቡ ምን እና እንዴት ይጠቅማሉ? የሚለውን የሚያጠና ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ የጥንታዊ Functionalism ቲዎሪ አራማጅ ዊሊያም አር ባስኮም ፎክሎር አራት ጥቅሞች እንዳሉት አመላክቷል፡፡

1. ማስተማር፡- ፎክሎር ላልተማሩት ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ጥቅም አለው፡፡ ለምሳሌ በአስራዎች የዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች ከአፈ ታሪኮች ከተረቶችና ከመሳሰሉት ጥንቁቅነትን ትጋትንና ብልጠትን ይማራሉ፡፡ በዚህም የልጆችን ባህርይ ለመቅረጽ ይችላል፡፡

2. ለማምለጥ፡- ይህ ከውስንና አይቻልም ባይነት ባህል ማምለጫ ነው፡፡ ፎክሎር ከውስንና በባህል ስም ከተጫኑብን ስርዓቶች ማምለጫ ነው፡፡ ከአሰልቺና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች ፎክሎር እንድንወጣ ያደርገናል፡፡ ይህም ደስታንና ፈንጠዝያን ይፈጥርልናል፡፡ ለምሳሌ፡- ተረት ማውራት ወይም ማዳመጥ ደስታን ይፈጥርናል፡፡ ምክንያቱም ታሪኩ መሳጭና አስደሳች ይሆናል፡፡ ለተራኪውም የራን ሀሳብ ለመጨመር እድል ይፈጥርለታል፡፡
3. ባህላዊ ማንነታችንን መጠበቂያ፡- አንድ ሰው ከማህበረሰቡ ባህል እንዲያፈነግጥ ፎክሎር ጥቅም አለው፡፡ ማህበረሰቡ ከሚደግፋቸው ባህሎች እና እሴቶች ሰዎች እንዳይወጡ ያደርጋል፡፡ በተረቶች እና በቀልዶች አማካይነት በስርቆት በፈሪነትና በክፋት ላይ ለመሳለቅ የህብረተሰቡ ባህል ተጠብቀው እንዲቆዩ ያደርጋል፡፡
4. የማህበረሰቡን ነባራዊ ባህልና ወግ ማሳያ፡- ፎክሎር የባህል ገጽታን ማሳያ ነው፡፡ በባህልና በአመለካከት አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያለውን ቁርኝት ያሣያል፡፡ በሰዎችና በባህል መካከል ያለውን ተፈጥሯዊ ቁርኝት መግለጽ ስለሚችል ሁለንተናዊ እይታና ገለጻ ይሠጣል፡፡ ለምሳሌ፡- የሰዎችን አለባበስ በማየት ስለመጡበት አካባቢ መግለጽ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በሆነ መልኩ Functionalism ቲዎሪ የአንድን ማህበረሰብ ስርዓትና ደንብ በተግባራቸውና ባላቸው አገልግሎት በማጥናት የእያንዳንዱን ደንብና ስርዓት ለይቶ ስለሚያቀምጥ ለፎክሎር ጥናት ከፍተኛ አስተዋፆ አለው፡፡

### 2.3.3 የሀገረሰባዊ ልብሶች ፋይዳ

ሀገረሰባዊ ልብሶች ተለብሰው ሰውነት ከመሸፈናቸው ባሻገር ለተለያዩ አገልግሎቶችም ይውላሉ፡፡ ከነዚህ ተግባራት ዋና ዋናዎቹም ማህበራዊ ደረጃን፣ ባህላዊና፣ ሀይማኖታዊ ሁኔታን የሚያ መላክቱ ተግባራት ናቸው፡፡

‹‹..*Categorizes magical, regional and national,age group,erotic, and everyday function.*›› በማለት ቁሳዊ ባህሎች በሚከተሉት መልኩ ተግባራቸውን ይመድቧቸዋል፡፡ ማጅካዊ ጠቀሚታ ያላቸው (የጤና ልብስ)፣ ሀይማኖታዊ ፋይዳ ያላቸው፣ አካባቢያዊ ፋይዳ ያላቸው፣ ብሄራዊ ፋይዳ ያላቸው የእድሜ ገደብን የመግለጽ ፋይዳ ያላቸው፣ ወሲብን የመቀስቀስ ፋይዳ ያላቸው፣ ሁልጊዜም የሚዘወተሩ (የስራ ልብስ) በማለት መድበውታል፡፡ (fekade azeze 2003:231)

ማህበራዊ ደረጃን ለማመልከት ሲባልም በዚህም መሰረት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የወንድና የሴትን ጾታ፣ ከህጻንነት ጀምሮ እስከ ሽምግልና ወቅት ያለውን የዕድሜ መለያየት ያገቡትን ካላገቡት ሴቶች ነጥሎ ማመልከት የሀገረሰዊ ልብሶች ተግባራት እንደሆነም (Dorson፡1972፡304) ይገልጻል፡፡

ሀገረሰባዊ ልብሱ በአንድ አካባቢ የሚኖረውን ህዝብ ባህል ወካይ ሆኖ ሲያገለግል ባህላዊ ሁኔታን ያመላክታል፡፡ የማህበረሰቡ አለባበስም የራሱን አሻራ ሊንጸባረቅበት ይችላል፡፡ ሰዎች በባህላቸው መሰረት በለበሱት ልብስ ያዘኑ ወይም በደስታ ላይ ያሉ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ስለዚህ ሰዎች በ ሀገረሰባዊ ልብሶቻቸው መልዕክትን ያስተላልፋሉ፡፡

## 2.4 ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ

ሰዎች ሀገረሰባዊ ልብስን ሲለብሱ ሊዋቡ የሚችሉባቸው ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች ይጠቀማሉ፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች የተለያዩ ነገሮችን ተጠቅመው የሚሰሯቸው ጌጣጌጦች አሉ፡፡ ከብር፣ ከነሀስ፣ ከብረት፣ ከፕላስቲክ፣ ከመዳብ፣ ከአልሙኒየም ወዘተ.. የተለያዩ ጌጣጌጦች ተሰርተው በእጅ፣ በእግር፣ በጣት፣ በጆሮ፣ በጸጉር ላይ እየተሰኩ እና እየተጠለቁ ለሰዎች መዋቢያነት ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ ከመዋቢያነት ባሻገር እንደ ወርቅ እና ብር ያሉት ማዕድናት በገንዘብ ማስቀመጫነት ይውላሉ፡፡

ሀገረሰባዊ ጌጦች ሰዎች እንዲያስውቧቸው የሚያበጇቸውና በባህላዊ መንገድ ተሰርተው የሚጠቀሙባቸው የጥበብ ውጤቶች ናቸው፡፡ ይህም ጥበብ ቀደም ያለ ታሪክ ያለው የጥበብ አይነት መሆኑን Evans እንዲህ በማለት ገልጾውታል፡፡

> Jewelary is one of the oldest the decorative arts. It answers to the deep human love of intrinsically beautiful materials, to the deep human wis h for bodily beautification and to the superstitious need for reinforcing hurnan powers by things that seem to a more lasting and more mysterious than man. (1970, 39)

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደቻልኩት ጌጣጌጥ ከቆየ የመዋቢያ ጥበቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህም ጥበብ የሰው ልጅ ለውብ ቁሶች ያለውን ጥልቅ ፍቅር፣ አካልን ለማቆንጀት ያለውን ጥልቅ ምኞትና ከሰው የበለጠ ብዙ ለቆዩ እና ሚስጥራዊነት ያላቸውን ነገሮች የሰው ልጅ ሀይልን ከማጠናቀር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚገልጽባቸው ናቸው፡፡ ጌጣጌጦች ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ጥንታዊ የጥበብ አካላት ናቸው፡፡

ሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ብዙ ጊዜ ለተጨማሪ ውበት የሚውሉ ቁሶች ሲሆኑ በጆሮ፣ በአንገት፣ በእጅ፣ በአፍንጫ፣ በራስ ወዘተ.. ላይ ሊደረጉም የሚችሉ ናቸው፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ በሰውነት ላይ የሚደረጉ ውቅራቶችም (ንቅሳቶችም) በሀገረሰባዊ ጌጥ ስር ይካተታሉ፡፡ ጌጣጌጦች እንደ ማህበረሰቡና እንደ መኖሪያ አካባቢው መለያየት ሁሉ በሚበጁበት ቁስ እና ቅርጽ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ በዚህ አይነቱ የልዩነት ሁኔታ ላይ Clark (1986:6) ትንታኔ አድርጓል፡፡ በትንታኔውም ጌጣጌጥን ለመስራት የዋሉት ቁሶቹና የጌጣጌጡ ቅርጽ እንደ ቁሱ መገኘት እንደ ማህበረሰቡ ፍላጎትና እንደ ባለሙያው የጥበብ ብቃት ከባህል ባህል ይለያያሉ፡፡ ጌጣጌጥ በአብዛኛው ሰዎች ተጨማሪ ቁንጅናን ሲሹ የሚሰሯቸው ቁሶች ቢሆኑም ከማስዋብ በተጨማሪ ከባህል ጋር የተያያዘ ተግባርም አላቸው፡፡ Clark (1986:7-12) የሀገረሰባዊ ጌጦችን ተግባር ሲገልጹ ከመዋቢያነት በተጨማሪ ያላቸው ተምሳሌታዊ (Symbolic) ፋይዳ ላይ አጽንኦት መደረግ እንዳለበትም ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ስለ ጌጣጌጥ ከተሰነዘሩ ንድፈ ሀሳቦች በሀገረሰባዊ ጌጣጌጥ ጥናት ወቅት ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ጉዳዮች የጌጣጌጦቹ መስሪያ ቁስ፣ ዲዛይን፣ባህላዊ ልዩነቶች፣ ማህበራዊ ደረጃዎች፣ተግባሮች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦቹ ለማህበሰቡ ከሚሰጡት ግልጋሎት፣ ከሚሰሩበት ቁስ በአሰራር ሁኔታቸው ላይ እና ማህበረሰቡ ማህበራዊ ፋይዳ አንጻር ተቃኝተው በምዕራፍ አራት ቀርበዋል፡፡

## 2.5 የቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት እና የአተናተን ሂደቶች

በዚህ ክፍል የቁሳዊ ባህል ጥናት ሊያተኩርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችንና ሊከተላቸው የሚገቡ የአጠናን ሂደቶችን አስመልክተው ምሁራን የሰነዘሯቸው ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡

Fleming (1974:156) በየትኛውም መስክ ውስጥ ያለ አጥኚ እንደ ጥናቱ ሁኔታ ቁሳዊ ባህ ልን የጥናቱ ትኩረት ካደረገ በትኩረቱ ሊዘነጋቸው የማይገቡና ለትንተናውም መሰረት ይ

ሆናሉ ያላቸውን 5 የትኩረት ነጥቦች አቅርበዋል፡፡ እነሱም የቁሱን ታሪክ ማጥናት፣ ቁሱ የተሰራበትን ንጥረ ነገር አካባቢያዊ ሁኔታውን ጨምሮ ማጥናት፣ የቁሱን አወቃቀር ከነባለሙያው ማጥናት፣ ምስሉን ማጥናት እና ተግባሩን ማጥናት ናቸው፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991፡127) ማንኛውም በፎክሎር መስክ ተሰማርቶ ጥናት የሚያደርግ ሰው በምን? እንዴት? መቼ? የት? ምንድን? ለምን? ለማን? ከማን? የሚሉትን ጥያቄዎች የትኩረት አቅጣጫው ሊያደርጋቸው እንደሚገባ መክረዋል፡፡ ስለዚህ የFleming ትኩረት ቅጣጫዎች ደግሞ በዝርዝር እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

1. የቁሱን ታሪክ ማጥናት ሲባል ቁሱ የትና መቼ ተሰራ? በማን? ለማን? እና ለምን ተሰራ? በባለቤቱ በሁኔታውና በአገልግሎቱ ላይ የተደረገ ለውጥ አለ? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ምላሽ እንድንፈልግ የሚመክር ነው፡፡
2. ቁሱ የተሰራበትን ነገር ከአካባቢው ጋር ማጥናት፡- ይህ ቁሱ ከምን ከምን ነገሮች ተሰራ በቁሱ መገኘት ላይ ተፈጥሯዊና መልካምድራዊ ሁኔታዎች ለውጥ አሳድረዋል፡፡ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ እንድንፈልግ የሚጠቁም ነው፡፡
3. የቁሱን አወቃቀር፡ ይህ ቁሱ እንዴት ተሰራ? በሚሰራበት ጊዜ የትኞቹ መሳሪያዎች አገልግሎት ሰጡ? የተለያዩ ክፍሎች እንዴት ተገጣጥመው ለአገልግሎት በቁ? ባለሙያው ማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በጥናታችን ወቅት እንዳንዘነጋ የሚያስገነዝብ ነው፡፡
4. የዲዛይን ጥናት፡- ይህ የቁሱ ቅርጽ በተጨማሪ ማስጌጫዎች እና ምስል ላይ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ የሚመክር ነው፡፡
5. የተግባር ጥናት፡- ይህ ቁሱ መጀመሪያ ሲሰራ እንዲሰጣቸው የታሰበው አገልግሎቶች ብቻ ሳይሆኑ ተያይዞ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ጭምር ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥናት በሚደረግበት ወቅት ቁሶቹ ከመለበስ እና ከማስጌጥ በተጨማሪ የተወሰነ ቡድንን መለየት አስተሳሰብን፣ እምነትን፣ ባህርይን፣ መግለጽ እና ተግባቦትን መፍጠር መቻል አለመቻላቸውን ማየት የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥም የቁሱን ታሪክ ማጥናት፣ የቁሱን አወቃቀር እና የተግባር ጥናት የሚሉት በምዕራፍ አራት ገለጻ ላይ ውለዋል፡፡

በተጨማሪም Fleming (1974፣154-161) የመተንተኛ ሂደቶች ያሏቸውን ሀሳቦች አስፍሯል፡፡ እነዚህን ሀሳቦች ለማሳየት የተፈለገውም በጥናቱ የገኙ መረጃዎችን ለመተንተን ያመች ዘንድ ነው፡፡

አንደኛው በትንታኔያችን ወቅት ቀዳሚው ተግባር ገለጻ ሲሆን ቁሱ ምን እንደሆነ በዝርዝር የሚገለጽበት ነው፡፡ ገለጻ ቀላልና ስዕላዊ በሆነ መልኩ የሚቀርብም ነው፡፡ ቁሱን ያላዩ ሰዎች በአዕምሯቸው የቁሱን ምስል እንዲከስቱ ማድረግን ይሻል፡፡ የቁሱ ቅርጽ የተሰራበት ንጥረ ነገር ክብደቱ፣ እርዝመቱ፣ ቀለሙ ወዘተ. መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ ቁሱን ያላዩት እንዲያዩት ለማድረግም ደግሞ እንደ አጥኚው አተያይ የሚወሰን ቢሆንም ብዙዎቹ ግን አገልግሎትን መሰረት ያደርጋሉ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ግምገማ ሲሆን በትንታኔያችን ሂደት ውስጥ የምንፈጽመው ነው፡፡ በገለጻ ሂደት ከምንነቱ ጋር የተዋወቅነውን ቁስ ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ የምንከተለው ነው፡፡ ቁሳዊ ባህሉን በግምገማ መልክ ለመተንተን የምንጠቀምባቸው ሁለት አይነት መንገዶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ቁሱን በመመልከት ከሚሰጥ ስነውበታዊ ብቃት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ትኩረቱም ቁሱ እና አሰራሩ ባለሙያው ክህሎቱና ምርጫው ምስሉና ተገቢነቱ፣ የቅርጹ፣ የስልቱና የጌጥነቱ ማህበረሰባዊ ገላጭነት ላይ ነው፡፡ ሁለተኛው የግምገማ ሂደት ደግሞ አንዱን ቁስ ከተመሳሳዩ ሌላ ቁስ ጋር ከመጠን ፣ከዋጋ፣ እንደ ልብ ከመገኘት እና አለመገኘት አንጻር እያወዳደሩ ተመሳስሎ እና ልዩነታቸውን በማሳዬት ቁሱ ይበልጥ እንዲታወቅ የሚደረግበት ነው፡፡

ሶስተኛው ባህላዊ ትንተና ሲሆን ከማህበረሰቡ ባህል ጋር ያለውን የተዋሀደ ግንኙነት መሰረት በማድረግ የሚተገበር የትንተና ሂደት ነው፡፡ ይህ አይነቱ ትንተና ቁሱን ከጌጥነቱ አንጻር የሚቃኝ ሳይሆን ከተምሳሌታዊ ተግባሩ አንጻር የሚያጤን ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ቁሱ ከብር የሚሰራ፣ ክብደቱ 20 ግራም ቅርጹ አራት ማዕዘን እና ከድንቡልቡል የፕላስቲክ ውጤት ጋር ተሰካክቶ በአንገት ላይ የሚደረግ ቢሆን ቁሱ ለምን ከብር ብቻ ሊሰራ እንደቻለ፣ የሚሰካኩትን ቁሶች ማህበረሰቡ በቁጥር የወሰናቸው መሆን አለመሆኑን ቁሱ ከጌጥነት በተጨማሪ ሰላለው አገልገሎት ወዘተ. ጠይቆ ትንተና ማድረግ በእነዚህ የትንተና ሂደት የሚከወን ነው፡፡ በገለጻና በግምገማ የትንተናው ሂ ደት የተገለጸው ቁስ የያዘው መልክ፣ ቅርጽ፣ የተሰራበት ጥሬ ዕቃ ፣ ክብደቱ፣ እርዝመቱ፣ ቀለሙ ወዘተ. በማወቅ በዚህ መልኩ ብቻ ሊሆን እንደቻለ ጠይቆ መረዳት እና ፋይዳውን መተንተን በዚህ ሂደት የሚካተት ነው፡፡

በመጨረሻም የግኝት ትንተና ነው። ይህ በሶስቱ ሂደቶች የተተነተኑትን የተጠኝ ቁሱ መረጃዎች በመያዝ እና አጠቃላይ ከሆነው የአጥኚው እውቀት ላይ የሚመሰረት ነው። አጥኚው ስለ ቁሱ በቂ መረጃ ስለሚኖረው ቁሱ ከሚገኝበት አካባቢ ወይም ከቁሱ እርቆ ትንተናውን ሊያደርግ ይችላል።

በቁሳዊ ባህል ጥናት አንድ ተመራማሪ ሊከተላቸው የሚገቡ ጉዳዮች የመኖራውን ያህል በጥናቱ ሂደት ሳይገነዘባቸው ቀርቶ ግኝቱን የተሳሳተና ጎደሎ የሚያደርጉበት ሁኔታዎች በመኖራቸው ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባም Schlereth (1985:27-31) ይመክራሉ።

## 3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ገጽታ እና የማህበረሰቡ ዳራዊ መግለጫ

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ በአጭሩ ይገለጻል፡፡ ስለ መልክዓምድራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበረ ባህላዊ ሁኔታዎችም በጥቂቱ ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.1 የአዊ ብሔረሰብ ገፅታ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከታቀፉት አስር ዞኖች ሶስቱ የብሔረሰብ ዞን ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ የአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር አንዱ ነው፡፡ አዊ ብሔረሰብ አስተዳደር የተመሰረተው ሚያዚያ 1986 ዓ.ም ነው፡፡ የአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር 1ሚሊዮን 78 ሺ 235 የሚጠጋ ህዝብ የሚኖርበት፣ 837 ሺ 886 ሄክታር የቆዳ ስፋት 75 ፐርሰንት ወይና ደጋ 25 ፐርሰንት ደጋና ቆላ የአየር ንብረት ባለቤት ነው፡፡ ብሔረሰቡ በ8 የገጠር ወረዳዎች እና በ3 የከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ነው፡፡ የብሔረሰቡ ርዕሰ ከተማ እንጅባራ ከአዲስ አበባ በ435 ኪ/ሜ ከክልሉ ርዕስ ከተማ ባህርዳር ደግሞ 120 ኪ/ሜ ይርቃል፡፡

የአዊ ባህል ፌስቲቫል በጥር 11/2004 ዓ.ም የተዘጋጀው መጽሄት እንደሚገልጸው በብሔረሰቡ ከአዊኛ በተጨማሪ አማርኛ በስፋት ጉምዝኛና ሽናሽኛ በጥቂቱ የሚነገርበት ነው፡፡ አዊ የበርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስህብ ሀብቶች ባለቤት ነው፡፡ የዘንገና፣ የጥርባ ሀይቅ፣ የትስኪ፣ የደንዳር፣ የረፋንግና የፋርቆ ፏፏቴ፣ የዳንጉላ ዋሻና የወለተ ጴጥሮስ ገዳምን መጥቀስ ይቻላል (ገጽ 4፡2004 ዓ.ም)፡፡

### 3.2 የባንጃ ወረዳ ገጽታ

የባንጃ ወረዳ በአዊ ዞን ውስጥ ይገኛል፡፡ በወረዳው ውስጥ ሰፍሮ የሚገኘው ህዝብ በአብዛኛው የአዊ ብሔረሰብ ሲሆን አልፎ አልፎ የአማራ ብሄር ይኖርበታል፡፡ የባንጃ ወረዳ በሰሜን፣ የፋግታ ለኮማ ወረዳ በደቡብ የጓጉሳ ሽኩዳድ ወረዳ፣ በምዕራብ የጓንጓ አንከሻ ወረዳዎች በምስራቅ የፋግታ ለኮማና የሰከላ ወረዳዎች ያዋስኑታል፡፡ አጠቃላይ የወረዳው የቆዳ ስፋት 45618 ሜትር ይሆናል፡፡

ወረዳው በውስጡ 26 ቀበሌዎች አሉት፡፡ የባንጃ ወረዳ ለተለያየ ጥቅም የሚውሉ ፏፏቴዎች ወንዞችና፣ ሀይቆች አሉት፡፡ ከእነሱም ውስጥ ቡችከሲ፣ ባሪና ዚንጊኒና የመሳሰሉ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የወረዳው እና የዞኑ ትልቁ የዘንገና ሀይቅም በዚህ ወረዳ ይገኛል፡፡ የተለያዩ አዕዋፍት፣

ዋሻዎች፣ መካነ መቃብሮች፣ ተራሮች የድንጋይ ካብ እና ታሪካዊ ስፍራዎች በወረዳው ይገኛሉ፡፡

እንደ አቶ አዲሱ መንገሻ እና እንደ አባ እንዳላማው አማረ ገለጻ፡-

*በባንጃ ወረዳዎች ከሚታወቁ ባህላዊ እሴቶች መካከል «አለም የፈረሰኞች ማህበር» አንዱና ዋናው ነው፡፡ አመጋገባቸውም የባንጃ ህዝብ በአብዛኛው ለክብር እንግዳ መጣጣ በእንጀራ እና የነጠረ ቅቤ ጉዝጉዝ፣ አብዚ ለማዕድ ይቀርባሉ፡፡ ድንች በእንጀራ ማባያው ተልባ እና ጭብጦ የሚዘወተሩ የባህል ምግቦችም ናቸው፡፡ በዚህ ወቅትም ጠላ ማወራረጃ የባህል መጠጥ ነው፡፡ ሲበላም ተዋረዳዊ በሆነ መልኩ ሲጀመር አባወራ በረከት ለሁሉም በማድረስ ነው፡፡ (በቃለ መጠይቅ ጥር 13/2004ዓ.ም)*

## 3.3 መልክዓምድራዊ አቀማመጥና የአየር ንብረት ሁኔታ

የወረዳው መልክዓምድራዊ አቀማመጥ በአብዛኛው ሜዳማ ሲሆን የተወሰነው ቦታ ደግሞ ተራራማና ሸለቋማ ነው፡፡ በዞኑ ብዙ ምንጮች ወንዞችና ሀይቆች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዳራ፣ አዮ፣ ፈጣም፣ ግዛኒ፣ አርዲና፣ የመሳሰሉ ትላልቅ ወንዞችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ትስኪ፣ ፋንዳ፣ ጋርኛ፣ ዳንዳር፣ ኳሻኒ፣ ልብሲ ቢምብላ የተባሉ ማራኪ ፏፏቴዎች አሉ፡፡ ዘንገና እና ጥርባ ሀይቆችም አሉ፡፡ በወረዳው የሚገኘው ከፍተኛ ቦታ የአሰም ተራራ ነው፡፡ የከፍታው መጠን 2700 ሜትር ዝቅተኛው ቦታ ደግሞ ዙፋሪ አብስክተም ሲሆን የከፍታው መጠን ደግሞ 1900 ሜትር ይደርሳል፡፡

የዞኑ አብዛኛው ክፍል ደጋማ ሲሆን አነስተኛው ክፍል ደግሞ ወይና ደጋ ነው፡፡ የደጋማው ክፍል በአብዛኛው ዝናባማ ስለሆነ የአየር ንብረቱ ቀዝቃዛ በመሆኑ በአመት የሚገኘው የዝናብ መጠን 2206 ሚሊ ሜትር ነው፡፡ አማካይ የሙቀት መጠን 19 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እንደሚደርስ ከወረዳው እስታስቲክስ ክፍል የወጣው በራሪ ወረቀት ያመለክታል፡፡ (ህዳር 7/2004 ዓ.ም)

## 3.4 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

የአዊ ብሄረሰብ እንደ ሌላው የሀገራችን ህዝቦች በበሬ ከማረስ በተጨማሪ በፈረስና ፈረስን አቀናጅቶ የማረስ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ በአንድ ፈረስ የማረስ ልማድ አላቸው፡፡ ዞኑ ለእርሻ የሚሆን ለምና ሰፊ መሬት አለው፡፡ አርሶ አደሩ ጥራጥሬ እህሎችን እና ፍራፍሬዎችን ያለማል፡፡

በመንገድ እና በከተማዎች ውስጥ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ባህላዊ የቱሪስት የስጦታ እቃዎች በሸመና፣ በቅርቀሀ፣ በቆዳ፣ በጭራ በዋንጫና በጥልፍ ውጤቶች እያመረቱ ይሸጣሉ፡፡ በአጠቃላይ የብሄረሰቡ ዋና መተዳደሪያና የገቢ ምንጭ ግብርና ሲሆን አልፎ አልፎም የንግድ እንቅስቃሴ ይታያል፡፡

በወረዳው የደጋማውና የወይና ደጋው ክፍል ጤፍ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ድንች፣ ኑግ፣ ዳጉሳ፣ ባቄላ፣ አተር፣ የአገው ድንች፣ ተልባን በቆሎ የመሳሰሉት ለምግብ ፍጆታና ለገበያ ያመረታሉ፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪም የወረዳው ህዝብ የቀንድ ከብት፣ የጋማ ከብት፣ በግና ፍየል በማርባት ኑሮዋቸውን እንደሚገፉ በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት በተዘጋጀው አዱክ የተሰኘው መጽሄት ይገልጻል፡፡ (ቁ፡1፣6፣2002)

## 3.5 የወረዳው ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታ

ባንጃ ወረዳ በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ቢኖሩትም በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ስር ግን ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ብቻ አነሳለሁ፡፡ እነሱም የጋብቻ ስነስርዓት እና የለቅሶ ስነስርዓት ናቸው፡፡ ምክንያቱም በጋብቻ ጊዜ የሚለብሱ ልብሶች እና ጌጣጌጦች በመኖራቸው እንዲሁም በለቅሶ ጊዜ ልዩ ልብሶች ስለሚለበሱ ነው፡፡

### 3.5.1 ሀገረሰባዊ ጋብቻ

በወረዳው ጋብቻ የሚወሰነው በተጋቢዎቹ ወላጆች ምርጫ እና ፈቃድ ነው፡፡ በልማዱ መሰረት የጋብቻ ጥያቄ የሚቀርበው በወንድ ልጅ አባት ወይም በቤተሰብ በኩል ነው፡፡ የወንድ ልጅ ቤተሰብ ልጁ ‹‹ለአቅመ አዳም ደርሷል››፣ ‹‹ጎጆ ለመውጣት በቅቷል›› ብለው ሲገምቱ እና የእገሌ ልጅ ቆማ ቀረች ከሚል ሀሜት ለመሸሽ ሲሉ ‹‹ልጅህን ለልጄ›› ብለው ቃል ኪዳን በመግባት በብሄረሰቡ በተጋቢዎቹ የልጅ እድሜ ጋብቻ መመስረት የተለመደ ነው፡፡

ጋብቻው በተጋቢዎቹ እቻነት ላይ የተመሰረተ ነው። የእቻነት መገለጫዎቹ ደግሞ ሙያና ሀይማኖት ናቸው። ለምሳሌ፡- አርሶ አደር ልጁን ለአርሶ አደር ወይም ከራሱ ሙያ ጋር ተመሳሳይ ሙያ ላለው ቤተሰብ ይድራል። የአርሶ አደር ልጅ  በእደ ጥበብ ሙያተኛ ለተሰማሩት ቤተሰቦች አትዳርም። ሁሉም ሙያተኛ በየሙያው መጋባት እንዳለበት ይታመናል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሽመና፣ በአንጥረኝነት፣ በሸክላ ስራ እንዲሁም በቆዳ ስራ የተሰማሩ ቤተሰቦችም ከሌሎች ሙያተኞች ጋር መጋባት አይፈልጉም። (የቡድን ውይይት የካቲት 4 ቀን ፣2004ዓ.ም)

> አቶ ቢተው ወንዳገኘው ሲገልጹ፡- *የወንድ ልጅ ቤተሰብ ለልጃቸው ሚስት የምትሆን ሰባት ጉልበት[2] ቆጥረው ሚስት የምትሆን ልጃገረድ ያፈላልጋል። ፈልገው ካገኙ በአ ካባቢው አሉየተባሉትን  ሽማግሌዎችን በመላክ  ያስጠይቃል።የልጅቷ ቤተሰቦች (አባት) ‹‹ምን ፈልጋችሁ መጣችሁ የአገር ሽማግሌዎች ባካችሁ ቁጭ በሉ›› ይላል። የመጡ ሽማግሌዎችም የለም የመጣንበት ጉዳይ ቁመን መናገር ስላለብን እንናገር "ልጃችሁን ለልጃችን ብለን መጠናልና"እሽታችሁን ሳንቀበ አንቀመጥም በማለት ክር ክር ይገጥማሉ። (ጥር 17/2004ዓ.ም)*

የልጅቷ አባትም ሽማግሌዎችን በማክበር ፊንታ እንዲቀመጡ በመሀላ ቃል ያስገባቸዋል። ሰዎችም ይቀመጡና መቼ እንደምንመጣ  ይንገሩን  በማለት ያጣድፏቸዋል። የልጅቷ አባትም ከሚስቴ ጋር ተማክሬ በማለት ከ1-3 ወር ባለ ጊዜ ይቀጥራቸዋል። የሴቷ ቤተሰቦምችም ሽማግሌዎችን ከሸኙዋቸው በኋላ የቅርብ ዘመዶቻቸውን ሰብስበው በጉዳዩ ይማከራሉ። በዘር፣ በባህሪ፣ በንብረት፣ የሚስማማቸው ከሆነ በቀጠሮው እለት የእሽታ መልስ ያቆያሉ።

በእርግጥ የወንድ ቤተሰቦች ከመጀመሪያው ሽማግሌ የሚልከው የሴቷ ቤተሰቦችን አቋም አጥርቶና በእቻነታቸው ላይ የጎላ ልዩነት አለመኖሩን አረጋግጦ ስለሆነ በአብዛኛው ጊዜ ጥያቄው የሚያልቀው በእሽታ ነው። (ቢተው ወንዳገኝሁ፣ ቃለ መጠይቅ፣ጥር 17፣2004)

ከወረዳዋ ቀበሌ ነዋሪዎች ባገኘሁት መረጃ ሁለቱ ወገኖች ለልጆቻቸው ለወደፊት ኑሮዋቸው መቋቋሚያ ሀብት የሚሆናቸውን ከብቶች ይወስናሉ። በእለቱም የማጫ[3] ቀብድ ይከፍላሉ። በሴቷ

---

[2] ከአያት ቅድመ አያት ጀምሮ  እስከ ልጅልጅ ድረስ ሰባት ጊዜ የሚደረግ የዘር ሀረግ ቆጠራ ነው።
[3] ማጫ ማለት በአካባቢው ቋንቋ ጥሎሽ  ማለት ሲሆን ለልጅቷ ከሚሰጡ ከብቶች ተጨማሪ የሚሰጥ የገንዘብ ነው።

ወገን በግ ወይም ፍየል ታርዶ በቀጠሮው የተሳተፉትን ሽማግሌዎች በሙሉ ይጋብዟቸዋል። የወንዱ ወገን በሴቷ ወገን በቀጠሮ[4] የተያዙትን ከብቶች ከራሱ ጋር አደባልቆ ወደ ቀየው ይወስዳቸዋል። እነዚህ ከብቶች የተዳሪዎቹ የወደፊት መተዳደሪያ አንጡራ[5] ንብረቶች ናቸው። ከሴቷ ወገን አንድ ሰው ለሙሽራዋ የሚያስፈልገውን ማንኛውም ድግስ መቻል አቅልቋይ መያዝ አንድ ጋን ጠላና የታወቀ መጠን ያለው እንጀራ ማቅረብ የተለመዱ ናቸው።

ሰርጉ ሶስት ክፍሎች አሉት። እነሱም፡- ዋዜማ፣ አይነታ እና ምላሽ ናቸው። የዋዜማው እለት በሁለቱም ወገን ቤት ወዳጅ ዘመድና የሰፈር ሰው "መጥታችሁ ልጃችንን መርቁ ተብላችኋል" እየተባለ ይጠራል። የተጠራው ህዝብ አመሻሽ በሰርጉ ቤት ይሰበሰባል። ተበልቶ ተጠጥቶ ከተመረቀ በኋላ የሙሽራ እናት በነጭ ሻሽ ዋንጫ ይዛ "እንሶስላዬ›› በማለት እየነቀነቀች የተጋበዘው ልጅ አዋቂ ሳይቀር ተነስቶ ያጅባታል። ይህ እንሶስላዬ የሚያመለክተው ሙሽራዋ በሰርጉ ዋዜማ እንሶስላ መሞቋን ነው።

እንዲሁም የስር ሚዜ የሚመርጠው ሙሽራው ወይም ሙሽራዋ ናት። ወደ ሙሽራዋ ቤት ከመሄዳቸው በፊት የስር ሚዜው ሙሽራውን አለባብሶ አባትና እናት ቁጭ ባሉበት ከሽማግሌዎች ፊት አቅርቦ ያስመርቃል።

ከምርቃቱ በኋላ ሙሽራው የአባትና የእናት ሽማግሌዎችን ጉልበት እንዲስም ይደረጋል። ሙሽራውም ከሚዜው ትክሻ ላይ ታዝሎ ፅዋ ሙሉ ድፍድፍ በእጁ ይዞ ሌሎች አጃቢዎች አጅበውት ከቤት ያውጡትና እደጅ በቆመው ሙቀጫ ሶስት ጊዜ ካዞሩ በኋላ የያዘውን ፅዋ ከእነድፍድፉ ወደ ምስራቅ[6] ዞሮ ድፍድፉን በያዘው ዱላ ይቀጠቅጠዋል። የፅዋውና የሙቀጫው ተምሳሌት በሄደበት ክፉ አደጋ ወይም ጠላት ቢያጋጥመው ድል ነስቶ እንዲመለስ ለመግለጽ ነው። በተጨማሪም የሙሽራዋን ክብረ ንፅህና የመስበር አቅሙን ለማረጋገጥ ተብሎ ነው።

ከዛም በተዘጋጀው በቅሎ ወይም ፈረስ ጉዞ ወደ ሙሽራዋ ቤት ይሆናል። ሰርጉ ቤት አካባቢ እንደደረሱ መታየት በሚችሉበት ግልፅ ቦታ ላይ ይሰፍራሉ። ከዚያም ሚዜዎቹ አንድ አሳዳሪ[7]

---

4 ለሙሽሮች በውል ስምምነት የሚያዝ ቋሚ ንብረት

5 ቋሚ ለማለት ነው።

6 ወደ ጽሀይ መውጫ በመዞሩ ኑሮው እንደ ጽሀይ ያበራል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

6 አስተናጋጅ ለማለት ነው፡፤

ይመርጣሉ፡፡ ከሴቷ ወገንም አንድ አሳዳሪ ይመረጣል፡፡ ሁለቱም የወንድና የሴት አሳዳሪዎች ለብቻቸው በመመካከር ከተስማሙ በኋላ የወንድ ወገን አሳዳሪ አጅበው የያዙትን በትር (ዱላ) ተቀብሎ ለሴቷ ወገን አሳዳሪ ይሰጣል፡፡ የሴቷ ወገን አሳደሪም በቅሎ (ፈረስ) ከነኮርቻው ጭምር ይረከባል፡፡ የተረከባቸውን ንብረቶች አንድም ንብረት ከጠፋ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ከባንጃ ዙሪያ ወረዳ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው እና እኔም እንደተመለከትኩት የወንድ ሙሽራ ሙሽራዋን ለመረከብ ሲመጣ በባህሉ መሰረት አልብሶና አስጊጦ የሚወስድበትን ልብስና ጌጣጌጥ አቅርቦ ነው፡፡

እነዚህም ውስጥ ሱሪ፣ ቀሚስ ፣ ካባ፣ ሻሽ ናቸው፡፡ የሴት ወገን አሳድሪም የሙሽራዋን ልብሶችና ቁሳቁሶች ማለትም ቀሚስ፣ ነጠላ፣ ኩታ፣ቁኒ ቅል፣ ሙዳይ ጀንዲ ትራስ ለስር ሚዜው ያስረክባል፡፡ የሙሽራው ልብሶችና ቁሳቁሶች እርክክብ ካለቀ በኃላ ሶስቱ ሚዜዎች በሽማግሌዎች ፊት እንዲጨፍሩ ይደረጋል፡፡ ድግሱ ተበልቶ ተጠጥቶ ምርቃን ከተደረገ በኃላ ሙሽራዋ በእናቷ ወንድም ወይም በቅርብ ዘመዷ ታዝላ ስትወጣ የወንድ ሙሽራ ሚዜው ይረከባታል፡፡ ሙሽራዋ ታዝላ እንደ ወጣች ጀምሮ የሴት ወገን ይጨፍራሉ፡፡ ሙሽራዋ በበቅሎ ላይ እንደወጣች በሴት ወገን ያለው ወጣት በጉሲት እና በድንጋይ እየተወራወሩ አጃቢዎችን በመምታት የተለመደ ነውና በሴት በኩል የቤት ሽማግሌዎች በተለይም የሙሽራዋ የቅርብ ዘመዶች አባት፣ ወንድም፣ አጎት አጥብቀው ይከላከላሉ፡፡

የወንድ አጃቢዎች ሙሽራዋን ከበቅሎ እንዳወጧት እየጨፈሩ ከሚወረወርባቸው ጉሲት[8] እና ድንጋይ በተቻለ መጠን እያመለጡ በፍጥነት ይሄዳሉ፡፡ የሴቱ ወገን ህፃን ተሸክሞ ይመለሳል፡፡ ምክንያቱም የሄደችዋ ሙሽራ ወልዳ እንድትመለስ ለማመልከት ነው፡፡ ሙሽራው ቤት ከደረሱ መድረሳቸውን ለማመልከት ጥሩንባ እየነፉና እየጨፈሩ የወንድ አባትና እናትም በር ላይ በመሆን እልልታው ይቀልጣል፡፡

ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሳይገቡ በላይ ሆነው ሙሽራዋ በሚዜ ታዝላ ምርቃን ይደረጋል፡፡ ሙሽራው በጎን ሆኖ ይህንን ምርቃን የሚያደርጉ ሽማግሌዎች እርጥብ ሳር በሁለት እጃቸው ይዘው በዋንጫ ተሞልቶ በተያዘ ጠላ አንድ ምርቃን በመረቁ ቁጥር እየነከሩ በማውጣት ይካሄዳል፡፡ የስር ሚዜው ሙሽራው የሙሽሪትን ክብረ ንፅህና እንዲወስድ ይነግረዋል፡፡ እኩለ ሌሊት ላይ

[8] እርሻ ቦታ ላይ የሚገኝ ትልቅ የተድቦለቦለ አፈር

ሲጨፍሩ በድንገት ጩኸት ይሰማል። ጩኸቱን የሰሙት የስር ሚዜዎች ወደ ሚጨፍሩ ሰዎች ይመጡና "ብር አምባር ሰበረልዎ ጀግናው ልጅዎ›› እየተባለ ይዘፍናሉ።

ሰርጉ በወንዱ ቤተሰቦች ድሮ ድሮ ለ1 ወር አሁን ለ 7 ወይም ለ3 ቀን ከቆዩ በኋላ መልስ እንደሚጠሩ የወረዳው ቀበሌ ነዋሪዎች ገልጸዋል። (የቡድን ውይይት ጥር 20ቀን፣ በቸውሳ ቀበሌ፣ 2004 ዓ.ም)

### 3.5.2 የለቅሶ ሥነስርዓት

በመስክ ስራዬ ወቅት እንደተመለከትኩት እና በቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው አዛውንቶች መረዳት እንደቻልኩት አንድ ሰው ሲሞት ዘመድ አዝማድ ጎረቤትና ቤተሰብ ተሰባስበው ለሞቱ ማብሰሪያ ይጮሀሉ። እንዲሁም ጥይት ይተኩሳሉ።

ዘመድ አዝማድ እንደ ዝምድና መጠናቸው ከቤት ወይም ከመንገድ ጀምሮ እየተጯጯሁ ወደ ሟች ቤት ይሄዳሉ። የፊት መንጨት እና የዋዋጃይ ስርዓትም ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት በቀብር እለት ይፈጸማል። እሬሳው መከፈን ሲጀምርም የዋዋጃይና እለቅሶ ስርዓቱ ይጀመራል። ሌሊቱን በመልእክተኛ መልዕክት የደረሰው ዘመድ አዝማድ ከቅርብና ከሩቅ በመምጣት ይሰበሰባሉ። ሟች እቤት ያደሩ ሰዎች አጥቢያ ላይ የመጡትን በለቅሶ ይቀበሉዋቸዋል።

ሲነጋም ሁሉም ተሰብስበው ማልቀስ ሲጀመር በለበሱት ጋቢና ነጠላ በእጃቸው መዳፍ ጨምድደው በመያዝ ወንድ ግንባሩን ሴቷ ደግሞ የፊቷን ጎንና ጎን ጉንጮቿን ይፈትጋሉ ወይም ይነጫሉ።

ለሊት መልዕክት ደርሶት የመጣውን ህዝብ እና ሟች ቤት ያደሩት ሀዘንተኞች በቀጥታ እንደተያዩ ተቃቅፈው አያለቅሱም። አንደ ብዛታቸው መጠን በቅርብ እርቀት እስከ አራትና አስር ሜትር ተራርቀው ይቆማሉ። ከዛም ሴቶች ተሰብስበው ከወንዶች በፊት ይገቡና ወንዶችን ከበስተኋላ አሳልፈው ተቃቅፈው ያለቅሳሉ።

‹‹ዋዋጃይ›› ማለት መጨረሻው የታወቀለትን ሰው መሞቱንና ሂዶ መቅረቱን ለማመልከት "ወይኔ ሂዶ ቀረብኝ" ማለት ነው። የወንዱ ቡድን የራሱ ዜማና ቅላፄ በተሞላበት መልኩ በመቀባበል ሀዘናቸውን ይገልፃሉ። ከሩቅ ቦታ ሌሊቱን በሙሉ በመጓዝ ለለቅሶው የደረሱት ሰዎች ዋ.ዋ.ዋ.ዋ. ጃይ...... ወይ....ወይ በማለት በእጅጉ ውስጣቸው ማዘኑን በእንጉርጉሮ ሲገልጹ ሟች ቤት ያደሩት ሰዎችም ዋ......ዋ.....ጃይ... ይላሉ።

መረጃ አቀባዮቹ እንደገለጹልኝ ዋዋጃይ የራሱ የሆነ ዜማና የአለቃቀስ ስርአት፣ እንዲሁም የራሱ የሆነ አረማመድና ትርጉም ያለው በመሆኑ በዘፈቀደ ገብተው ሲያለቅሱት የማይችሉት የግል የሆነ ሲወርድ ሲዋረድ የተወረሰ ባህል እንደሆነ ነው፡፡

ተራርቀው የተሰለፉ ሀዘንተኞች ስልፉን ይተውና አንገት ለአንገት ተቃቅፈው ካለቀሱ በኋላ ከተመሳሳይ ቦታ ወደ ተቃራኒ ቦታ በመሆን ሴቶች ወደ ወንዶች እንዲሁም ወንዶች ወደ ሴቶች በመሄድ ይላቀሳሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ጉዳይ ወ/ሮ ብርቱካን አካሉ ሲገልጹት *‹‹አሁን ነገሩ ሁሉ ተቀይሯል፡፡ ባህሎቻችን በብዛት ተደባልቀውና በአማራ ባህል ተለውጠው የጥንት ባህላችንና ልምዳችን ተቀይሯዋል፡፡ እንዲህ አለ፣ እንዲህ ሆነ፣ እየተባለ ሲናናቅ ባህላችን እየተመናመነ ሂዷል››* በማለት ገልጸዋል፡፡ (*ቃለ መጠይቅ መጋቢት* 10/2004 *ዓ.ም*)

የተከፈነውንና ፍታት የተደረገለትን አስክሬን ከቤት እስከ ቤተክርስቲያን እስከ ሚደርስ ሶስት ጊዜ መሬት መንካትና ማረፍ አለበት፡፡ እንዲሁ በየመንገዱ ሲጓዝ ዛፍ ስር ሶስት ጊዜ የጉዞ ፍታት ይደረጋል፡፡ ወደ ቀብር በሚሄድበት ሰዓትም በመንገድ በሚያገኙዋቸው ዛፎች ላይ ለ20 ደቂቃ ያክል እረፍት ያደርጋሉ፡፡ የመጨረሻው እረፍትም ከቤተክርስቲያን ክልል ውጭ ፊት ለፊት ድንኳን ይጣል እና እዛው ይካሄዳል፡፡ ዋንጫ፣ ብርሌ፣ የቆዳ ስጋጃ፣ ሞሰብ፣ የአጓዛ እና የሰሌል ምንጣፍ ከድንኳኑ ስር ይደረደራሉ፡፡ ይህ ይደረግ የነበረው በድሮ ጊዜ ለጌጥ እንጂ ለስራ እንዲውሉ አልነበረውም፡፡ አሁን ግን ለአገልግሎት ይውሉበታል፡፡ (የቡድን ውይይት የካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም)

ከድንኳኑ ፊት ለፊት በእንስራ አፍ ላይ ጀበና ተደፍቶ ከወንበር ይቀመጥና በልብስ ተከናንቦ እና ባርኔጣ ተጥሎበት ሰው መስሎ ይቀመጣል፡፡ ይኼም የሚደረገው ሟችን በህይወት ዘመን እንዳለ ለማስታወስና ለማስለቀሻነት ያመቻቸው ዘንድ ነው፡፡ ይህ ነገር ታዲያ በካህናት እና በሀይማኖት አባቶች ከፍተኛ ውግዘት በመድረሱ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ (አዱክ የወ/ባ/ቱ/ጽ/ቤት ቁ 2፡5፡2003) ሀዘንተኞች ሟችን ቀብረው ሲመለሱ ማህበርተኞች፣ እድርተኞች፣ ጎረቤቶች እና ሌሎች ሰዎች ንፍሮ፣ ቆሎ፣ ጠላ፣ እንጀራ እና መሰል ነገሮችን አዘጋጅተው ይጠብቋቸዋል፡፡ በዚህ ወቅትም ሀዘንተኞች እረፍት ወስደው እህል ውሀ እንዲቀምሱም ይደረጋል፡፡

# 4. የአዊ ብሄረሰብ አለባበስና አጊያጊያጥ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሴቶች እና ወንዶች ወጣቶች ከማግባታቸው በፊት እና ካገቡ በኂላም ምን ምን እንደሚለብሱ፤ በምን እንደሚያጌጡ ወይም በምን በምን አይነት ጌጣጌጦች እንደሚዋቡ ቁሶቹም ከምን ከምን እንደሚሰሩ፤ እንዲሁም እናቶችና አባቶችም በተመሳሳይ ምን ምን ልብሶችን እንደሚለብሱና እንደሚዋቡ ቁሶቹም ከምን ከምን እንደሚሰሩ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በተጨማሪም የልብሶቹና የጌጣጌጦቹ ሰራተኞች በምን አይነት የኑሮ ደረጃ ላይ እንደሚገኙና የአካባቢው ማህበረሰብ በእነሱ ላይ ያለው አመለካከት ምን እንደሚመስል ይገለጻል፡፡ በዚህ ገለጻና ትንተና ውስጥም ልብሶቹን እና ጌጣጌጦቹን በተመለከተ የሰማኂቸው ቃላዊ ግጥሞች ተካተዋል፡፡

## 4.1 ሀገረሰባዊ አለባበስ

በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ የሚገኙ ማህበረሰቦች በአብዛኛው ከጥጥ ድርና ማግ ፈትለው በማሰራት ይለብሳሉ፡፡ የተሰራውን ሸማ ወንዶች እጀ ጠባብ ሱሪ፣ ወንጨሬ ወይም ተነፋነፍ፣ ጋቢ እና ኩታ አድርገው ሲለብሱ ሴቶች ደግሞ ቀሚስ፣ ነጠላ፣ መቀነት፣ ሻሽ ይጠቀማሉ፡፡ እንዲሁም ሁለቱም ጾታዎች የፋብሪካ ውጤት የሆነውን ካሽሚር እና ካኪም ይለብሳሉ፡፡

### 4.1.1 የሴቶች ሀገረሰባዊ ልብሶች

በአብዛኛው ህጻን፣ ወጣትና እናት ሴቶች የሚለብሱት ሽብሽቦ ሲሆን በተለይ ወጣቶች ያዘወትሩታል፡፡ እንዲሁም ጉንፍ፣ ሽብሽብ ቀሚስ፣ነጠላ፣መቀነት፣ሻሽ ፣ጎዶ ቀሚስ የሚባሉ ልብሶች አሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ልብሶቹ በዝርዝር ይገለጻሉ፡፡

- ሽብሽቦ፡-

ይህ በአካባቢው አጠራር ሽብሽብ ቀሚስም በመባል ይታወቃል፡፡ ይህን የሚለብሱት ወጣቶች በአማካይ ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ናቸው፡፡

ወ/ሮ ደጅይጥኑ ምናለ እንደገለጹት

> *ሽብሽቦ ያላገባችም ሆነ ያገባችዋ ትለብሳለች፡፡ እናም አሰራሩ ራሱ ቅድም ለየት ያለ ነው፡፡ በመኪና ሲሰፋ ክሽክሽ ወይም ጣውላ ስፍ አድርጋ እንዲያሁና የወጣች እንደሆነ*

*ያምርባታል፡፡ ያገባችዋ ከደረቷ ላይ ቁልፍ ትደረድርበታለች፡፡ ያላገባችዋ ግን የለም፡፡ (ቃለ መጠይቅ፡ የካቲት 25 ቀን 2004 ዓ.ም)*

በዚህ ሀሳብ መሰረት ያገባችዋ የተለያየ ቀለም ያላቸውን የልብስ ቁልፎች በመርፌ በመትከል በአንገቷ ዙሪያ ትደረድራቸዋለች፡፡ በዚህም ልብስ በደረቷ ዙሪያ ቁልፍ ካለው ያገባች መሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታወቃል፡፡ ጋብቻ የምትፈጽመዋ ሴት ግን በእናት እና በአባቷ ፈቃድ ስለሆነ እድሜዋ ለአቅመ ሄዋን የደረሰችም ሆነ ያልደረሰች ልትሆን ትችላለች፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት ግን በአብዛኛው ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ሴቶች ጋብቻ ይፈጽማሉ፡፡ ይህንም በአካባቢው በነበረኝ ቆይታ በገበያ እለት ላይ ሲገበያዩ እንደተመለከትኩት እድሜያቸው በአማካይ ከ7 እስከ 16 ያሉት በደረታቸው ላይ ቁልፍ ደርድረዋል፡፡ የቁልፎች ቀለምም የተለያየ ነው፡፡ ምክንያቱም ሙሽራዋ በሙሽርነት ጊዜዋ ብዙ ታዳሚዎች እንዳዩዋት ለማመልከት ነው፡፡ ይህን ወ/ሮ ሻሽቱ በዜ እንደሚከተለው ገለጸውታል፡፡

*ሙሽሪት ተሸፋፍና ሰው እንዳያያት ትደበቃለች የዚያን ጊዜ የቁልፍ እየሰጠን እናያታ ለን ማለት ነው፡፡ ሙሽራዋም የተሰጣትን ቁልፍ በማጠራቀም ከደረቷ ዙሪያ ባለው ልብስ ትተክለዋለች፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙ ቁልፎችን ካደረገች ብዙ አይታ ነበራት ማለት ነው እንላለን፡፡ ትንሽ ቁልፎች ብቻ ከሆኑ ግን ብዙ ሰው ትኩረት አልሰጣትም ነበር እንላለን፡፡ (ቃለ መጠይቅ ጥር 16 /2004 ዓ.ም)*

ስለዚህ ለአንዲት ሙሽራ ብዙ ቁልፍ ከታዳሚ በተሰጣት ቁጥር የተለያየ አይነት ቀለሞች ያሏቸው ቁልፎች ይደርሷታል ማለት ነው፡፡ በዚህም የቁልፎቹ ቀለሞች እጅግ ይበዛሉ ማለት ነው፡፡ የቁልፎቹ ቀለም የሚወክሉት ነገር እንደሌለም ይህንን ሀሳብ በማጠናቀር የአካባቢው ማህበረሰብ (ጥር 12 /2004 ዓ.ም) በተደረገው የቡድን ታውቋል፡፡

አንዲት ሴት ይህን የምትለብሰው ካገባች በኋላ ነው፡፡ ጉንፍ እና ጎዶ ቀሚስ ሁለቱም የሸማ ውጤቶች ሲሆኑ ልዩነታቸው ጉንፍ በላስቲክ (ጎማ) ተይዞ መሰፋቱ ነው፡፡ ጎዶው ቀሚስ ልቅ ሆኖ የሚሰፋ ሲሆን በመቀነት ከወገብ ይያዛል፡፡ ጉንፉ ግን ከወገብ በጎማ ነው የሚያዘው፡፡ ይህንን ሁኔታ ወ/ሮ አቡኔ ተፈራ ሲያስረዱ

> *ጎዶ ማለት ጥለት የሌለው ሆኖ እኛ እናቶች ነን ምንለብሰው፡፡ ጉንፉ ግን ከኛ አነስ ብላ ገና ያገባች ሰሞን ወጣት እንዳለች ትለብሰዋለች፡፡ ቢሆንም ግን ጉንፍ በአብዛኛው ዛሬ ዛሬ ያላገባው ወጣቱ ሁሉ መልበስ ጀምሯል፡፡ ምን ታረጊዋለሽ ዘመኑ የነሱ ሁኗል፡፡ (የካቲት 25/2004 ዓ.ም)*

ጉንፍና ጎዶ ቀሚሶች እንደ አሰሪው ቁመት መጠን በክንድ ተለክተው የሚሰሩ ናቸው፡፡ አንዲት ሴት ይህን በምታሰራበት ጊዜ በአማካይ ሀያ ስምንት ክንድ ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱም መጠናቸው እንደ አሰሪዋ ፍላጎት ነው፡፡

- መቀነት



ፎቶ.3 መቀነት የታጠቁ ሴቶች

መቀነትን ከህጻናት እስከ አዋቂዎች ያደርጉታል፡፡ መቀነት በሸማ ሰሪ የሚሰራ ጨርቅ ነው፡፡ አሰራሩ ሙሉ በሙሉ በቤት ውስጥ ፈትል አልያም ፈትልና ዝህውን በማቀላቀል ሊሆን ይችላል፡፡ የመቀነቱ ርዝመት ለሁሉም የቀሚስ አይነቶች የሚሰራው ስድስት ወይም ሰባት ክንድ

(ሶስት ሜትር) ሲሆን ስፋቱ ደግሞ ሁለት ክንድ ወይም አንድ ሜትር ነው፡፡ ከስድስቱ ክንድ በመቀነቱ ግራና ቀኝ ጫፎች ላይ ያሉት እዳይቶች ሁለቱን ክንድ (50 ሳ.ሜ x 2) ይይዛሉ፡፡ መቀነቱን ለማሰራት አሰሪዎቹ እንደፈለጉት የቀሚስ አይነቶች ነው፡፡ ይህም ለሽብሽቦ ወይም ለሽብሽብ ቀሚስ፣ ለጉንፍና፣ ለጎዶ ቀሚሶች የሚሰራው መቀነት በመጠንም ሆነ በእዳይት ይለያያል፡፡ ዋጋውም በአማካኝ እስከ 400 ብር ይደርሳል፡፡ እንደ እታገኘሁ ታፈረ ገለጻ፡-

*አሁን ለሽብሽቦ፣ ለነዶ (ጎዶ) እና ለጉንፍ ቀሚሶች የሚሰራው መቀነት እዳይቱ ይለያያል፡፡ ምክንያቱም ወገብ ላይ 3 ዙር ከተጠመጠመ በኋላ ወደ ታች እስከ ጉልበታችን ድረስ ዘርፈፍ ብሎ መለቀቅ አለበትና ነው፡፡ እናም የሽብሽቦ መቀነት ግን ወደ ታች ለቀቅ ብሎ ዘርፈፍ ስለማይል የተረፈውን አራትና አምስት ዙር በመጠምጠም ቀፈጣችንን ይሸክፍልናል" (የካቲት 25/2004 ዓ.ም)*

ሌላዋ መረጃ ሰጭ ደግሞ ወ/ሮ ሻሸቱ በዜ ሲሆኑ ይህንን ጉዳይ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል፡፡ *"መቀነት ሽብሽቦ ላይ ዝናር አስመስለን ሳናንዘረፍፍ እንታጠቀዋለን፡፡ ጉንፍና ቀሚስ ላይ ግን ቢያንስ አንዱን ዙር ያህል ዘርፈፍ እናረገዋለን፡፡ ስናሰራውም ቁመቱ 6 ክንድ ነው፡፡ ዝሀውን በክንዳችን ልክ እንጨቷን ለክተን በእንጨቱ እየለካን እናዘጋዋል፡፡"* መቀነት ለሽብሽቦ፣ለጉንፍ፣ ለጎዶ ቀሚስ እንዲሁም ለሌሎች የቀሚስ አይነቶች ወገብ ላይ የሚደረግከመሆኑም በላይ በባንጃ ወረዳ ነዋሪዎች መቀነት ላይ እዳይት[9] በብዛት አድርጎ ማሰራት የሀብት መገለጫ ነው፡፡

በመቀነቶቹ የሚገቡት እዳይቶች ብዛታቸው እስከ ሰባት የሚደርሱበትም አጋጣሚ አለ፡፡ እነሱም አረንጓዴ፣ ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ ጥቁር፣ ወይን ጠጅ፣ ደማቅ ሰማያዊ፣ ሲሆኑ ቀለሞቹ ውክልና ካላቸው ቀለሞች መካከልም ቀይ እና አረንጓዴ ናቸው፡፡ እነዚህም ቀዩ ውቃቤ አምላክን የሚጠቁም ሲሆን አረንጓዴው ደግሞ በመስከረም ወቅት ሰብሉና አበቦች በሚደርሱበት ጊዜ ያለውን ልምላሜ ያሳያል፡፡ በእነዚህ የእዳይት አይነቶች እና ብዛት የተሰሩት መቀነቶች ለሁሉም አይነት ቀሚሶች ያገለግላሉ፡፡ የመቀነቶቹ ግልጋሎቶች ወገብና ቀፈጥን (ቦርጭን) ሽክፎ ለመያዝ እና ቀሚሶቹ በተለይ ጉንፍና ጎዶ ቀሚሶች ወደ ታች ወርደው እንዳይዘረፈፉና መልክ እንዳያጡ ሽክፎ መያዝ ነው፡፡

---

[9] ጥለት ለማለት ነው፡፡

ሌላው ተጨማሪ ተግባሩ ደግሞ በቀጥታ መቀነቱ ላይ ካረፉት እዳይቶች ብዛትና ስፋት ጋር የተያያዘ ነው። እሱም የለባሿን የሀብት ደረጃ ማሳየት ነው። ብዙ እዳይት (ጥለት) ያለው መቀነት የለበሰች ሴት እንዲህ ተብሎም እንደሚገጠምላት አቶ አሳቤ ሙሉ ገልጸዋል።

እኔ እንደምወድሽ ትወጅኝ እንደሆን

አመጣለሻለሁ ቹንጉርጉርም ቢሆን (አሳቤ ሙሉ ጥር 12/2004 ዓ.ም)

### 4.1.2 የወንዶች ሀገረሰባዊ ልብሶች

በአዊ ብሄረሰብ በባንጃና አካባቢዋ ያሉ ወንዶች የሚለብሱት ልክ እንደ ሴቶች ሁሉ ከጥጥ ድርና ማግ በማሰባጠር ወይም እየቀል በማድረግ በሸማ በማሰራት ነው። የተሰራውን ሸማ በሱሪ መልክ እጀ ጠባብ፣ ወንጨሬ ወይም ተነፋነፍ፣ ጋቢ እና ኩታ አድርገው ይጠቀሙበታል። በአብዛኛው ግን ከጋቢና ከኩታ ውጭ የፋብሪካ ውጤት ከሆነው ከካሽሚር እና ካኪ የሚሰሩ ልብሶችን ይለብሳሉ።

- ወንጨሬ ወይም ተነፋነፍ



**ፎቶ4. ወንጨሬ ወይም ተነፋነፍ የለበሱ**

ይህን የሚለብሱት ከጋብቻ በኋላና ልጆች መውለድ ሲጀምሩ ነው። በአብዛኛው በዕድሜ ገፋ ያሉ ወንዶች ይለብሱታል። ከላይ ከወገባቸው እስከ ጉልበታቸው ድረስ ሰፋ ብሎ ከጉልበታቸው በታች እስከ ቁርጭምጭሚታቸው ድረስ ጠበብ ያለ ነው። ይህ የሱሪ አይነት ስያሜውን ያገኘው ከጉልበት

በላይ ያለው ሰፊና ለቀቅ ያለ በመሆኑ ተነፍንፏል በሚል ከአሰራሩ አንፃር ነው፡፡ ከጉልበት በታች ያለው በመጥበቡም ተወንጭሯል ከሚል ከአሰራሩ ሂደት የተነሳ የመጣ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች ያስረዳሉ፡፡ (ቡድን ውይይት የካቲት 23/2004 ዓ.ም)
ይህን የሱሪ አይነት ከሸማና በፋብሪካ ከተሰራ ጨርቅ የሚያሰሩት ሲሆን ሁለቱም ለተለያየ አላማ ይውላሉ፡፡ አንደኛው ከሸማ የሚሰራው ለጤና በሚል ታስቦ በአመት አንዴ የሚለበስ ሲሆን፤ ከፋብሪካ ጨርቅ የሚሰራው ደግሞ የክት ልብስ ነው፡፡ በሸማ ለማሰራት አቅም የሌለው በፋብሪካ የተሰራውን መብሩቅ የተሰኘውን ጨርቅ አሰፍቶ ለጤና በአመት አንዴም ቢሆን ይለበሳል፡፡

- ባተ ሁለት

ይህ ልክ እንደ ወንጨሬ ሁሉ አንድ ወንድ ወጣትነትን ሲያልፍ ወይም እጎልማሳነት የእድሜ ክልል ሲደርስ እንዲሁም ከጋብቻ በኂላ የሚለበሰው ነው፡፡



ፎቶ.5 ባተ ሁለት የለበሱ ወንዶች

ይህ የልብስ አይነት ከወገብ ወደ ታች እስከ ጉልበት ድረስ ሰፋ ያለ ሆኖ ከባት መሀል ላይ ከጉልበት በታች ጠበብ ተደርጎ የሚሰፋ ነው፡፡ ጥሬ ቁሱ በፋብሪካ በተመረተው ካኪ ይሰራል፡፡ ወንዱ ሱቅ ሂዶ ካኪውን በሜትር አስለክቶ ከገዛ በኂላ በመኪና ስፌት የሚሰፋ ነው፡፡ ባተ ሁለት መልበስ የሀብት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የሚለበስበት አጋጣሚም በዝክረ በዓላት፣ በሰርግ፣ በለቅሶ ወዘተ. ነው፡፡

- ጋቢ እና ኩታ

እነዚህ የልብስ አይነቶች ከወገብ በላይ የሚደረቡ ናቸው፡፡ የሚለበሰውም በዕድሜ የገፉ እናቶችና አባቶች ሲሆን ሙሉ በሙሉ ከጥጥ በተሰራ ማግ በሸማ የሚሰራ ነው፡፡ ቁመቱም በአብዛኛው ከ28 እስከ 32 ክንድ ሲሆን ወርዱ ደግሞ 400 ዝሀ በመሆን የሚሰራ ነው፡፡ ጋቢ ላይ የሚደረገውን እዳይት በተመለከተ አቶ አዲሱ መንገሻ ሲገልጹ፡- *‹‹ለጋቢ የምናሰራት እዳይት በመጠኗ ትንሽ ናት፡፡ ለሴት ሲሆን ትንሽ ሰፋ ይላል፡፡ ለኛ ለወንዶች ግን መጠኗ ማነስ አለባት፡፡ ምክንያቱም ከኩታው ጋቢውን ለመለየት ያክል እንጅ የጥለት ብዛት ለነጠላ ነው፡፡››*

ጋቢ ጥለቱ በጣም ትንሽ ነው፡፡ ኩታ በአካባቢው አጠራር ጎዶ በማለትም ይጠሩታል፡፡ ጎዶ እዳይት (ጥለት) የለውም፡፡ ከጋቢ የሚለየውም በጥለት አጣጣሉ ነው ማለት ነው፡፡ ጋቢና ኩታ የሚለበሱት በለቅሶ ጊዜ፣ በሰርግ እንዲሁም በተለያዩ በዓላት ወቅት ነው፡፡

- **የእረኛ አለባበስ**

- ቁምጣ



ፎቶ 6. ቁምጣ የለበሰ

ይህ ከእረኝነት ጀምሮ እስከ ጋብቻ ለመፈጸም እስከ ሚችሉበት እድሜ ድረስ የሚለበስ ነው፡፡ የሚለበሰው ከጭን በላይ አጠር ተደርጎ ነው፡፡ ቁምጣው የሚሰራው ከካሽሚር ሲሆን በመኪና

ስፌትም የሚሰፋ ነው። ሲሰፋ እንደ ተጠቃሚው የቁመት መጠን ይለያያል። ቁምጣ በመኪና ስፌት በሚሰፋበት ወቅት እንደ አሰሪው ፍላጎት ከጭኑ ጥብቅ ተደርጎና ሰፋ ተደርጎም ሊሰፋ ይችላል። በአካባቢው ባህል መሰረት ቁምጣ የለበሰ እረኛ የለበሰው ቁምጣ  ውበት እንዲኖረው ከኪሱ ጎን ወረንጦ ወይም ወስፌውን በቆዳ ከተሰራ ሽፋን ሽፍኖ ከጎኑ በማንጠልጠል ያደርጋል። ቁምጣ ሱሪ የሚያደርግበት ዋናው ምክንያትና ተግባሩ ከግማሽ ጭኑ በታች ያለውን የሰውነት ክፍል በውሀ በመታጠብ ሳሙና ለመቀባት እንዲያመቸው ነው። ይህ የሚሆነውም እግሩ ከሩቅ እንዲያብረቀርቅ ሲሆን ወረንጦ ወይም ወስፌው ከቁምጣው የሚንጠለጠለው ደግሞ ከብት ወይም ሌላ የእንስሳ ዝሪያዎችን በሚጠብቅበት ጊዜ እሾህ እግሩን ከወጋው ለማውጫነት እንዲያገለግል በሚል ነው።

ወረንጦው ውበት እንዲኖረው ለመያዥነት የሚጠቀሙበት ማንጠልጠያ ከበግ ቆዳ የተሰራ ሁኖ በቀለም የተነከረ መሆን አለበት። እንዲሁም ለተጨማሪ ውበት ሲባል ቁምጣው በመርፌ በክር ወይም በማዳበሪያ ይሰፋል ወይም በአካባቢው አጠራር ይዶከዶካል። ቁምጣው ሳይቀደድ እንዲሁ ከላዩ ላይ ይሠፋል። ይህ ተደጋግሞ በሚሰፋበት ጌዜ ጨርቁ እንዲወፍር ተብሎ ነው።


- ለምድ



ፎቶ 7.  ለምድ የለበሰ

በባንጃ ወረዳ በባታ ማሪያም፣ በቸውሳ እና በቅዳማጃ ቀበሌዎች በቆየሁባቸው ጊዜያት ወንዶች በእረኝነት ጊዜ በግብርና ስራ ወቅት ከቁምጣ በተጨማሪ ለምድ እንደሚለብሱ ተመልክቻለሁ። የዚህ ለምድ አሰራር ከበግ ቆዳ የሚሰራ ሲሆን ቆዳው ከደረቀ በኋላ የቆዳው ፀጉር አይነሳም። ምክንያቱም የለምዱ ዋና ተግባር ቅዝቃዜን ለመከላከል፣ እንዲሁም ለከብቶች ድርቆሽና የመሳሰሉትን መኖ ሲያቀርቡላቸው በትክሻቸው ለመሸከሚያ እንዲሆን ነው። ለምድ ከአቧራና ከመሳሰሉት ይከላከላል። በአሁኑ ጊዜ ይህ የቁስ አይነት መለበሱ እየቀነሰ መጥቷል። ምክንያቱም አዘነጎጃም እየተባለ በሚጠራው የቁስ አይነት እየተተካ በመምጣቱ ነው።

- **ገሳ**



**ፎቶ.8 ገሳ የለበሰ ወንድ**

ገሳ በአዊ የእረኞች ልብስ ነው። አሰራሩንም አቶ አብታም ምናለ ሲገልጹ *‹‹ አሰራሩ ከግራምጣ ሳር የሚሰራ ሲሆን ከላይ ከፅጉር እራስ እስከ ጉልበት በታች ድረስ በቁመት ልክ የሚሰራ ነው። ግራምጣውን ከግራምጣ እያጠላለፍነ ዝናብና ፅሀይ እንዳያስተላልፍ ጥቅጥቅ በማድረግ እያጠጋጋን የሚሰራ ነው።›› (መጋቢት 18/2004ዓ.ም)*

ይህን የለበሰ እረኛ በክረምትም ሆነ በበጋ ሌላ የዝናብና የጸሀይ መከላከያ አያስፈልገውም። ገሳ ለብሶ እንስሳትን የሚጠብቅ እረኛ ለስራው ታማኝና ታታሪ ነው ተብሎ እንደሚታሰብ የአካባቢው ነዋሪዎች ነግረውኛል። ይህ ቁስ ልክ እንደ ለምድ ሁሉ መለበሱ እየቀነሰ የመጣ ነው። ምክንያቱም አዘነ ጎጃም ከመጣ በኋላ በእረኞች መለበሱ እየቀረና እየቀነሰ እንደመጣ በአካባቢው በነበረኝ ቆይታ መረዳት ችያለሁ።

- **የጤና ልብስ**

የጤና አንድ ሰው ህመም በሚያመው ጊዜ ከህመሙ ለመፈወስ ሲል የሚያሰፋው የልብስ አይነት ነው። በሸማ የሚያሰሩት ወይም ከካሽሚር የሚያሰፉት ይህ የጤና ልብስ ለወንዶች መብሩቅ፣ እጀ ጠባብ ወይም ተነፋነፍ ነው። እንዲሁም ከላይ ጃኖ ጥለት ያለው ነጠላ ይለብሳሉ። ሴቶች ከሸማ የሚሰራ ጃኖ እዳይት ያለው ትፍትፍ (ዘርፉ ያልተፈተለ) መቀነት፣ ጎዶ ቀሚስ፣ነጠላ ናቸው።



**ፎቶ 9. የጤና ልብስ የለበሱ**

ለጤና ተብሎ የሚዘጋጀው ቀሚስ እዳይት ወይም ጥለቱ ክብ ሳይሆን ከኋላ በኩል ግማሽ ነው። የጤና ልብሱን ከባለቤቱ ውጭ ለሌላ ወገን ማሳየት የማህበረሰቡ ባህል አይፈቅድም። ምክንያቱም አንድም በሽታው ይተላለፋል ተብሎ ስለሚታመን አንድም አይን ያማል ስለሚባልና ያየችዋ ያየችውን አሰሩልኝ በማለት ስለምትታመም ነው። እዳይቱ ጃኖ የሆነበት ምክንያትም እናት አምላኳ

ደም ስለምትፈልግ በቀለሙ ለማመሳሰል እንደሆነ በአካባቢው ቆይታዬ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ወ/ሮ ፈለጉሽ ብርሌ እንደገለጹት

*የጤና ልብስ የምናሰፋው እኮ ዝም ብለን አይምሰልሽ ያየሁትን አይቼ ደስ ካለኝና ካመመኝ ያየሁትን እንዲሰፋልኝ አደርጋለሁ፡፡ ታዲያ እንዲያ ከሆነልኝ ከበሽታየ ይሻለኛል ማለት ነው፡፡ ውቃቤ አምላኬም በምትነሳብኝ ጊዜም ቢሆን የተሰራልኝን ስለብስ ከጤናየ ታሽለኛለች ማለት ነው፡፡ (መጋቢት 17/2004ዓ.ም)*

በአንዳንድ የአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ "ቡላን" የምትባል አባት አምላክ አለች ተብሎ ይታመናል፡፡ የሚያምኑባት አንዳንድ ሰዎች ለዚህች የሚሆን ልብስ ወንዶችም ሴቶችም አሰፍተው ይለብሳሉ፡፡ የሚለበሰውም ልብስ ከላይ ከጸጉራቸው እስከ እግራቸው ድረስ ሙሉ ነጭ ልብስ እና ጃኖ እዳይት ያለው ነው፡፡ የሚለበሰውም የአባት አምላኳ ትፈቅዳለች ተብሎ በሚታሰብበት በአብዛኛው በዘመን መለወጫ ወቅት ነው፡፡ ወ/ሮ ጽህይነሽ አበራ ስለ ጤና ልብስ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

*....ስናሰራ አንዷ የለበሰችውን አይተን ደስ እና እዳይቱ ደንገጥ ካረገን ደነገጥኩኝ አሰሩልኝ እንላለን፡፡ ወንዱም ቢሆን ያየውን "ያን መሳይ መብሩቅ አይቼ ነው ያመመኝ ይላል፡፡ እና የጤና ልብስ አይጎነፍም ልቅ ነው ሚሆነው፡፡የምንለብሰውም በዮሀንስ ነው፡፡ ያን ጊዜ ትከበራለች እና ነው፡፡ (ጥር 16 ቀን /2004 ዓ.ም)*

አንድ ሰው ሲታመም አይኑ ምን እንዳዩ ለህመም እንዳበቃው በቤተሰቡ አማካይነት ይጠየቃል፡፡ ያየውን ወይም ያየችውን አይነት ልብስ ይሰራላቸዋል፡፡ የጤና ልብስ በሚለበስበት ወቅት ለምሳሌ፡- ቅዱስ ዮሀንስ ከመድረሱ በፊት 1 ወር ቀደም ብሎ ከሚደረጉ ቅድመ ጥንቃቄዎች አንዱ የግብረ ስጋ ግንኙነት አለማድረግ ነው፡፡ አሰራሩን ስንመለከት ደግሞ ከጥጥ ማግ ብቻ ነው የሚሰራው፡፡ እንደ ሌሎቹ የሽማ ውጤቶች የፋብሪካ ውጤት የሆነውን ዝሀን አያካትትም፡፡ ምክንያቱም ሌላ ባዕድ ነገር እንዲቀላቀልበት ልማዱ ስለማይፈቅድ ነው፡፡ በባህሉ መሰረት የጤና ልብሱ ሌላ ባዕድ ነገርን አካቶ በሽማ ከተሰራ በሽታን ላያድን ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ለጤናው ልብስ የሚሆነውን የምትፈትለዋ ሴት የወር አባባዋን ማየት ያቆመች መሆን አለባት ተብሎም ይታመናል፡፡ በሽማ የሚሰራውም ሰውም የግብረ ስጋ ግንኙነት የማያደርግ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ልብሱ ይረክሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (የቡድን ውይይት በቸውሳ ቀበሌ መጋቢት 12/2004 ዓ.ም)፡፡

በተጨማሪም እንደዬ አሰሪው ፍላጎት በሸማ ተሰርቶ ካለቀና ከተቆረጠ በኋላ በመኪና ስፌት ሳይሆን በሰው እጅ ወፍ እግር[10] በሚባለው ቅርጽ ይሰፋል፡፡ በመኪና ስፌት ከተሰፋ ባዕድ ነገር ከነካው ይረክሳል ተብሎ ይታሰባል፡፡

የወንዶች መብሩቅ፣ጋቢ፣ ነጠላ፣ ሻሽ፣ሲሆኑ አዳይታቸውም ጃኖ ነው፡፡ ጃኖ ቀይ ጥለት የሚሆነው ውቃቤ አምላካቸው የሚፈቅደው ቀይ ጥለት ስለሆነና አዳይቱ ቀይ ካልሆነ ያስጎራል፣ ያሳምማል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

## 4.2 ሀገረሰባዊ ጌጣጌጦች

በአዊ ብሄረሰብ የተለያዩ አይነት ጌጦች (በተለይ የሴቶች) አሉ፡፡ ሴቶች ከብር ከነሀስና ከቆርቆሮ የተሰራ አልቦ፣ ድሪ፣ ጉትቻ፣ አምባር፣ እርባን፣ መስቀል፣ ብር ቅጥል አንገታቸው ላይ፣ እግርና እጃቸው ላይ በማድረግ ያጌጣሉ፡፡ ጌጦች እንደየ አገልግሎታቸው የተለያዩ ሲሆኑ በዚህ ንዑስ ክፍል የሚገለጹት ጌጣጌጦችም ትዕምርታዊ ፋይዳቸው ጉልህ የሆኑት ናቸው፡፡

ሀገረሰባዊ ጌጦች ተጨማሪ ውበት ከመስጠታቸው በላይ የተለያዩ ተግባራት አሏቸው፡፡ ከሚደረጉበት የሰውነት ክፍል አንፃር የጆሮ፣ የአንገት፣ የእጅ፣ የእግር ተብለው ይለያያሉ፡፡ በሚሰሩበት የቁስ አይነትና ቅርፅ እንዲሁም ማህበረሰቡ በሚሰጣቸው ውክልናም ይለያያሉ፡፡

[10] በሰው እጅ የሚሰፋ ሲሆን ለጋቢና ለነጠላ የሚያገለግል ነው፡፡

### 4.2.1 የአንገት ጌጥ




ፎቶ 10. የአንገት ጌጥ ያጠለቀች

በባንጃና አካባቢዋ የሚኖሩ ሴቶች በሌሎች አካላቸው ከሚያደርጓቸው ጌጦች ይልቅ በአንገታቸው ላይ የሚያደርጓቸው ጌጦች በቁጥርም ሆነ በአይነት ይበዛሉ፡፡ ጌጦቹም ዘጠኝ ያህል ሲሆኑ እነሱም፡- ሳንቃድሪ፣ እርባን፣ ቢሪጂ፣ ትልቅ መስቀል፣ ድንብል ቀለበት፣ ታጣፊ መስቀል (ግማደ መስቀል)፣ ትርገብገብ መስቀል፣ ብር ቅጥል፣ የብር ቅጥል ማከፋፈያ ሲሆኑ እነሱም በጥቁር በማተብ የሚታሰሩ ናቸው፡፡

ሴቶች ክርስቲያን መሆናቸውን ለማመልከት በአንገታቸው ከሚያደርጉት ትንሽ የብር መስቀል በተጨማሪ አንደ እድሜያቸው እና እንደሚያልፉባቸው ማህበራዊ ደረጃዎች ማለትም ከማግባታቸው በፊት እና ካገቡ በኂላ የተለያዩ ጌጦችን ያደርጋሉ፡፡

እነዚህ ቁሶች የሚሰሩት በአገው ባህል መሰረት ከብር ነው፡፡ ነገር ግን አሁን አሁን ጌጦችን በሌሎች ግብዓቶች እያቀላቀሉ መሰራት የተለመደ ሁኗል፡፡ ይህ ደግሞ ከብሩ መወደድ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጉዳይ ነው፡፡ አባ ያየህ ሙሴ እደገለጹትም

*‹‹ጌጣጌጦችን በብር ብቻ ማሰራት ድሮ ቀረ ምክንያቱም ብሩ በጣም ስለተወደደ ነው እንጅ ሰው ጠልቶት አይደለም፡፡ ያው በጣም ሀብታሞቹ ጌጣቸውን በብር ብቻ ያሰራሉ፡፡ አቅሙ የሌላቸው ግን ሌሎች ግብዓቶችን በመቀላቀል ያሰራሉ፡፡›› (መጋቢት 18/2004ዓ.ም)*

ጌጦቹን በሌሎች ግብዓቶች መስራት በተጀመረበት በአሁኑ ጊዜም ቢሆን አቅም እስካለ ድረስ የሚመረጠው በብር ማሰራት ነው፡፡ ማጌጫዎች ከጥንት ጀምሮ በብር የሚሰሩበትን ምክንያት ከመረጃ አቀባዮቼ ባገኙሁት መረጃ መሰረት አንድም ጠገራ ብር የክብር መገለጫ ተደርጎ መቆጠሩ ነው፡፡ ይህ ሲባል ከሰይጣን፣ ከሰው አይን እና ከሌሎች ባዕዳን ነገሮች ቁሱ ይጠብቀናል ከሚል እምነት የተነሳ ነው፡፡

አንገቷ ላይ ጌጣጌጥ ያበዛች ሴት የሀብት ደረጃዋን ያመላክታል፡፡ አቶ አሳቤ ሙሉ እንዲህ ተብሎም እንደሚገጠምላት ገልጸውልኛል ፡፡

> *ያንገቷ መሳሪያ ወርዶ ቢከማች*
>
> *አንድ ላም ያስገዛል ታማ የዳነች፡፡* (መጋቢት 15/2004 ዓ.ም) ተብላ ትሞገሳለች፡፡

- ሳንቃ ድሪ፡-



ፎቶ 11. ሳንቃ ድሪ ያደረገች ሴት

በአዊ ብሄረሰብ ባንጃ አካባቢ ያሉ ያገቡም ሆነ ያላገቡ ሴቶች እራሳቸውን ለማስጌጥ ከሚጠቀሙባቸው ጌጦች መካከል ሳንቃ ድሪ አንዱ ነው። ድሪ በአሁኑ ወቅት ብዙውን ጊዜ ከኒኬል አንዳንዴ ደግሞ ከብር ይሰራል። ድሪ ከጋብቻ በኂላ ለረጅም ጊዜ (በእርጅና ወቅትም) ቢሆን ይጌጥበታል። ሳንቃ ድሪው ቁመቱ 1 ሜትር 30 ሳ.ሜ ሲሆን ከቁመት ጫፍ ወይም መሀል ላይ አራት ማዕዘን ሳጥን እና ከላዩ ክብ ዋንጫ መሳይ ቅርፅ ሲኖረው መሀሉን ክፍት በማድረግ የሚሰራ ነው።

አሰራሩን በተመለከተም ብር ወይም ኒኬል አልያም መዳብን በመቀላቀል እና ለየቅል በማድረግ መጀመሪያ በእሳት ይቀልጣል። ከዛም ከቀለጠ በኂላ በቅርፅ ማውጫ ብረት ይቆራረጣል። በክብ ማውጫዋ ብረት የተቆራረጠውን ቁስ እርስ በርስ ወይም አንዱን በአንዱ በማሳካካት ይቆላለፋል።

አባ ያየህ ሙሴ ድሪው ስለሚሰራበት እቃና አሰራሩን በተመለከተ እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡-

> *መቀጥቀጫዋ መሰፍ ትባላለች። አንዳንዶች ዝቤዛም ይሏታል። ከጭቃ የተሰራችዋ ቅርፅ ማውጫ አፈሞራ ትባለለች። ለእሳቱ ማያያዣ ደግሞ ማናፊያ ሲባል የእሳቱ ከሰል እንደማናቸውም ሳይሆን ከጨባና ከቀሞ ዛፍ የከሰለ መሆን አለበት። ካለዚያ የሌላ ዛፍ ከሆነ ጌጡን አመዱ ያከስለዋል። አሁን እኔ የምሰራቸው ድሪ፣ አምባር መስቀል፣ አልቦ ቀለበት ጉትቻ ሲሆኑ እንደ ድሮው ብዙ ገበያ የለውም። ምክንያቱም መዳርና መኳል እየቀረ ስለመጣ ነው። (ቃለ መጠይቅ/አንጥረኛ መጋቢት 18 2004 ዓ.ም)*

ሳንቃ ድሪ ከጌጥነቱ በተጨማሪ ለሽቶ መያዣነትም ያገለግላል። መሀል ላይ በአራት ማዕዘን ቅርጽ የተሰራው እና በጀርባ በኩል በማድረግ ሽታ ካላቸው ቅጠሎች የተሰሩ "ስንቡል" እና "አደስ" ሽቶዎችን በመያዝ አንዳንድ በዓላትና ዝክሮች ላይ በሚሄዱበት ጊዜ ይጠቀሙባቸዋል።

- ብር ቅጥል




**ፎቶ12. ብር ቅጥል ያደረገች ሴት**

ይህ ጌጥ በባንጃ ባህል መሰረት ሴቶች ብቻ የሚያደርት ነው፡፡ በዓላት ሳይጠበቅም ቢሆን ዘወትር በአዊ ሴት አንገት ላይ የብር ቅጥል አይጠፋም፡፡ ይህ የጌጥ አይነት ስያሜውን ያገኘውም ከላይ ለማተብ ማስገቢያ የሚሆን ቅጥያ ስለተጨመረበት ነው፡፡

እንደ የክትነሽ ገለፃ ደግሞ፡-

*አሁን አሁን በነሀስና ኒኬል እያስሩ በማስቀጠል አንገታቸው ያደርጉታል፡፡ ግን ልክ እንደ ብሩ አያምርምም አይደምቅምም እንደው እንዳይቀር ነው ሚያረጉት፡፡ አንገቷ ላይ ብር ቅጥል ያላረገች ሴት አንድያው ከቤቷ የምትበላው እህል የለም ማለት ነው፡፡ ለምን ብትይ ቅድም ሲቸግረን ያንገታችንን መሳሪያ እንሸጣለን እናም የአንገታችን ብር የክፉ ቀናችን መጠጊያ በመሆኑ አንገቷ ባዶ ከሆነ "እረ ቢቸግራት ሸጠችው" እንላለን፡፡ (ጥር16/2004 ዓ.ም)*

አንድ ሴት ስታገባ ባሏ ማጫ ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ ይሰጣታል፡፡ ከዛም እሷ ከማግባቷ በፊት ለማጌጥ ቢያንስ የተወሰነ በአንገቷ ማድረግ አለባት፡፡ ይህን ካላደረገች ግን "የድሀ ልጅ" ስለሆነች እሚያጫት አይኖርም ተብሎ ይታመናል፡፡

በአዊ ብሄረሰብ በባንጃ ገጠራማ አካባቢ የምትገኝ ሴት በአንገቷ ቢያንስ ሁለትና ከዚያ በላይ ጠገራ ብር ማድረግ አለባት፡፡ ይህ የቤተሰቧን የባሏን የኑሮ ደረጃም ይገልጻል፡፡ በብዛት ብር ቅጥሎችን

በማተቧ ካደረገች ሀብታም እንደሆነች ያሳያል፡፡ እንዲሁም ከጋብቻ በኂላ ልጅ ስትወልድ የእንግዴ ልጅ ሲዘገይ በጥርሷ በማጣበቅ ብር ቅጥሉን ትነክሰዋለች፡፡ ይህ የሚሆነውም እንግዴ ልጁን ቶሎ ያመጣዋል ተብሎ ስለሚታሰብና ድንገት ህሊናዋን ከሳተች ብር ቅጥሉን ከጥርሷ ስትለቀው ራሷን እንደሳተች ጥቆማ ይሠጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ (የቡድን ውይይት ቅዳማጃ ቀበሌ ጥር 16 2004ዓ.ም)

ብር ቅጥል ትክክለኛ ከብር የተሰራ ከሆነ እስከ 450 ብር ያወጣል፡፡ አንጥረኛው ግን ለገንዘብ መያዣነት ተቀብሮ ከነበረውና አውጥተው ከሚሸጡት የተቀበረ ብር በቀነስ ሂሳብ ይገዛዋል፡፡

- ቢሪጃ



ፎቶ 13. ቢሪጃ ያደረገች

ይህ የጌጥ አይነት ለሁለቱም ጾታዎችና ለሁሉም የእድሜ ክልሎች የሚያገለግል ነው፡፡ ከህጻን እስከ አዛውንት ለጌጥነት ከመጠቀም ባሻገር ሌላ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው እና በማንኛውም ወቅት እና ጊዜ የሚደረግ እንደሆነ ከአካባቢው በነበረኝ ቆይታ ተገንዝቤያለሁ፡፡ አሰራሩን በተመለከተ በቂ መረጃ ለማግኘት አልቻልኩም፡፡ ምክንያቱም ይህ የቁስ አይነት ሲሰራ በድብቅ በመሆኑ እና የቁስ ተማሪዎቹም ስለ አሰራሩ ለመናገር በሚሰጥር የሚሰራ በመሆኑ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡

ይህ በሌላ ስሙ "የደም መድሀኒት" በመባል የሚታወቀው ጌጥ አይነት የሚሸጠው እንደማንኛውም የጌጥ አይነት በገበያ ላይ ሳይሆን በአካባቢው ነዋሪ ከሆኑት የቆሎ ተማሪዎች ነው፡፡ ወ/ሮ ብርቱካን

አካሉ ይህ የጌጥ አይነት ለሴቶች ለወር አበባ ጊዜ ደም እንዳይበዛ፣ ሲነስራቸው፣ ለደም ግፊት፣ በመንገድ እንቅፋት በሚመታቸው ጊዜ ደግሞ ብዙ ደም እንዳይፈስ የሚከላከል እንደሆነ ገልጻውል ኛል፡፡ ለወንዶችም በተመሳሳይ በተለያዩ አጋጣሚ እና ምክንያት የሚፈስ ደምን መጠን ለመቀነስ ያገለግላል፡፡

➢ እርባን



ፎቶ 14. እርባን ያደረገች ሴት

ይህ የጌጥ አይነት የሚያደርጉት በአብዛኛው እናቶች ሲሆኑ የሚሰራው ከብር፣ ከኒኬል እና ከነሀስ የሚሰራ ሆኖ አራት ማዕዘንና ሶስት ማዕዘንን ቅርፅ የያዘ ሲሆን ለማተብ ማስገቢያ ከላዩ ላይ ቅጥያ ያለው ነው፡፡ ይህ ከጋብቻ በኂላ አመት በዓል ተጠብቆና በሰርግ ጊዜ እንዲሁም በአንዳንድ የደስታ አጋጣሚዎች የሚደረግ ሲሆን በተደራራብ ጥቁር ማተብ በእያንዳንዱ እርባን መካከል 0.3 ሳ.ሜ ተራርቆ የሚደረደር ነው፡፡

## 4.2.2 የእጅ ጌጥ

➢ አምባር

ፎቶ15.



ድንብል አምባር



ጥፍጥፍ አምባር



ጉብጉብ አምባር

ጥናቱ በተካሄደበት ወረዳ ያሉ ልጃገረዶች እና እናቶች በእጃቸው አድርገው ከሚያጌጡባቸው ቁሶች አንዱ አምባር ነው፡፡ በእደ ጥበብ ሙያተኞች የሚሰሩ የተለያዩ የአምባር አይነቶች አሉ፡፡ ሁሉም የአምባር አይነቶች ከብር፣ ከነሀስ እና ከኒኬል የሚሰሩ ናቸው፡፡ ጉብጉብ አንባር የሚባለው የውጨኛው አካሉ ጉብጉብ ወይም ጉጥ ጉጥ ያለ ቅርጽ አለው፡፡ ድምብል አምባር የሚባለው ደግሞ ክብደቱ በአማካይ 20 ግራም ይሆናል፡፡ በወፍራሙ የሚዘጋጅ ሲሆን በስፋቱ አነስ ያለ ነው፡፡ አሰራሩ ብር ኒኬል ወይም ነሀስ በእሳት ከጋለ በኂላ በወፍራሙ ክብ ይሰራና ጫፍ ላይ ትንሽ ክፍተት በመተው በክፍተቱ ጫፍና ጫፍ ላይ ጉጠት ወይም ደቡልቡል ቅርፅ እንዲይዝ ይሆናል፡፡ ጥፍጥፍ አምባር የሚባለው ደግሞ ከሌሎች የአምባር አይነቶች በስፋቱ ረዘም ብሎ የሚሰራ ሲሆን በውጨኛው አካሉ ምንም አይነት ቅርፅ እንዳይኖረው ተደርጎ የሚሰራ ነው፡፡

እነዚህ የአምባር አይነቶች እንዳሰራራቸው መለያየት ዋጋቸውም ከፍ እና ዝቅ ያለ ነው፡፡ በተለይ ከብር የሚሰራው ድንብል አምባር እና ጉብጉብ አምባር እስከ አምስት ጠገራ ብር ሊወስድ ስለሚችል በአሁኑ ገበያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ሀምሳ ብር በላይ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የሚያጨው ሰው አንደ አቅሙ ከእነዚህ የአምባር አይነቶች እንዱን ብቻ ገዝቶ ሊሰጥ እንደሚችል አቶ ከተማ ቢተው ገልጸውልኛል፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ የጌጣጌጥ ሰራተኛ፣ መጋቢት 23 ቀን 2004 ዓ.ም)

በዚህ መሰረት ላቅ ያለ ሀብት ያለው ሰው ድንብል (ብዙ መጠን ያለውና ውድ) የሚባለውን አምባር ሲገዛ ባንጻሩ ደግሞ ዝቅ ያለ ኑሮ የሚኖረው አነስተኛ ዋጋ ያለውን አምባር ሊገዛ ይችላል፡፡ በመሆኑም እጮኛዋ ገዝቶ በማጫ በሰጣት አምባር ሴቷ ከታጨት እለት ጀምሮ እስከ ምታረጅ ድረስ ልታጌጥበት ትችላለች

## 4.2.3 የእግር ጌጥ

- አልቦ



ፎቶ16. አልቦ ያደረገች ሴት

በዚህ ጌጥ የሚዋቡት ሴቶች ብቻ ናቸው፡፡ በግራና ቀኝ እግር የሚጠለቅ ሲሆን አልቦ በማለት ይጠሩታል፡፡ አልቦ የሚሰራው ከብር ከኒኬልና ከነሀስ ነው፡፡ በዚህ ጌጥ የሚዋቡት ያገቡትም ያላገቡትም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚደረገውም ዘወትር ወቅቶችን ሳይጠብቅ ሲሆን አሁን አሁን ግን መደረጉ እየቀነሰ መጥቷል፡፡

## 4.2.4 የጸጉር አሰራር

በባንጃ የተለመዱት ባህላዊ የጸጉር አሰራርና አይነቶች ከእድሜና ከማህበራዊ እርከኖች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በአዊ ባህል መሰረትም ፀጉር በረጅሙ አያድግም ወይም ሹሩባ ለመሰራት ልማዱ አይፈቅድም፡፡ በባህሉ መሰረት ሴት ልጅ ጸጉራን አሳድጋ ሹሩባ ከተሰራች እንደነውር

ከመቆጠሩ ባሻገር ያገባችም ሆነ ያላገባች ከሆነች እንደ ሴተኛ አዳሪ እንደምትታይ በአካባቢው በነበረኝ ቆይታ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ሴቶች በአጭሩ በመላጨት እና በመቆረጥ ጎፈሬ በማድረግ ዙሪያውን ወይም ዳርዳሩን ክርክም፣ ጋሜና ቁንጮ፣ጋሜ ቅርድድ፣ሳዱላ የሚባሉትን የአለጫጨት አይነቶች ሲጠቀሙ ወንዶች ደግሞ ቁንጮ እና ተሬ ይላጫሉ፡፡ ወንዶች ከእረኝነት ጊዜያቸው በኋላ ተሬያቸውንና ቁንጯቸውን በመተው በአጭሩ በመላጨት ሻሽ ይጠመጥማሉ፡፡

➢ ጋሜና ቁንጮ



ፎቶ 17. ጋሜና ቁንጮ




ጋሜ ቅርድድ የተላጩ

ጋሜና ቁንጮ ከላይ ምስሉ እንደሚያሳየው ከፊት ለፊት ከግንባራቸውና ከመሀል አናታቸው ላይ ጸጉር በማስቀረት የሚላጭ ነው፡፡ ጋሜና ቁንጮ እንዲሁም ጋሜ ቅርድድ መሀል አናታቸውን በሰፊው በመላጨት ዳርዳሩን በማስቀረት የሚላጭ ነው፡፡ ሴቷ ጋሜ ቅርድድ ሆና መላጨት በምትጀምርበት ወቅት ለመታጨት መድረሷን አመላካች ነው፡፡ በጋሜና ቁንጮ እረኝነቷን አቁማ ወደጋሜ ቀረድድ ስትሸጋገር እራሷን እየጠበቀች ከእናቷ ጋር ቤት ውስጥ መዋል ትጀምራለች፡፡ በዚህ ወቅትም ትታጫለች፡፡ ከጋሜዋ ቁንጮ ካለው ደግሞ በእረኝነት ስራ ላይ እንዳለች አመላካች ነው፡፡ ለመታጨት ከጋሜው ያለውን ቁንጮ መላጨት አለባት፡፡ በዚህም ከመሀል ያለችዋን ቁንጮ ሽሩባ ትሰራለች፡፡

> *እኛ አዊዎች ግልጽ ብርሀን እንጅ ጨለማን አናውቅም በዚህም ጋሜ ቅርድድ የተላጨች ሴት መሀሉን በክብ ክፍት አድርጋ ምትላጨው ግልጽና ልቧ ምንም ድብቅነት እንደሌለ ለማሳየት ነው፡፡ ለዚህም መሀሉን ሙሉ በሙሉ በመላጨት ዳርዳሩን በትንሹ ታስቀረዋለች፡፡* በማለት ፈለጉሽብርሴ (ቃለመጠይቅፐር 12 /2004ዓ.ም) ስለ ጌጦቹ ነግራኛለች፡፡

ይህ የጌጥ አይነትም የሚሰራው ሙሉ በሙሉ በቤት ውስጥ ሲሆን በእናትና በሴት አያት አማካይነት የሚፈጸም ነው፡፡

- **ሳዱላ**



ፎቶ 18.

ሴቷ የጋሜና ቁንጮ ጊዜዋን እንደጨረሰች ወደ ሳዱላ ተሻግራ በሳዱላ ማጌጥ ትጀምራለች፡፡ ሳዱላ የሚባለው ጋሜና ቁንጮ ከደፈነ በኋላ የሚመጣ የጸጉር አለጫጨት ሂደት ነው፡፡ ሴቷም ወደ ትልቅነት የምትሸጋገርበት  ጊዜዋ ነው፡፡

ሳዱላ የሚወጣው ጋሜ እና ቁንጮ እያደገ፣ እየጠበበ በሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም ህፃን እያለች ቁንጮዋ አርፎበት ከነበረው መጨረሻ ላይ ከላይ በክብ ቅርፅ (በብር ተለክታ) በቅርፅ ትላጫለች፡፡ በዚህ ወቅት ‹‹የእከሊት ሚስት ትልቅ ሆነች፤ ሳዱላ ተቀረደደች›› ይባላል፡፡ ይህንን ሀሳብ ወ/ሮ ፀሀይነሽ ፡-

*ሳዱላ ካገባች በኋላ አንድ ወይም ሁለት እንዲያ ስትወልድ በክቧ እንድታምር በብር ቅጥል ተለክታ ትላጫለች፡፡ የዛን ጊዜ እከሊት አደገች ትልቅ ሆነች እንላለን፡፡ ከዚያ ሳዱላዋ እየጠበበች ትሄድና ድፍን ክርክም ትቆረጣለች ማለት ነው፡፡ ያን ግዜ እናትነቷን አሳወቀች ማለት ነው››፡፡ (ቃለመጠይቅ ጥር 19/2004 ዓ.ም)*

ሳዱላ የተቀረደደች ሴትም በዘፈን መልክ እንዲህ ተብሎ እንደሚገጠምላት አክላ ገልጻለች፡፡ በማለት ገልጸውልኛል፡፡


ሳዱላዬ ነይ አልቦሽን አርገሽ
በጥልፉ ቀሚስ አምረሽ ተውበሽ *(ጸሀይነሽ አበራ ቃለመጠይቅ ጥር 19/2004 ዓ.ም)*

## 4.2.5 ውቅራት (ንቅሳት)

ፎቶ 19.



የአንገት



የእግር

ንቅሳት (ውቅራት) በአብዛኛው ማለት ይቻላል በአዊ ብሄረሰብ በገጠሩ ነዋሪ ተዘውትሮ ይፈጸማል፡፡ ይህ ክዋኔ የሚፈፅመው በሴቶች ሲሆን በአብዛኛው በወጣት ሴቶች ይዘወተራል፡፡ በዋነኝነት ሴቶች የሚነቀሱበት ምክንያት አንዱ የቁንጅና ወይም የማስጌጫ መንገድ ተደርጎ ስለሚታይ ነው፡፡ ንቅሳት (ውቅራት) ለእይታ አመቺ በሆኑ ቦታዎች ማለትም ፊት፣ ጥርስ፣ አንገት፣ እግር፣ ግንባር የሚደረግ ሲሆን የሚወቀሩትም ሴቶች በአብዛኛው ቀላ ያሉት ናቸው፡፡ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ይነቀሳሉ፡፡ ውቅራት ከማስዋቢያነቱ ባሻገር ለእራስ ምታት፣ለድድ መድማት፣ ለእንቅርት በሽታዎች መፈወሻነት እንዲሁም የሴትን ልጅ ቁመት ለማሳጠር ይጠቅማል ተብሎ የሚታመን መሆኑን በመረጃ አቀባዮቼ ከሰጡኝ ሀሳብ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ምክንያቱም ሴት ልጅ እግሯን የምትነቀሰው ቁመቷ ከረዘመ የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ትሰብራለች ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

ወንዶች በሁሉም አካላቸው ላይ የሚያደርጓቸውን የውቅራት አይነቶች የእረኝነት ጊዜያቸውን ጨርሰው እስኪያገቡ ድረስ ባለው ጊዜ ያጌጡባቸዋል። የጥርስ ውቅራቱም የሚጌጥበት በዚህ ወቅት ሲሆን አወቃቀሩም ጉራማይሌ[11] የሚባለው አይነት ነው።

የአዊ ብሄረሰብ ባንጃ ወረዳ አካባቢ ጎረምሳ በጉራማይሌ እንጂ ጥርሱን ሙሉ በሙሉ ተወቅሮ አያጌጥም። ሙሉ ውቅራት የትልቅነት (የማጌጫ ጊዜን የመጨረስ) ምልክት ነው። እንደ ደጅ ጥኑ ምናለ ገለፃ *‹‹ንቅሳት በወንዶች የሚያምረው በእረኝነትና በጉርምስና ወቅታቸው እንጂ በተለይ ካገቡ በኋላ መሳቂያ ነው ሚሆነው። ደም ካገባ በኋላ እሱ ምን ሲያረግ ጉራማይሌ ይነቀሳል። ለሚስቱም ጥሩ አይደል›› (ጥር 14 ቀን 2004 ዓ.ም)* ወንዶች ከጋብቻ በፊት ከሚያጌጡባቸው ጌጦች መካከል ንቅሳት አንዱ ሲሆን በአብዛኛው ጥርሳቸውን ጉራማይሌ እና አይናቸውን ከቅንድባቸው መሀል እንዲሁም እግራቸውን ከቁርጭምጭሚታቸው ከፍ ብሎ በመነቀስ ያጌጣሉ።

- የአንገት ንቅሳት



ፎቶ 20.

ከውቅራት አገልግሎት አንዱ ውበትን ጨምሮ ጎልተው እንዲታዩ ማድረግ ነው። ይህ ተጨማሪ ውበት ደግሞ ተመራጭነትንና ሙገሳን ያስከትላል። በባንጃ አካባቢ በአንገት ውቅራት ደምቆና አጊጦ መታየት በአካባቢው ማህበረሰብ እንዲህ በማለት እንደሚሞገስ አቶ አሳቤ ሙሉ ነግረውኛል።

ሲፃፍ የምናየው በወረቀት ላይ
ቀለም በሰው አንገት እንዲህ ያምራል ወይ (ጥር 16/2004ዓ.ም)

[11] ድዳቸው አልፎ አልፎ የሚነቀሱት የወንዶች የጥርስ ንቅሳት አይነት ነው።

በማለት ተራኪው የአንገቷን ውቅራት ያሞካሻታል። ይህ የንቅሳቱን ቀለም አጣጣልና የዲዛይን ቅርፅ ምን ያህል እንደማረከው ለማመልከት የተነገረ ቃል ግጥም ነው።

በባህሉ መሰረት አንገታቸውን የሚነቀሱት ቀላ ያሉ አንገተ መለሎ የሚባሉት ናቸው። ጠቆር ያሉ እና አንገተ አጭር ሴቶች ከተወቀሩ በማህበረሰቡ ዘንድ ይነቀፋሉ።


- የእጅ ውቅራት



ፎቶ21.

የእጅ ውቅራት በአብዛኛው ሴቶች ከማግባታቸው በፊት የሚነቀሱት ሲሆን በእረኝነት ጊዜያቸው እርስ በርስ የሚነቃቀሱት ነው። የአዊ ሴቶች እጃቸውን የሚነቀሱበት ምክንያት ከማጌጫነት በተጨማሪ ለቁርጥማት መፈወሻነትም ብለው ነው። ይህ ውቅራት ባለሙያን የሚጠይቅ ሳይሆን በአቻ እድሜ ላይ ያሉ ሴቶች በእረኝነት ስራቸው ወቅት ሜዳ ላይ በሚያገኙዋቸው ቁሶች (የድንች ቅጠል እና ዋኸርማ ቅጠል) አማካይነት በአብዛኛው እርስ በእርስ የሚወቃቀሩት ነው።

➢ የእግር ውቅራት



ፎቶ 22

በባንጃ አካባቢ ሴቶች ቁመታቸው እንዲረዝም አይፈለግም፡፡ ስለዚህ በመሆኑም ከቁርጭምጭሚ ታቸው በታች ባታቸው ላይ በመነቀስ ቁመታቸው ያጥራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ሴት ልጅ ቁመቷ ከረዘመ የቤት ውስጥ እቃዎችን ትሰብራለ በሚል እምነት ስላለ ነው፡፡ ወንዶችም ባታቸውን በመነቀስ ከጌጥነት በተጨማሪ ለቁርጥማት መከላከያነት ይጠቀሙበታል፡፡

➢ የጥርስ ውቅራት

የጥርስ ውቅት ከማጌጫነት ባለፈ ለድድ መድማትና የወጣን ድድ ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ሲባል ይደረጋል፡፡ ወንዶች ጉራማይሌ (ድዳቸውን አልፎ አልፎ) የተሰኘውን ውቅራት ሲነቀሱ ሴቶች ደግሞ ድዳቸውን ድፍን ይወቀራሉ፡፡ ይህ የውቅራት አይነት በባለሙያ የሚከናወን ነው፡፡ ምክንያቱም ሲወቀሩ ድዳቸው ላይ ብዙ ደም ስለሚፈስና ህመሙ ይከብድባቸዋል፡፡ የሚወቀሩት አስቀድመው አረቄ እን ዲጠጡ ይደረጋል፡፡ በአፋቸው ተጎንጭተው እንዲይዙትም ይደረጋል፡፡ ይህም የሚደረገው ህመሙ እንዳይሰማቸው ሲባል ነው፡፡ ጥርሷን የተነቀሰች ወጣትም እንዲህ ተብሎ ይገጠምላታል፡፡

ዝንጀሮ በገደል ይላል አጎምደሌ

የጥርሷ ንቅሳት ያስለውጣል በሬ (አሳቤ ሙሉ መጋቢት 22/2004 ዓ.ም

ይህ ውቅራቷ ውበቷን እንዳደመቀውና ማጫዋን ክብደት እንደሰጠው ያመለክታል፡፡ የወደዳት ጎረምሳም በውቅራቷ የተማረከ በሬን ያህል ጥሎሽ ሊሰጥ እንደሚችል ይጠቀማል፡፡

በአጠቃላይ ወጣቶች ልብሶችና ከጌጣጌጦቹ በተጨማሪ ሌሎች የሚዋቡባቸው ነገሮች መኖራቸውን በተካሄደው ቃለመጠይቅ እና ምልከታ የተገኘው ምላሽ ያስረዳል፡፡ በዚህ መሰረትም በባንጃ ወረዳ ቀበሌዎች ሴቶቹ የአይናቸውን ሽፋሽፍትና ስሩን ኩል ይኳኳላሉ፡፡ እጅና እግራቸውን በእንሶስላ ይሞቃሉ፡፡ በተለያዩ በዓላት እና ሰርጎች ጊዜ የሴቶች እንሶስላ መሞቅ የተለመደ ነው፡፡ በሰርግ ወቅትም ሙሽራዋ በዋዜማው እለት እንሶስላ እጇን እና እግሯን ትሞቃለች፡፡ እንዲሁም ቅቤ በሚቀቡበት ሰዓት ስንቡል እና አደስ አብረው በመቀላቀል ይቀቡታል ፡፡ ይህ የቅቤውን ሽታ ወደ ጥሩ መዓዛነት ለመቀየር ነው፡፡ ከወንዶች ይልቅ በአብዛኛው ሴቶች ቅቤ ይቀባሉ፡፡ ይህም ቅቤ በመቀባት የፊትን ወዝ እንዲጨምር እና በአናታቸው ቅቤው በመግባት ከእራስ ምታት ህ መም ስለሚያድናቸው ነው፡፡ (ደጅይጥኑ ምናለ ቃለ መጠይቅ መጋቢት 16 /2004 ዓ.ም)

በአሁኑ ጊዜ የውቅራት አጊያጊያጥ በእጅጉ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ይህም የሆነው በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት እና በተለያዩ የሚዲያ ሽፋኖች አማካይነት ውቅራት አጉል ባህል ነው እየተባለ ስለሚሰበክ ነው፡፡

## 4.3. የባንጃ ሃገረሰባዊ ልብሶችና ጌጠጌጦች ፋይዳ

በዚህ ክፍል የባንጃ ሀገረሰባዊ ልብሶች በሚይዙት ትዕምርት አማካይነት በሚያስተላልፉት መ ልእክት የሚገልፁትን ማህበራዊ ፋይዳዎች ይዳስሳል፡፡ ይህም በተለይ በFleming የትኩረት አ ቅጣጫዎች ውስጥ አምስተኛው በሆነው አገልግሎት ላይ ያተኩራል:: በዚህም አስቀድሞ ቁሱ ከ ተሰራበትና በግልፅ ከሚታየው አገልግሎትን (Intended Function) ከማየት ባሻገር ቁሱ ከዚ ህ ተግባሩ በተጨማሪ ቁሱ ከተገኘበት የባህል ገፅታዎች አንፃር ሲታይ የሚሰጠውን አገል ግሎትንም (Unintended Function) ያጠቃልላል:: የባንጃ ሀገረሰባዊ ልብሶችና ጌጣጌጦች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሲሆን በዚህ መሰረትም ከትንተናው ለማሳያነት በተመረጡ ሃገረሰባዊ ልብሶችና ጌጣጌጦች ይቀርባሉ፡፡ በዋናነትም ዕድሜን የመግለፅ፣ ማህበራዊ ደረጃን የማሳወቅ፣ ከእርኩስ መንፈስ ለመጠበቅ፣ እናትነት ለማሳየትና ማህበራዊ ሁነቶችን የማሳወቅ ፋይዳ አላቸው፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ይተነተናሉ፡፡

### 4.3.1 ዕድሜን መግለፅ

ሃገረሰባዊ ልብሶችና ጌጣጌጦች ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንዱ የለባሹንና ያጌጠውን እድሜ ማመልከት ነው:: በተለይ በሴቶች ልብሶች፣ የፀጉር አሰራርና ጌጣጌጦች ውስጥ በጉልህ ይታያል። የሴቶችን የእናትነት ሁኔታ በባንጃ ሃገረሰባዊ ልብሶችና ጌጦች እንዴት እንደተገለፀ ስናይ ከወንዶች የተለዩ ነው::

የሴቶችን እድሜ ገላጭነት ከሚያሳዩ የብሄረሰቡ አጊያጊያጥ ውስጥ የፀጉር አለጫጨት አን ነው። "ሳዱላ" በመባል የሚታወቀው የፀጉር አሰራርና ክርክም ተጠቃሾች ናቸው:: ይህን የፀጉር አለጫጨት የሚላጩ ሴቶች ያገቡና ልጅ የወለዱ ናቸው።

እንዲሁም ሙሉ በሙሉ "ጋሜ ቅርድድ" የሚባለው የፀጉር አለጫጨት አይነት ይጠቀሳል:: ከትንተናው በሰፊው እንደተገለፀው ደግሞ "ጋሜ" የሚባለው የፀጉር አሰራር አይነት የሚሰሩት ያላገቡ ወይም ደግሞ ያልወለዱ ሴቶች ናቸው። ከዚህ መገመት እንደሚቻለውም በአብዛኛው ይህን የፀጉር አሰራር የሚሰሩ ሴቶች ወጣቶች ናቸው። በዚህ የፀጉር አለጫጨት መሰረት የሴቶች የዕድሜ ሁኔታ ምን እንደሆነ በቀላሉ ማወቅ ይችላል።

ወንዶች እድሜያቸው ሲገፋ የሚያደርጓቸው አልባሳት የእድሜ ሁኔታ ከማሳየቱ በተጨማሪ የክብር መግለጫ ሁነው ይወሰዳሉ:: ከዚህ በተጨማሪም ጋቢ በሽማግሌዎች የሚደረግ ሃገረሰ ባዊ ልብስ ሲሆን በተለይ ሽማግሌዎች ለእርቅ እና ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ሲሄዱ የሚያደርጉ ትና የሚያዘወትሩት በመሆኑ ዕድሜ አመላካችነቱ የጎላ ነው። እርጅናን ከሚያሳዩ የተለያዩ ሃገረሰባዊ ልብሶች በተጫማሪ ወጣትነትን የሚጠቁሙም የተለያዩ ልብሶች ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ ሽብሽቦና የወንዶች ቁምጣ ሱሪ ተጠቃሽ ናቸው።

### 4.3.2 ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት

ሃገረሰባዊ ልብሶች ማህበራዊ ደረጃንና ሃብት ደረጃን ሀብትን ያሳያሉ:: ማህበራዊ ደረጃን ማሳየት ሲባል በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ማህበራዊ ልዩነት ማለትም የሃብት የስልጣንና የመሳሰሉትን ልዩነቶች የሚያጠቃልል ሲሆን የባንጃ ማህበረሰብ ሃገረሰባዊ ልብሱ በያዙት ትዕምርት

ከሚያስተላልፉት መልዕክት አንደኛው ልዩነትን ማሳየት ነው። ይህም በተለይ በጌጣጌጦች ላይ ጎላ ብሎ ይታያል።

ማህበራዊ ደረጃን ከሚያሳዩ የባንጃ ሃገረሰባዊ አጊያጊያጥ መካከል "ብር ቅጥል" አንዱ ነው። ይህ የአንገት ጌጥ በጣም ውድ በመሆኑ የሚያደርጉት ሰዎች የታዋቂ ሰው ሚስቶች እንዲሁም በኢኮኖሚ ደረጃቸው ከፍ ያሉ ሴቶች ናቸው። ይህን የአንገት ጌጥ የምታደርግ ሴት በተመልካቹ ልቦና ስለምንነቷ በቀላሉ ታሳውቃለች:: በአጠቃላይ እነዚህ ሃገረሰባዊ ልብሶች እና ጌጣጌጥ በማህበረሰቡ መካከል ያለውን የማህበራዊ ደረጃ ልዩነት በማሳወቅ በተመልካቹ እና በለባሹ መካከል መግባባትን ይፈጥራሉ::

## 4.3.3 ከእርኩስ መንፈስ ለመጠበቅ

ጠገራ ብር የሀብት መገለጫ ምልክት ተደርጎ እንደሚወሰድ ሁሉ ከእርኩስ መንፈስ መከላከያና ማባረሪያም ሆኖ ያገለግላል። ይህንን ፋይዳ ከያዙት ሃገረሰባዊ ጌጣጌጦች መካከል ከብርቅጥል የሚሰራ ጌጥ አንዱ ነው:: በመሆኑም ይህ ጌጥ ምንም እንኳን ለማጌጥ ወይም እናትነትን እና ወጣትነትን ለመግለፅ ቢሆንም ተጨማሪ ተግባርንም የያዘ ነው:: ከብር የሚሰራ ጌጥ ማህበረሰቡን ከእርኩስ መንፈስ ለመጠበቅ የሚረዳና በዚህም የተከላካይነት ተግባርን የማስፈፀም ፋይዳ ያለው በመሆኑ ለልጆች እንኳን በትንሽ መስቀል አማካይት ይሰራላቸዋል። እንዲሁም በልብስ በኩል ደግሞ ለጤና ተብለው የሚሰሩ ልብሶች ተጠቃሾች ናቸው።

## 4.3.4 እናትነትን ማሳየት

በአዊ ብሄረሰብ አንዷት ሴት ወደ እናትነት ስትሸጋገር ‹‹ጋሜ›› ስተሰራው የነበረው ፀጉሯ ወደ ‹‹ሳዱላ›› ይሸጋገራል። እንዲሁም ሳዱላዋ እየጠበበች ከደፈነች በኋላም ሙሉ ጸጉሯን ትከረከማለች። ይህ ሙሉ ክርክምም እናትነቷን የሚያሳይና ሁለትና ሶስት ልጆች መውለደዋን የሚያመላክት ነው። ስለዚህ ሳዱላ እና ሙሉ ክርክም የተሰራች ሴት እናት መሆኗን ወይም ልጅ እንዳላት ከማህበረሰቡ ጋር ትግባባለች። ማንም የማህበረሰብ አባል ይህን አይቶ የተሰሪዋን እናትነት ማወቅ ይችላል።

### 4.3.5 ማህበራዊ ሁኔታዎችን መጠቆም

ማህበራዊ ሁነቶች ሲባል በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ አጋጣሚዎችን ማለትም ሀዘን፣ ሰርግ እና የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው። በባንጃ ማህበረሰብ እነዚህን ማህበራዊ ሁነቶች ለማሳወቅ ሃገረሰባዊ ልብሶቹ የራሳቸው የሆነ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በአዊ ባህል መሰረት ጥቁር የሃዘን ቀለም ተደርጎ ይወሰዳል። አንድ ሰው ሲሞት በባትሪ ድንጋይ ከሰልና በጥቁር ካርቦን ተዘፍዝፎ ጨርቅነት ያላቸውን ልብሶች ይነከራሉ። እነዚህ የተነከሩት ልብሶችም ወደ ጥቁርነት ይቀየራሉ። በመሆኑም የሃዘን መግለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። የቅርብ ዘመድ ሲሞት የቤተሰቡ ጸጉር የሚላጭ ሲሆን እናቶችም ፊታቸውን (በተለይ ጉንጫቸውን) በሸክላ ስባሪ ይነጩታል። ይህ የመላጨት እና ፊት የመንጨት ጉዳይ የሟችን የቅርብ ዝምድናን ያመለክታል። (አቶ አስማማው በለው፣ መጋቢት 24 2004 ዓ.ም)

ሌላው በባንጃ ማህበረሰብ ውስጥ ከሚከሰቱ ማህበራዊ ሁታዎች ውስጥ በሃገረሰባዊ ልብሶቹ የሚገለጹት በሙሽርነት ጊዜ ነው። ይህም ሴቷ ሙሽራና ወንዱ ሙሽራ ካቦርት የሚባለውን ሃገረሰባዊ ልብስ ይለብሳሉ። በዚህ ወቅት ወንዶች የሙሽርነት ጊዜያቸው እንደሆነ ማህበረሰቡ በቀላሉ ያውቃል። ሃገረሰባዊ ልብሶች በማህበረሰቡና በለባሹ መካከል ቃላዊ ባልሆነ መንገድ ተግባቦትን የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን አመላካች ነው።

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት በባንጃ ወረዳና አካባቢዋ ያሉ ማህበረሰቦች ምን ምን ልብሶችንና ጌጣጌጦችን እንደሚጠቀሙ፤ ልብሶቹና ጌጣጌጦቹም ያሏቸው ባህላዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ምን ምን እንደሆኑ መርምሮ ለማወቅ ገላጭ የምርምር ስልት ተግባር ላይ ውሏል። የባህላዊ ልብሶችን፣ ጌጣጌጦቹን እና የማህበረሰቡን የፀጉር አሰራር፤ የንቅሳት (ውቅራት) መልክ ማሳየት፤ የአለባበስ ስርዓቱን እና አጋጣሚዎቹን መግለፅ፤ እንዲሁም ልብስ እና የጌጣጌጦቹን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት የሚሉን ዑሳን ዓላማዎችን ዳሷል:: የጥናቱን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የመስኩ ምሁራን የሰነዘሯቸውንን ድፈ ሀሳቦች ተቃኝተዋል። በመስክ ስራ በተደረገው ቆይታም መረጃዎቹ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታና በቡድን ተኮር ውይይት ተሰብስበዋል። በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችም ተተንትነው ውጤታቸው በሚከተለው ሁኔታ ተጠቃሎ ቀርቧል።

በዚህ አማካይነትም የፀጉር አለሜጨት እንደ አለሜጨት አይነቱ በሶስት፣ ልብሶች እንደለባሾቹ ፆታ በሁለት እና ጌጣጌጦች እንደሚደረጉበት የሰውነት ክፍል በአምስት ተመድበዋል:: በአጠቃላይ በትንተናው ሶስት የፀጉር አሰራር፣ አስር ልብሶችና ስድስት የጌጣጌጥ አይነቶች ተካተዋል:: በዚህ መሰረት ልብሶቹ ከቆዳ፣ ከጥጥ፣ ከክር እና ከፋብሪካ ውጤት ከካኪ የሚሰሩ ሲሆኑ ጌጣጌጦቹ ደግሞ ከብር፣ ከብርጭቆ ስባሪ፣ ከነሃስ፣ ከብረት እና ከኒኬል የሚሰሩ ናቸው:: እነዚህ ሃገረሰባዊ ልብሶች እና ጌጣጌጦች እንደየ እድሜ ደረጃ፣ እንደየ ፆታ፣ እና ማህበራዊ ደረጃ የአለባበስ ስርዓቱ እንደተለያየ ጥናቱ ያመለክታል::

ወንዶቹም ሆኑ ሴቶች ሀገረሰባዊ ልብሶችን የሚለበሱባቸው ጌጣጌጦችንም የሚያጌጡባቸው አጋጣሚዎች በዝክር በዓላት፣ በሰርግ፣ በማህበራዊ አጋጣሚዎች፣ በገበያና በመሳሰሉት ናቸው። በእነዚህ አጋጣሚዎች ልብሶችን በመልበስ ጌጣጌቶችንም በማድረግ ወንዱ ለሴቷ ሴቷም ለወንዱ ውስጣዊ ስሜታቸ የሚገልጹ ቃላዊ ግጥሞችን ያቀነቅናሉ።

ልብሶች በተለያዩ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ አጋጣሚዎች የሚደረጉ ሲሆን የተለያዩ ለውጦችን እያስተናገዱም ይገኛሉ:: እነዚህ የለውጥ ሂደቶች በአብዛኛው ከመሰሪያ ቁሶች መለወጥ እስከ መጥፋት ድረስ ያለውን ያጠቃልላል። (ይህ በተለይ በጌጣጌጦችና በፀጉር አለሜጨት እንዲሁም ንቅሳት ላይ ይበረታል):: ለዚህ እንደ ዋና ምክንያትነት የሚጠቀሱት ደግሞ የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት አንዱ ነው::

የባንጃ ሃገረሰባዊ ልብሶች በዋናነት ከሚሰጡት አገልግሎት ገፅታዎች አንፃር ሲታዩ በሚያስተላልፉት መልዕክት የተለያዩ ማህበራዊ ፋይዳዎች አሏቸው:: በዚህ መሰረትም በማህበረሰቡ እድሜን በማሳወቅ፣ የተለያዩ ማህበራዊ ደረጃዎች በማሳየት፤ ከእርኩስ መንፈስ ለመጠበቅ፤ እናትነትን ለመግለፅ እና በማህበረሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ማህበራዊ ሁኔታዎችን በማሳወቅ ትልቅ አስተዋፆ አላቸው:: በተጨማሪም ከሰውነታቸው ላይ የተለያዩ አይነት ንቅሳቶችን (ውቅራቶችን) በመወቀር ከማጌጫነት በተጨማሪ ለተለያዩ በሽታዎች መፈወሻነትም ያገለግላሉ፡፡

በመጨረሻም በዞኑም ሆነ በወዳው ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ሲካሄዱ የአዊ ባህል ቡድን አባላት ሀገረሰ ባዊ ልብሶችን ለብሰው ጌጣጌጦቹንም አድርገው ባህሉን ሊያንጸባርቁ የሚችሉ የግጥም፣ድራማ ዝግ ጅቶችን ቢያቀርቡ መልካም ነው፡፡ እንዲሁም ለእደ ጥበብ ባለ ሙያዎች የወረዳው ባህልና ቱሪዝ ም ጽ/ቤት ስልጠናና ድጎማ በመስጠት ፤ባዛሮችን በማዘጋጀት እገዛ ቢደረግላቸውና ማህበረሰቡ ለባለሙያዎቹ ያለውን አሉታዊ አመለካከት እንዲቀየር የግንዛቤ ማስጨበጫ ቢሰጥ እላለሁ፡፡

በዞኑና በወረዳው ያሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች እንዲሁም የሚዲያ ተቋማት ማህበረሰቡ ቁሳዊ ባህሉን እንደጠበቀ ዘመናዊ ትምህርቱንም ሆነ አስተሳሰቦችን መተግበር እንዲችልና የሚችል መሆኑንም በተከታታይ ቢያስተምሩ

# የአማርኛ ዋቢ ምንጮች


ሄለን አላምረው። "ባህላዊ ሽመናና የቆዳ ስራ በደምበጫ አካባቢዋ።"ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፤ የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም።

ሰይድ ይማም፤ "በከሚሴ ከተማ ዙሪያ በሚገኙ ገጠር አካባቢዎች የወጣት ወንዶችና ሴቶች አለባበስና አጊያጊጥ"፤ የኤም. ኤዲግሪ ማሟያ ጥናት፤ ኢትዮጵያ ቋንቋ ዎች እና ስነፅሑፍት ምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002 ዓ.ም።

አያል አድማሱ ፤ "የጎጃም አካባቢ የአልባሳት ስያሜ"፤ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጥናት፤የኢትዮጵያ ቋንቋዎችእና ትምህርት ክፍል፤አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1992 ዓ.ም።

አያሌው ሲሳይ። *የአገው ህዝቦችና የዛግዌ ስርወ መንግስት ታሪክ።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1995 ዓ.ም።

አለም እሸቱ። *መሰረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ።* አዲስ አበባ፣ ቅድስት ማሪያም ኮሌጅ የሊብራል አርትስ ፋክልቲ፣ 1992 ዓ.ም።

አስቴር ሙሉ። "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ዐቢዩ አስማማው፤ "የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን አርጎባ ልዩ ወረዳ"፤ የኤም. ኤዲግሪ ማሟያ ጥናት ኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ባንጃ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት። ‹‹አዱክ›› ቁ1፤ ባንጃ፣ 2003።

ባንጃ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት። ‹‹አዱክ›› ቁ2፤ ባንጃ፣ 2004።

አዊ ብሄረሰብ አስተደሰደር ምክር ቤት። ‹‹አዊ የባህል ፌስቲቫል›› እንጅባራ፣ 2004ዓ.ም።

የአዊ አስተዳደር ዞን የወጣቶች ባህልና ጉዳይ መምሪያ፣ የስነ ልሳን ክፍል። "የስነቃል ስብስብ"። እንጅባራ፣ 1997 ዓ.ም።

የኔአለም አረደ፤"የአርሲ ሴቶች ጌጣጌጥ ጥናት በኮኮሳና ገደብህሰሳ ወረዳዎች" ፤የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥት፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፤ አዲስ አበ ባዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም።

ያሬድ ተፈራ፣ "በሰቆጣና በአርገሌ ገጠራማ ወረዳዎች የሴቶችና የወንዶች የአለባበስና የአጊያጊያጥ ማህበራዊ እሴቶች" ፤የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ፅሑ ፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ውብሸት አሰፋ፣ "የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥስሞች በአማራው ክልል"፣ የባችለርዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ የኢትዮጵያቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1972 ዓ.ም፡፡

ዋልተንጉስ መኮንን፣ "የሽመናና የጥልፍ ትውፊት በአክሱም"፣ የኤም. ኤዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ 2000 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የሥነ_ቃልመምሪያ*፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፣ 19991 ዓ.ም፡፡

## የእንግሊዝኛ ዋቢ ምንጮች

Beals, Rarph L. and Hoijer Harry. *An Introduction to Anthropology*: New York: Los Angeles: University of California. The Macmillan Company Led. 1959.

Best, J.w. *Research in Education*, New Delh, Prentice Hall of India privatelimited, 1981.

Clark, Gahame. *Symbols of Excellence.*London:Cambridge University. Press.1986.

Dorson, M.Richard (ed.); *Folklore and Folk Life*: An Introduction.Chicago and London; The University of Chicago press 1972.

*Encyclopedia Americana.* V.7, USA: Scholastic Library Publishing Inc. 2006.

Evans,Joan. *A History ofJewelry 1100-1870.* Boston Book and Art. Publisher.1970.

Fekade Azeze. *The State and oral Literature in Ethiopia: Retrospect and prospects.* A. paper presented to the plenary session of XIV international conference Ethiopian studies. November 6-11, Addis Ababa, Ethiopia, Published in JES, 2001.

Fekade Azeze, *"Teaching Material Selected and Compalied; Reader for Etli 621".* Department of Ethiopian Language and Literature, M.A in Ethiopian Literature and Folklore, 2003.

Fleming, E. McClung. "Artifact Study: A Proposed Model." Online at:URL: *http://WWW,Jstor.org/stable/118052.*1974.

Georges, Roberts. A. and Michal Ownjones. *Folkloristic:An introduction.* USA: Indiane University. 1995.

Glassie, Henry. *Material Culture.* Bloomington and Indianapolis. Indian. University Press;1999.

Goldstein, s.Kenneth. *AGuide For Field Works in Folk lore Pennysylvania*: Gale Research company,1974.

Goldstein, S.Kenneth. AGuide For Field workers in Folk lore. *"The American Folklore Society." Folklore Associates. Inc. 1964.*

http://www.Jstor.org/Jewellery. (accessedon January 7, 2012).

Michael ,John. "Material Culture". *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art.* USA. Thomas A. Green(ed.). ABC-CLI Inc.,(1997);145-151.

Prown, Jules David. "Mind in Matter" *An Introduction to Material Culture Theory and Method.* On line Availble at: WWW.http:// Jstor org/ about/ terms/ Html. 1982.

Prown, Jules. "Mind in Matter:" *An Introduction to Material Culture Theory and Method.* Interpreting Objects and Collections. Susan M. Pearce(ed.). routledge; (1994), 67-75.

Prown,David. "Mind in matter": An Introduction to Material Culture Theory and Method: http://www.Jstor. Org/aboutterms.htm 1982. (accssed on march 21,20012)

Roberts, E warren. "Folk Crafts" *In Folklore and Folk life: An Introduction.* Dorson, Richard's ed; Chicago and London; The University of Chicago press. 1972.

Schlereth,J Thomas. "*Materal Culture Research and Historical Explanatin.*" Online. Available at: http://www .Jst Or.org/stable/3377 54 81,1985.

Schlerth, Thomas "*Understanding The Nine Models of Material Culture Interpretation.*" On line available at: http://www Btneporg/1985 . (Accessed on November. 1, 2011).

Sims, Martha C. and Martine Stephen. *Living Folklore*: an Introduction to the study of People and Their Tradition. Logan, Utah. Utah state University Press, 2005.

*The New Encyclopedia Britannica,* USA: Encyclopedia Britannica Inc. 2005.

Vlach, John Michael. "Folk Crafts Men." *In Hand Book of American Folklore.* Richard M. Dorson (ed). Bloomington; Indiana University press, 1983.

Wilson, Kathryn. “Costume, Folk” ”.Folklore An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music and Art. Thomas A.Green(ed.). USA. ABC-CLIO Inc., (1997); 145-151.

Wilson,William A-.”Documenting folklore” in Elliot oring (ed). Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Longman, Utah state University Press. (1989).

Yoder, Don. “Folk Costume”. *In Folklore and Folk life: An Introduction.* Richard Dorson(ed.). Chicago; University of Chicago, 1972

# አባሪ 1

## ለተለያዩ መረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች

### 1.ግላዊ መረጃዎችን ለማግኘት

1. ሙሉ ስምዎትን ቢነግሩኝ?
2. የትውልድ ስፍራ?
3. እድሜዎ ስንት ደርሷል (መቼ ተወለዱ)?
4. እየተከተሉ ያለው ሀይማኖት ምንድን ነው?
5. ስለቤተሰብዎ ሁኔታ ቢነግሩኝ? አግብተዋል? ልጆች ወልደዋል? ስንት ልጆች?
6. ትምህርት ተምረዋል?
7. መተዳደሪያዎ ምንድን ነው?
8. የመኖሪያ ስፍራዎ የት ነው? ምን ተብሎ ይጠራል?
9. በማህበረሰቡ (በስራ ያለዎት ቦታ (ድርሻ) ስልጣን ምንድን ነው?

2. አካባቢያዊና ባህላዊ መረጃዎችን ለማግኘት የቀረቡ ጥያቆዎች

1. በአካባቢው የተለመደው ባህላዊ አለባበስ እና አጊያጊያጥ ምን አይነት ነው?
2. ልብሶቹ እና ማጌጫዎቹ ምን እየተባሉ ይጠራሉ? ስያሜያቸውስ? ከምን ጋር የተያያዘ ነው?
3. ልብሶቹ እና ማጌጫዎቹ ከምን ይሰራሉ? ተምሳሌታቸውስ ምንድን ነው?
4. ልብሶቹና ማጌጫዎቹን ማን ይሰራቸዋል?
5. ልብሶቹ እና ማጌጫዎቹ በምን አጋጣሚ እና ወቅት የሚለበሱና የሚደረጉ ናቸው? እንዴት ይደረጋሉ?
6. ወጣቶች ምን ይለብሳሉ? በምን ያጌጣሉ? በምን መልኩ? ለምን በዘህ መልኩ ብቻ?
7. ያገቡ ሴቶች እና ወንዶች ምን ይለብሳሉ? በምንያጌጣሉ? በምን መልኩ? በዚህ መልኩ ለምን?
8. በእድሜ የገፉ እናቶች እና አባቶች ምን ይለብሳሉ? በምን ያጌጣሉ? በምን መልኩ? በዚህ መልኩ ብቻ ለምን?

9. በብዓላት ወቅት የሚለበሱ ልብሶች እና ማጌጫዎች ምን አይነት ናቸው? ከብዓል ብዓልስ ይለያያሉ?
10. በሀዘን ወቅት ምን ይለበሳል?
11. የአዘቦት ልብሶች ምን ምን ናቸው? በምን መልኩ ይለበሳሉ?
12. በነጠላ፣ በቀሚስ በኩታ በጋቢ በመቀነት ወዘተ. ላይ የሚደረጉ አዳይቶች ቀለማቸው ምን ምን ናቸው? ቀለም ባይኖረውስ? ከልብስ ልብስስ ይለያያሉ? ለምን?
13. ንቅሳት (ውቅራት) ለምን ይደረጋል? በየትኛው የሰውነት ክፍል ላይ ይደረጋል? በእድሜ ደረጃስ ይለያያሉ? ለተነቀሱት ቀደም ባለው ጊዜ ይሰጥ የነበረው ቦታ ምን ይመስል ነበር? አሁንስ?
14. የወንዶች ጸጉር በምን መልኩ ይያዛል? ይቆረጣል? ይላጫል? ምን ይቀባል? በዚህ መልኩ ለምን?
15. የሴቶች ጸጉር በምን መልኩ ይሰራል? ህጻን እያለች ፣ልጃገረድ እያለች ፣ በእድሜ ስትገፋ ምን  ምን ጸጉር አሰራሮችን ትከተላለች? በዚህ መልኩ መሰራቷ ምንን ያመለክታል?
16. የልብስ ቁልፍ በልብሱ ላይ የሚደረገው ለምንድን ነው? የሚደረግበት ቦታስ? የት ነው? ለምን? እንዲህ መደረጉስ መቼ ተጀመረ?
17. ልብሶቹ የሚሰፉት በምን መልኩ ነው? ለምን? ጨርቆችስ ምንድን ናቸው?
18. ልብሶችንና ጌጣጌጡን እነማን ይሰሯቸዋል? የአሰራር ሂደታቸው ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ለእነዚህ ሰዎች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
19. ስለ ልብሶቹ እና ማጌጫዎች ስለ ባለሙያዎች ወይም ከሌላ ሁኔታና ድርጊት ጋር ተያይዘው ስለነዚህ የተዘፈኑ ዘፈኖች የተባሉ ግጥሞች የተነገሩ ተረቶች ወዘተ. ካሉ ቢነግሩኝ?
20. በእርስዎ ጊዜ ልብሶቹ እና ማጌጫዎቹ የተለወጡበት ሁኔታ አለ? ምክንያቱ ምንድን ነው? እንዳይለወጡ ማድረግ አይቻልም ነበር?
21. ባህላዊ ልብሶቹን እና ጌጣጌጦቹን በማየት የሰዎችን የኑሮ ደረጃ መገመት የሚቻልበት ሁኔታ ነበር? አሁንስ?
22. የአዊ ባህል ልብሶች እና ጌጣጌጦች ባህላዊነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

3. ሙያውን እና የገበያውን ሁኔታ ለማወቅ የቀረቡ ጥያቄዎች

1. በምን ሙያ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታወቃሉ?
2. ሙያውን ከማን ተማሩት? መቼ? በምን አይነት መንገድ እና ሁኔታ?
3. የሚሰሩባቸው ቁሶች ምን ምን ናቸው የአሰራር ሂደታቸው እንዴት ነው?
4. ልብሶችን እና ጌጣጌጦችን የሚሰሩዋቸው በትዕዛዝ ነው? ወይስ በራስዎት ፍላጎት እየሰሩ ገበያ ለማቅረብ?
5. ይህ ቁስ በምን ያህል ዋጋ ይሸጣል?
6. ቁሶቹ ይበልጥ የሚሸጡበት ወቅት አለ?
7. ልብሶችንም ሆነ ጌጣጌጦቹን የሚገዙት ምን አይነት የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው? ማህበረሰቡ ይሄነው ትክክል ያለው ምርጫ አለ?
8. ልብሶችንም ሆነ ጌጣጌጦችን የሚገዙት ምን አይነት የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው?
9. ወጣቶቹ ልብስ ለመግዛት ሲመጡ መምረጫ መስፈርታቸው ምንድን ነው? የማህበረሰቡ ምርጫ ይጠበቃል?
10. የገበያው ሁኔታ ቀደም ባለው ጊዜ ምን ይመስል ነበር? አሁንስ? ለምን?
11. ስራው በህወትዎ ላይ ያመጣው ለውጥ አለ?
12. ይህን ስራ በመስራትዎ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያሰጥዎት ክብር ምን ይመስላል?
13. እርስዎስ ቀደም ባለው ጊዜ ከማህበረሰቡ ጋር የነበረዎት ግንኙነት የት ድረስ ነበር? አሁንስ?

ለተተኳሪ ቡድን ውይይቶች

1. በአካባቢው የተለመዱት ባህላዊ አለባበስ እና አጊያጊያጦች ምን አይነት ናቸው? በሚደረጉበት አጋጣሚ በጾታ በቀለም በሚሰሩበት ቁስ እና በአሰራራቸው ወዘተ. ይለያያሉ? በምንስ ይለያያሉ?
2. ልብሶችና ማጌጫዎቹ ምን እየተባሉ ይጠራሉ? ስያሜያቸውስ ከምን ጋር የተያያዘ ነው?
3. ልብሶቹን እና ጌጣጌጦቹን እነማን ይሰሯቸዋል? የአሰራር ሂደታቸው ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ለእነዚህ ሰዎች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
4. ስለ ልብሶቹ እና ከባለሙያዎች ሁኔታና ድርጊት በተመለከተ ተያይዘው የተባሉ ግጥሞች ዘፈኖች ካሉ

# አባሪ 2

## የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ/ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | ስራ | የመኖሪያ አድራሻ | ቃለመጠይቅ የተካሄደበት ቦታ | መረጃው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አብታም ምናለ | 49 | ወ | አርሶ አደር | ቅዳማጃ | በቅዳማጃ ቀበሌ ቅጥር ግቢ ውስጥ | መጋቢት 18 2004 ዓ.ም |
| 2 | ሻሽቱ በዜ | 52 | ሴ | ነጋዴ | ባንጃ | በባንጃ ወረዳ በቤት ውስጥ | ጥር 16 |
| 3 | ጽሀነይሽ አበራ | 61 | ሴ | አርሶ አደር | ባታማሪም ቀበሌ | ባታማሪም ቀበሌ | ጥር 16 |
| 4 | ደጅይጥኑ ምናለ | 43 | ሴ | አርሶ አደር | ባንጃ ወረዳ | በባንጃ ወረዳ በ ቤት ውስጥ | የካቲት 25 መጋቢት16 ጥር14 |
| 5 | ፈለጉሽ ብርሌ | 62 | ሴ | አርሶ አደር | ቸውሳ ቀበሌ | ቸውሳ ቀበሌ | መጋቢት17 |
| 6 | አቶ አሳቤ ሙሉ | 36 | ወ | የባንጃ ወረዳ ባቱጽ/ቤት ሰራተኛ | ባንጃ ወረዳ | ባንጃ ወረዳ ባ/ቱ/ጽ/ቤት | መጋቢት15 መጋቢት15 ጥር12 |
| 7 | የክትነሽ አበራ | 71 | ሴ | ነቃሽ | ባታ ማሪያም | ባታ ማሪያም ቀበሌ | ጥር 16 የካቲት2 |
| 8 | ከተማ ቢተው | 47 | ወ | አንጥረኛ | ባንጃ ቀበሌ | ጌጣጌጥ እየሰሩ | መጋቢት 18 የካቲት2 |
| 9 | አቶ አስማማው በለው | 49 | ወ | የሽመና ባለሙያ | ባንጃ ወረዳ | በሽመና ስራ ላይ | መጋቢት17 |
| 10 | ጽሀይነሽ አበራ | 56 | ሴ | ነቃሽ | ቸውሳ ቀበሌ | ቸውሳ ቀበሌ | ጥር19 |
| 11 | የክትነሽ አበራ | 71 | ሴ | ነቃሽ | ባታ ማሪያም ቀበሌ | ባታ ማሪያም ቀበሌ | የካቲት2 ጥር16 |
| 12 | አባ ያየህ ሙሴ | 57 | ወ | አንጥረኛ | ቸውሳ ቀበሌ | ቸውሳ ቀበሌ ጌጣጌጥ በመስራት ላይ | መጋቢት 18 |
| 13 | ቢተው ወንዳገኘሁ | 54 | ወ | አርሶ አደር | ባታ ማሪያም | ባታ ማሪያም ቀበሌ | ጥር17 |
| 14 | አቶ ከተማ ቢተው | 47 | ወ | አንጥረኛ | ባንጃ ወረዳ | ባንጃ ወረዳ ጌጣጌጥ እየሰሩ | መጋቢት18 |
| 15 | ሀይለየሱስ አበራ | 34 | ወ | ባ/ወ/ባ/ቱ/ጽ/ቤት ሰራ ተኛ | ባንጃ ወረዳ | ባ/ወ/ባ/ቱ/ጽ/ቤት | ጥር12 መጋቢት7 |

## የረዳት መረጃ አቀባዮች

| ተ/ቁ | ስም | እድሜ | ጾታ | ስራ | የመኖሪያ አድራሻ | ቃለመጠይቅ የተካሄደበት ቦታ | መረጃው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቡኔ ተፈራ | 43 | ሴ | አረሶ አደር | ቸውሳ ቀበሌ | በቸውሳ ቀበሌ ቅጥር ግቢ | የካቲት25 |
| 2 | ብርቱካን አካሉ | 38 | ሴ | አርሶ አደር | ቸውሳ ቀበሌ | ቸውሳ ቀበሌ ቅጥር ግቢ | መጋቢት10 |
| 3 | አዲሱ መንገሻ | 38 | ወ | የባ/ቱ/ስራተኛ | ባንጃ ወረዳ | ባ/ወ/ባ/ቱ/ጽ/ቤት/ቢሮ ውስጥ | ጥር 13 |
| 4 | ቢተው ወንዳገኘሁ | 54 | ወ | አርሶ አደር | ባታማሪያም | ባታማሪያም ቀበሌ ቅጥር ግቢ | ጥር17 |
| 5 | ልመንህ ያየህ | 45 | ወ | የሽመና ባለሙያ | ባታማሪያም ቀበሌ | በሽመና ስራ ላይ እያሉ | የካቲት 2 |
| 6 | እታገኘሁ ታፈረ | 62 | ሴ | ልብስ ጠላፊ | ባንጃ ወረዳ | በቤቷ ውስጥ | የካቲት 28 |

# አባሪ3

## ልብሶች ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር

| ተ/ቁ | የአልባሳቱ ስም | አጫጭር መግለጫዎች |
|---|---|---|
| 1 | ጋቢ | ከወገብ በላይ የሚደረብ መስሪያ ቁሱ ፈትል ሲሆን በእድሜየገፍ እናቶችና አባቶች ይለብሱታል |
| 2 | ለምድ | ከወገብ በላይ የሚደረብ ከበግቆዳ በቤትውስጥ የሚዘጋጅ ሲሆን በእረኝነት ጊዜና በግብርና ስራ ወቅት የረደረባል፡፡ |
| 3 | መቀነት | በወገብ የሚታሰርበፈትል ወይም ፈትልና ዝሀ ይሠራል በአብዛኛው ያገባች ሴትየምታስረው ሲሆን የመለበሻ አጋጣሚው ቀንሷል |
| 4 | ሽብሽቦ | ወጣቶች የሚለብሱት ሲሆን ከፋብሪካ ውጤት ከተመረተ ከካሽሚርና ካኪ የሚሰፋ ነው፡፡ |
| 5 | ቁምጣ | እረኛችየሚጠቀሙበት ሲሆን ከእግራቸው ከጭናቸው በላይ ጠበብ አድርገው የሚያሰፉትነው፡፡ ጥሬ ዉሱም የፋብሪካ ውጤት ነው፡፡ |
| 6 | ጉንፍ እና ጎዶ ቀሚስ | ከጋብቻ በኋላ እናቶች የሚለብሱት ሲሆን ሙሉ በሙሉ በቤት ውስጥ ፈትል ይዘጋጃል |
| 7 | የጤና ልብስ | በሁለቱም ጾታዎች በኩል ለበሽታ መፈወሻነት የሚዘጋጅ ነው |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ጌጣጌጦች ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር

| ተ/ቁ | የጌጡ ስም | አጫጭር መግለጫዎች |
|---|---|---|
| 1 | ትልቅ መስቀል | በአንገት ላይ የሚደረግ ሲሆን ከብርየሚሰራ ነው፡፡ በሚሰራበት ቁስ ለውጥ ታይቶበታል፡፡ |
| 2 | ጉትቻ | አግብታ የወለደች ታደርገዋለች፡፡ |
| 3 | ድሪ | በአንገት የሚደረግ ሲሆን ከብር በመሰራት እናቶች ሲያደርጉት በሚሰራበት ቁስ ለውጥ ተደርጎበታል፡፡ |
| 4 | አልቦ | እናቶች የሚያደርገት ሲሆን ከብር የሚሰራና መደረጉ እየቀነሰ የመጣ ነው፡፡ |
| 5 | አምባር | ሴቷ ካገባች በኋላ የምታደርገው ሲሆን በመስሪያ ቁ ሱ በሚደረግበት ቦታና ቁሱ በሚሰራበት ላይ ለው ጥ ተገርጎበታል፡ |
| 6 | እርባን | እናቶች የሚያደርጉት ነው፡፡ |
| 7 | ብር ቅጥል | ከልጅ አስከ እናቶች ድረስ የሚደረግና ከክፉ መናፍስት ይጠብቃል ስለሚባል መስሪያ ቁሱ ላይ ለውጥ አልተደረገበትም፡፡ |

## ውቅራትና የጸጉር አለጫጨት ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር

| ተ/ቁ | የአለጫጨቱ አይነት | አጫጭር መግለጫዎች |
|---|---|---|
| 1 | ጋሜና ቁንጮ | በቤት ውስጥ ይሰራል የሴት ህጻናት አለጫጨት ነው፡፡ ለውጥም እየተደረገበት ነው፡፡ |
| 2 | ሳዱላ | በቤት ውስጥ የሚሰራ ሆኖ ሴቷ ካገባች በኋላ የምትላጨው ነው፡፡ ለውጥ እየተደረገበት ነው፡ |
| 3 | አጭር (ክርክም) | በቤት ውስጥ የሚሰራ ሁኖ ሴቷ አግብታ የሳዱላ ጊዜዋን ከጨረሰች በኋላ የምትሰራው ነው፡፡ |
| 4 | ጋሜ ቅርድድ | በቤት ውስጥ የሚሰራ ሁኖ ሴቷ ከማግባቷ በፊት የምትላጨው ነው |
| 5 | ተሬ | በቤት ውስጥ የሚሰራ ሁኖ ህጻን ወንድና ሴት የሚሰሩት ነው |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# አባሪ 4

## የፎቶ አባሪዎች



አጥኝዋ ከነቃሿ ጋር ቃለመጠይቅ ስታደርግ



ጌጣጌጦች በገበያ ላይ




ጌጣጌጦች በገበያ ላይ



ትልቅ መስቀል ና ቀለበቶች

ያደረገች



የጆሮ ጌጦች



ቀለበት ያደረገች



ቁልፍ የደረደረች ሴት



ጋሜና ቁንጮ የተላጨች




ጋሜ ቅርድድ የተላጩ



እንሶስላ የሞቁ እጆች



ጎዶ ቀሚስና ጋቢዎች በማረሚያ ቤቶች



ጋሜ ቅርድድ የጠላጨች



ለምድ የለበሰ ወንድ

ይህ ቴስስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የኔ ወጥ ስራ ሲሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩንቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም [illegible]

ፊርማ ______________

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ 2004ዓ.ም